# ሐመር

ሐመር ፲፮ኛ ዓመት ቁጥር ፫ መስከረም/ጥቅምት ፳፻፩ ዓ.ም



## አቤቱ አዲሱን ሺሕ ዓመት ባርክልን

## እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ አደረሳችሁ

©ማኅበረ ቅዱሳን 

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ስለዘመኑ ሥነ ሥዕል ምን ማስረጃ አለን?

በ፲፪ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያውያን በሥነ ሕንፃና በሥነ ጽሑፍ የተራቀቁበት ዘመን መሆኑን ዓለም ሁሉ የሚመሰክረው እውነታ ነው:: አውሮፓውያን ላሊበላን የሠሩት የእኛ ሰዎች ናቸው ማለት ከጀመሩ ውለው አድረዋል:: ትንሽ ቆይቶ ደግሞ የ፲፬ኛውና ፲፭ኛው ክፍለ ዘመን ሥነ ጽሑፎች ከነለዛቸውና ውበታቸው ወደ እንግሊዝኛ ተተርጉመው መነበብ ሲጀምሩ አርጋኖን፣ ሰዓታትና ማኅሌተ ጽጌ በእንግሊዛውያን መነኮሳት፣... ተጽፈዋል ይባል ይሆን ይሆናል::

የላሊበላ ዘመን /የዛጉዌ/ ኪነ ሕንፃ ቁንጮ ላይ የደረሰበት ዘመን መሆኑን ከ፱፻ ዓመታት በፊት የተሠሩት ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት ምስክሮች ናቸው:: በተጨማሪም በሕንጻው ውስጥ የሚገኙት አንዳንድ ቴክኖሎጂዎች ማለትም ከእንጨት በተቀረፀ ባለጥርስ ተሽከርካሪ /gear/ መሽጎሪያ ያለው በርና በቤተ ጊዮርጊስ ውስጥ ያለው ከእንጨት በተሠራ ብሎን የሚቆለፈው የላሊበላ ሳጥን ስለ ዘመኑ ሥልጣኔ አመላካች ናቸው::

ነገር ግን ስለ ዘመኑ ሥነ ሥዕል ምን ማስረጃ አለን? ሥዕሎች እንደ ድንጋይ ሕንፃ ዘመንን ተሻግረው ለመገኘት እጅግ አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል:: በተጨማሪም በግራኝ ወረራ ጊዜ የእግዚአብሔር ጥበብ ሕንጻውን እንዳያፈርስ ብትከለክለውም፣ ንዋየ ቅድሳትና ሥዕሎች ላይ አደጋ አድርሷል:: ከዚያም በኋላ ጦርነቶች፣ ስርቆትና ዝርፊያም እንዲሁ:: ስለዚህ በላሊበላ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የምናያቸው ሥዕሎች ከዛሬ ሰባና ሰማንያ ዓመት ገዳማ ከተሠሩት አብያተ ክርስቲያናት ባነሰ ሁኔታ የኢትዮጵያን ሥነ ሥዕል የማያንፀባርቁ ሥዕላትን እንመለከታለን:: ይባስ ብሎ በአሸተን ማርያም ቤተ ክርስቲያን የምናገኛቸው ሥዕሎች በወረቀት የታተሙ ዘመናዊ ሥዕሎች ሆነው እናገኛቸዋለን:: በእርግጥ ሁሉም ዘመናዊ ሥዕሎች ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አይውሉም ማለት ሳይሆን ቢቻል በላሊበላ ዘመን የነበሩ ሥዕሎችን በጥናት ላይ ተመሥርቶ በብቁ ባለሞያዎች ቢሠራ ይመረጣል:: ይህ ባይቻል ደግሞ በሌሎች ገዳማትና አድባራት የሚገኙትን ዓይነት ሥዕል መጠቀም የበለጠ ማንነትን ገላጭ ይሆናል:: ቤተ መድኃኔዓለም ያለው የጌታችን ሥዕል ቤተ ማርያም ያለችው የእመቤታችን ሥነ ሥዕል ወዘተ ... ለእኔ ዘመናዊ ሆነውብኛል፤ ለእናንተስ?

ጥንታዊ ሕንፃ፣ ጥንታዊ ቅዳሴ፣ ጥንታዊ ዝማሬ፣ ጥንታዊ ዜማ፣ ትውፊት ሆኖ ነገር ግን በዘመናዊ ሥዕል ሲሆን መንፈሳዊና ኪነ ጥበባዊ ውበቱን በጥቂቱ የሚቀንሰው ይመስለኛል:: በተረፈ የአባቶቻችንን የቅርስና ታሪክ አጠባበቅ እጅግ አደንቃለሁ፤ አመስግኑልኝ::✦

ጌትነት አወቀ
ምሥራቅ ጎጃም

## ማኅበረ ቅዱሳን የቤት ውጭ ዩኒቨርስቲ ቢከፍትስ

ስለ መጽሔታችሁና ጋዜጣችሁ የምለው ነገር የለኝም፤ እከታተላለሁ፣ እማርባቸዋለሁ:: መግለጽ የምፈልገው ስለሌላ ነገር ነው::ዛሬ አጽራረ ቤተክርስቲያን ለጥፋት ተልእኳቸው የመረጃ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ሆነዋል:: የሚሠሩትም በተደራጀ መንገድ ነው:: እኛስ ታዲያ ለምን የመረጃና በዚያም ላይ ተደግፎ የሚሰጥ የማስተማር አገልግሎት አይኖረንም:: በዚህ ረገድ የሚፈለገውን ለውጥ ለማምጣት የምጠቁማቸው መንገዶች አሉ::

፩ኛ. ውጭ ያሉ አብያተ ክርስቲያን ብዙዎች መካነ ድር /Web page/ አላቸው:: በሀገር ውስጥ ግን ታላላቅ የሚባሉት ቁልቢ፣ ግሸን ደብረ ከርቤ፣ ደብረ ሊባኖስ፣ አክሱም ጽዮን ወዘተ ... እንኳን ያላቸው አይመስለኝም:: ምንም የኮምፒውተር ባለሞያ ባልሆንም /ስለ ኮምፒውተር ዕውቀት ባይኖረኝም መካነ ድር ማዘጋጀት ቀላል ነገር ይመስለኛል:: ምናልባት ትንሽ ከበድ የሚለው ሰርቨር አከራዮች የሚጠይቁት ክፍያ ነው:: ያም ቢሆን ከተማ ላሉና አንዳንድ ታዋቂ ለሆኑ አድባራትና ገዳማት መክፈል በጣም ቀላል ሊሆን ይችላል:: እርግጠኛ ባልሆንም እስከ ፩ ወይም ፪ ገጽ በነጻ የሚሰጡ ድርጅቶችም እንዳሉ እሰማለሁ ይህ እንግዲህ የአጭር ጊዜ እቅድ ሊሆን ይችላል::

፪ኛ. ሁሉንም አብያተ ክርስቲያናት በስልክና ኢንተርኔት ማገናኘት፤ ገጠር ያሉትን በሽቦ አልባ ስልክ የከተማዎቹን ደግሞ በባለ ሽቦ ስልክ ማገናኘት፤ ምእመናን በቀላሉ የነፍስ አባቶቻቸውን በሞባይልና ሽቦ ስልክ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት፤ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ደግሞ የኢንተርኔትና ቴሌ ኮንፍረንስ አገልግሎት እንዲያገኙ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ቢያንስ አንድ ኮምፒውተር እንዲኖረው ማድረግ እና ቤተ ክርስቲያን የቴሌ ሴንተር አገልግሎትን በመስጠት ገቢንም እንድታገኝ ማድረግ ይቻላል::

፫ኛ. የሠለጠነ የመረጃና ግንኙነት ቴክኖሎጂን እና የኮምፒዩተር ሳይንስ ባለሞያ ማብዛት፤ ይህን ለማድረግ በቀጣዩ ዓመት በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ፣ በቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ፣ እንዲያም ሲል ማኅበረ ቅዱሳን ኮሌጅ ውስጥ፣ ዲፓርትመንቶችን መክፈትና ሰባክያንን፣ ዲያቆናትንና ካህናትን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማስተማር ነው:: ማኅበረ ቅዱሳን መቼ ኮሌጅ አለውና፤ እንዲያም ቢሆን በ፳፻፩ ዓ.ም እንዴት ሊጀመር ይችላል ትሉ ይሆናል:: መልሴ ግን ይቻላል ነው:: ይህን ስል ከኃይሌ ገብረ ሥላሴ ወስጄ እንዳይመስላችሁ፤ ከጌታችን እንጂ. «ላመነ ሁሉ ይቻላል» ያለውን ማሰብ ነው:: ደግሞስ ምን ያቅታችኋል! የተማረው ሰው በእጃችሁ ነው፤ የቤተ ክርስቲያን ግቢ ደግሞ ሰፊ ነው:: የላስቲክ ዳስ ወይም እንደ በአት ያለ የሣርና ቅጠላ ቅጠል ጎጆ ነገር እየሠራችሁ፤ ያም ባይሆን ዛፍ ሥር ወይም እንደ ካታኮምብ በየዋሻው ኤሌክትሪክ እየዘረጋችሁ ማስተማር ነው:: ኮሌጅ ማለት ሕንፃው ሳይሆን ዕውቀቱ አይደል:: ስንፍናው እንጂ. ማስተማሪያ መንገዱ ብዙም አይፈትንም::

እዚህ ላይ ሊታሰብበት የሚገባ ነገር የምትከፍቱት ኮሌጅ ለመምህራን ክፍያ የሚሆን ገቢ ለማግኘት እንደማንኛውም የግል ኮሌጅ በክፍያ ማስተማር ይችላል:: ተጨማሪ ዲፓርትመንቶችንም እንደ የሁኔታው መጨመር ይቻላል:: የምግብና ዶርሚተሪ ወጭን ለማስወገድ ለመጀመሪያ ዓመታት የምታስተምሯቸውን የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ተመላላሽ ለማድረግ ከአዲስ አበባ ብቻ ታደርጋላችሁ:: የሚያስፈልጋችሁ ብላክ ቦርድ፣ መጽሐፎችና ወደ ፲ የሚጠጉ ላፕቶፖች ሊሆኑ ይችላሉ:: /ላፕ ቶፕ ያልኩት ቋሚ ቤት ስለሌላችሁ ከዴስክ ቶፕ በተሻለ ሁኔታ በየተመቸው ቦታ ለመጠቀም እንዲቻል ነው/ ይህም የመነሻ ካፒታልን /Initial Investment/ በጣም ትንሽ ለማድረግ ይረዳል:: እንግዲህ ከብር 100,000.00 ባልበለጠ ወጭ ኮሌጅ ከፈታችሁ ማለት ነው:: ምናልባት ያለ ሕንፃ ከትምህርት ሚኒስቴር ዕውቅና ለማግኘት ለመጀመሪያ ጊዜ ሊከብድ ይችል ይሆናል:: እነሱ ዕውቅና ሰጡም አልሰጡም እኛ የምንፈልገው የተማረ የሰው ኃይል እንጂ. ሰርተፊኬት ስላልሆነ በቃ ሥራውን መጀመር ነው::

በነገራችን ላይ በጣም ቸኮልክ፤ ስሜታዊ ሆንክ እንዳትሉኝ፤ እጅግ በጣም የሚቸኩለው፣ ስሜትም በሕዝብ ላይ እየፈጠረ ያለው ዓለሙና የመረጃ ቴክኖሎጂ ነው:: እኔ መንፈሳዊ ኮሌጅ ባጭር ጊዜ ክፈቱ አላልኩም፤ በቂ ዝግጅት ያስፈልገው ይሆን ይሆናል:: ይሄ ግን ዓላማው በመረጃ ቴክኖሎጂ የሠለጠነ የሰው ኃይል በሚገባው ቦታ እንዲኖር ማምረት ብቻ ነው::

ደግሞም ከቤት ውጪ /Open Air College/ መሆኑ ትውፊታችንም ጭምር ነው:: በመላዋ ኢትዮጵያ የሚገኙ ገበያዎች ሁሉ ከቤት ውጪ ናቸው:: የአንድነት ትምህርት ቤቶቻችን ከቤት ውጪ ናቸው:: የማታ /የሠርክ/ ጉባኤ ከቤት ውጪ ነው:: ስለዚህ እናንተም ከቤት ውጪ ዩኒቨርስቲ ብትከፍቱ፤ ለሕንፃ የምታወጡትን ገንዘብ ከመቆጠብ አልፎ በትውፊት ጠባቂነታችሁ ትደነቃላችሁ እንጂ. አይሳቅባችሁም:: እንኳንስ ከቤት ውጪ ይቅርና የርቀት /Distance/ ተብሎ ትምህርትስ አለ አይደል:: ባማሩ ሕንፃዎች ውስጥ ከተጻፉ ጽሑፎች ይልቅ በፍጥሞ ደሴት ግዞት ካለምቾት የተጻፉ ጽሑፎች ምንኛ ዘመን ተሻጋሪ ሆኑ! ስለዚህ እናንተም የቤተ ክርስቲያን ሰዎችን «አዝጋሚ» «Passive» የሚል ስም በአጭር ጊዜ ለውጣችሁ በመረጃ ዘመን /Information Age/ ታሪክ ልትሠሩ ትችላላችሁ::✦

ገብረ ማርያም ደሳለኝ
ደሴ

©ማኅበረ ቅዱሳን

የዕለት ምግብ ሲባል ግን ለእኛ የሚታየን ምድራዊ እንጀራ ነው:: ጭንቀታችንም ለእርሱ ነው:: ከሁሉ በላይ ሊያሳስበን የሚገባው ግን ዘላለማዊውና ሰማያዊው ምግብ የሆነው የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው:: /ዮሐ.፮÷፳፯/ ክርስቶስ ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ /የዘላለም ምግብ/ ነው:: /ዮሐ.፮÷፶፩/

### በረከተ ወንጌል

ለክርስቲያኖች ከሥጋችን ኑሮ ይልቅ የነፍሳችን ጉዳይ የበለጠ አሳሳቢ ነው:: ይኸኛው ዓለም እጅግ የተመጠነ ዘመንና በሞትም የምንለየው ነው:: ይህንንም ያለ ነጋሪ ያለምስክር ሰው የሆነ ሁሉ ይረዳዋል:: ድካማችን በዚህ ዓለም እስካለን ድረስ ብቻ ነው::

### የኢትዮጵያ ሣልሳይ ሺሕ

የሃይማኖተ አበውም አመራርም ሲነቃበት እየወጣ ደግሞም እየተመለሰ ከሁለት ጊዜያት በላይ ተመልሶ ወጥቷል:: የአሁኑም ጥያቄው ከቀድሞው ግብሩ ሊመልሰው አይችልም:: በዚህ ጠባዩም ከዕሪያዋ ጋር ይመሳሰላል:: ዕሪያ እንደ ታጠበች ፈጥና ጭቃ ውስጥ ገብታ እንደምትንከባለለው የሃይማኖተ አበውም ጥያቄ ፈጥኖ ወደ ቀደመ ግብሩ በሰፊው ለመግባት ያቀረበው ነው::

### ወቅታዊ ጉዳዮች

የእኛን ቤተ ክርስቲያን አተረጓጐም ምንነትና የዚያኛውን ችግር የመፍታት አቅሙን ብታሳይ የተጠቀሰው ምክንያት የበለጠ ግልጽ ይሆን ነበር:: ይሁን እንጂ ይህ አለመሆኑ የተመራማሪ ፍላጐትን ባያረካም እውነታውን ስለማያስቀረው ወደ ጉዳዩ እንለፍ::

### ኪነ ጥበብ

የካህን ሕይወት በሁሉም አቅጣጫ በሚገባ የተጠበቀ ከሆነ ለጠላት አይጋለ ጥም:: ነገር ግን ትንሽ ለሆነ ነገር እንኳ ትኩረት ሳይሰጥ ቢቀር በሰው ጠባይ ዘንድ እንደሚታየው ሌሎቹ መልካም ሥራዎቹ ከከሳሾቹ አፍ እንዲያመልጥ አይረዱትም:: ነገር ግን ያ ትንሽ ሕጸጽ ሌላውን ሁሉ ይሸፍነዋል፤ ጥላውን ያጠላበታል::

### ትምህርተ ሃይማኖት


| | |
|---|---|
| ዋና አዘጋጅ | - ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ |
| ም/ ዋና አዘጋጅ | - ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ |
| አዘጋጅ | - ዲ/ን ማለደ ዋስይሁን |
| ሪፖርተሮች | - ጌታቸው በቀለ |
| | - ዲ/ን ምትኩ አበራ |
| ሌይ አውት ዲዛይነር | - ርብቃ ኃይለማርያም |
| ጸሐፊዎች | - ጸዳሉ ሁንዴሳ |
| | - ልደት አስፋው |
| | - ደብረወርቅ ተክለጽዮን |

የዝግጅት ክፍሉ:
Email:- hamermk08@gmail.com

የማኅበሩ ጽ/ቤት
E-mail: eoc-m-kidusan@ethionet.et
www.eotc-mkidusan.org

በማኅበረ ቅዱሳን የሰሜን አሜሪካ መካነ ድር
www.mahiberekidusan.org

መ.ሣ.ቁ 80078
አዲስ አበባ


## «ማኅበረ ቅዱሳን»

እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና አማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ
ይህን ስያሜውን አግኝቷል::


ሐመር
፲፮ኛ ዓመት ቁጥር ፫
መስከረም/ጥቅምት ፳፻፩ ዓ.ም.


# ይዘት


**መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን**

✱ የይሁዳ ሰላምታ የቀረ ሒሳብ ማስተካከያ ነው ........ ፪

**ደብዳቤዎች** ........ ፬

**በረከተ ወንጌል**

✱ «የዕለት ምግባችንን ዛሬ ስጠን» ........ ፭

**የኢትዮጵያ ሣልሳይ ሺሕ**

✱ ሰውም ጊዜውን አያውቅም ........ ፯

**ወቅታዊ ጉዳዮች**

✱ መዝሙራችን ወዴት እያመራ ነው? ........ ፲፪

✱ የ «ሃይማኖተ አበው» ሚጠት /መመለስ/ የእሪያ እጥበት ........ ፲፮

**ትምህርተ ሃይማኖት**

✱ ክህነት በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርት ........ ፳፩

**ምሰሶ** ........ ፳፭

**ኪነ ጥበብ**

✱ «ጡቶችሽም የወይን ዘለላ ይመስላሉ» ........ ፳፮

**እናስተዋውቃችሁ**

✱ በጆሮአችን የሰማነውን በዐይናችን አየነው ........ ፳፱

**ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ**

✱ እናንተስ 'ሀብትንና ክብርን' ሹ፤ ሌላው ሁሉ አይታወቅም ........ ፴፫

**ስቡጊዶ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት**

✱ ትውልድ የኀልፍ ወትውልድ ይተርፍ ........ ፴፱



*በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደ ራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነት ዋና ክፍል በመጽ ሔት ዝግጅት ክፍል የሚዘጋጅ ትምህር ታዊ መጽሔት::*

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥር ዐተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ::*

መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን።

# የይሁዳ ሰላምታ የቀሪ ሒሳብ ማስተካከያ ነው




ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይሁዳን ከሐዋርያት እንደ አንዱ የመረጠበት ምስጢር እጅግ ጥልቅ ነው። ይህን ባናውቅ፣ ታሪኩ ባይጻፍና መምህራኑም በየጊዜው ባይ ነግሩን ኖሮ ዛሬ ብዙ ዎቻችን እንጨነቅ እንታወክም ነበር። እርሱን እንድናስታ ውሰው ያደረገን ደግሞ «ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማ ሪዎች ማኅበር» ያቀረበው ተደጋጋሚ ጥያቄ ነበር፤ በቤተ ክርስቲያኒቱ ፈቃድ ተሰጥቶት የመንቀሳቀስ ጥያቄ። ጉዳዩን በቀጥታ ከማየታችን በፊት ግን ጌታችን ይሁዳን ሐዋርያ አድርጎ በመምረጡ ካስተማረን ትምህርት እንነሣ።

በትውፊት እንደሚታወቀው ይሁዳ ሳያውቀውም ቢሆን አባቱን ገድሎ እናቱን አግብቶ ይኖርበት ከነበረው ሕይወት የመጣ ሰው ነው። ጌታችን ንስሐውን ተቀብሎ እርሱን ከሐ ዋርያት እናቱንም ከቅዱሳት አንስት ደመራቸው። ጌታ አም ላክ ነውና የይሁዳን ምንነት ብቻ ሳይሆን ወደፊት ርሱንም እንደሚሸጠው እያወቀ ለምን ሐዋርያው አደረገው? ልንል እንችላለን። ቢያንስ የሚከተሉትን ነገሮች እንድንማር ነው።

ጌታ ለሚመለሱት ሁሉ እውነተኛ መሐሪ ነው። በተመለ ሰበት ጊዜ ፈጽሞ ይቅር ብሎ ወደ ማኅበረ ሐዋርያት ማም ጣቱ ፍጹም ፍቅሩንና ለተልእኮ የሚመርጠውም ሰው ተነ ሳሒ መሆኑን ያሳየናል። ጌታችን ድንግላዊ ዮሐንስን ብቻ አልመረጠም፤ ይህ እንግዲህ የሐዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ተነሳሕያን ለቅድስና የሚያበቃ የጽድቅ በር መክ ፈቷን የሚያውጅ ነበር። በዚህም የጌታችንን ፍጹም ይቅር ታና የምርጫውን ፍጹምነት እንማርበታለን።

ከዚሁ ጋር ተያይዞም ጌታችን ምንም አምላክ በመሆኑ የነገውን የይሁዳን ድርጊት ቢያውቅም ገና ባልበደለው በደል ግን ቀድሞ አልገፋውም። በዛሬ ማንነቱ ብቻ የተቀበለውን ሰው ክብሩንም ሓሳሩንም የሚወስነው ዛሬውኑ በሠራው ሥራ መሆኑን ለማስተማር ነው። የዚህ ተጨማሪ ጉዳይ ደግሞ ክፉን ሰው ምክንያት ማሳጣት የሚገባ መሆኑንም ለመናገር ነው። ይሁዳን በመዋዕለ ስብከቱ ከክብር ሳያሳንስ፣ መዓርግ በመስጠት ያኖረው በኋላ ሹመት አጉድሎብኝ ነው እንዳይ ለውም ጭምር ነበር። በዐሥራት ላይ ሾሞ፤ የገንዘብ ፍላጉ ቱንም እንደተመኘ ይወጣለት ዘንድ ነጻ ፈቃድን ሰጥቶ ስርቆቱን ታግሶታል። ጌታ ዐሥራቱን በሌላ ሐዋርያ እጅ ቢያደርገው እንዲጠበቅ እያወቀ ለይሁዳ የሰጠው ጾሩ ቢቀ ልለት ብሎ ብቻ ሳይሆን ምክንያትም ሊያሳጣው ነውና። ይህም ከሆነ በኋላ ሲሰርቅ በፍጹም ታግሦታል። ስለዚህም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ዘክርስቶስ እንደ ይሁዳ ሙዳየ ምጽዋት የሚገለብጡትን እንደ ይሁዳ ታግሣቸው ትኖራ ለች። የይሁዳን የሌብነት ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን ያየነው ደግሞ በጸሎተ ሐሙስ ዕለት ማታ እጁን ከወጭቱ መስደዱን ጌታ ገልጦ በመናገሩ ነው። «የለመደ ልማድ ከማድ ያሰርቃል» እንደሚሉት እንኳን ለሌላ ከመጣው ለራሱም ከተሰጠው የሚሰርቅ ምን ያህል ቢከፋ ይሆን? ዛሬም እንደ ይሁዳ ውሳጤ ውሳጢት /ቅድስተ ቅዱሳን/ ገብተው ለእነርሱ ብቻ የተፈቀ ደው ምስጢር ላይ እጃቸውን ያለአግባብ የሚጭኑ÷



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

መጻሕፍቱንና ንዋያቱን የሚሰርቁ ሲያጋጥሙ ቤተ ክርስቲያን ብታዝንም የማትታወከው ነገሩን ቀድማ ከይሁዳ ሕይወት ስለ ተረዳችው ነው። ከላይ የጠቀስናቸውን ሁሉ ብዙ ጊዜ ሰምተ ናቸው ይሆናል። ችግሮቹም በየጊዜው የሚገጥሙን ስለሆነ አሁን አሁን አያስደንቁንም።

ትልቁና ዋናው ጉዳይ ይልቁንም ለዛሬው ጉዳይችን የሚቀርበው ይሁዳ በመጨረሻው ሰዓት የፈጸመው ድርጊት ነው። ይሁዳ ተጠቃሚ ስለነበር ከሐዋርያት ጋር ጌታን እየተከተለ ይቆይ እንጂ ልቡ እንደ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ነበር። ይህም የታወቀው ሠላሳ ብር የጐደለበት በመሰለውና ማንነቱ በተነገረው ጊዜ ወደ እነርሱ በማምራቱ ነበር። ጌታም ራሱ ይሁዳ ባለበት ስለይሁዳ የተናገረው በአካል ከሐዋርያት ጋር ቢሆንም በምግባርና በአመለካከት ከእነ ሀና እና ቀያፋ ጋር በመሆኑ ነበር። በይሁዳ ሕሊና ያለው ግን አሁንም ሌላ ብልጠት ነበር። በመጀመሪያ ደረጃ ራሱን የተሻለ አሳቢ አድርጎ ስለወሰደ ከሐዋርያት ተደብቆ ከፈሪሳውያን ገንዘብ ተቀብሎ ጌታን አሳልፎ ከሰጠ በኋላ ጌታ በተአምራት ሲሰወርለት ገንዘቡንም አግኝቶ ከሐዋርያትም ጋር ሆኖ ለመኖር ነበር። ይህ ባልተሳካለት ጊዜ /ጌታ ራሱን አሳልፎ በሰጠ ጊዜ/ ደግሞ ፈጥኖ የታነቀው ሲኦል ገብቼ ካገኘኹም ትቶኝ አይወጣም ብሎ ጽድቁንም በብልጠትና በቀመር ሊፈጽም ነበር። ሁሉም ግን አልተሳካም። ድኅነትን በየዋሕነትና በእውነተኛ ንስሐ እንጂ በብልጠትና በቀመር ሊያገኙት አይቻልምና።

ይሁዳ ከማርያም ባለሽቱዋ ቀረብኝ ያለውን ገንዘብ ለማግኘት የተጠቀመበት ስልት «ሰላምታ» ነበር። ነገሩን ከሊቃነ ካህናቱ ጋር ከጨረሰ በኋላ እርሱ «ሰላም» ብሎ ሊሰጥ በዚህም እነርሱ ጌታን ይይዛሉ፤ ለእርሱ ደግሞ እንደመሰለው በስውር ገንዘቡን ተቀብሎ ከጌታም ጋር ሊኖር ነበር። የዚህ ነገር ፍጻሜው ታላቅ ጥፋት መሆኑን ብናውቅም ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ይህን ስልት እየተጠቀሙ ደሟን የሚያፈስሱ ጠላቶቿ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ከቤተ ክርስቲያን እንደማይጠፉ እውነተኛውን ትምህርት ትቶልን አለፈ።

በዕሥራ ምእቱ መጨረሻ በ«ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» ስም የሚወጡት የሚወርዱት «ውስጠ ዘ»ዎች ጥያቄም ከዚህ የተለየ አይደለም። እንደ ይሁዳ ቤተ ክርስቲያን ነበሩ፤ እንደ እርሱ ኮረጆአቸውን ይዘው ከዓለም አቀፍ የፕሮቴስታንት ተቋማት የሚፈልጉትን ሰበሰቡ። ቤተ ክርስቲያን ግን እንደ ይሁዳ አቅርባ ሾመቻቸው። ከአንድም ሁለት ጊዜ ጥያቄያቸውን ተቀብላ ፈቃድ ሰጥታ ቢሮ ከፍታ ሰየመቻቸው። እነርሱ ግን ከግብራቸው አልተመለሱምና ማኅበሩ በይፋ ተዘጋ። ደግነቱ ይሁዳ ገንዘቡን ለራሱ በተመኘ ጊዜ ሐዋርያትን ጨምሮ ለማሳመጽ «ይህ ሽቶ ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ለምንድን ነው?» በሚል ደስ በማያሰኝ ቃል ቅስቀሳውን ቢያደርግም ከሐዋርያት የተከተለው አለመኖሩ ነው። ሃይማኖተ አበውም ከጥንቶቹ ቀናዕያንና ንጹሐን አባላቱ እርሱን የተከተለው የለም። እነርሱ እንደ ሐዋርያት በታማኝነት አገልግሎታቸውን ቀጥለዋልና። ይሁን እንጂ በመካከለኛ ዕድሜ ከነበሩ ወጣት ዘማርያን መካከል ለሙሉ ወንጌል፣ ለሬማና ለመሳሰሉት የገበራቸው ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን የሚዘነጉ አይደሉም፡ አሁንም የሚያሳዝኑን ሆነው ቀርተዋልና።

ይህ ሁሉ ሳይንሰው አሁንም በተድበሰበሰ መንገድ እንደገና ፈቃድ ይሰጠኝ፤ ቢሮ ልክፈት የሚለው ጥያቄውን አቅርቧል። ይህ ጥያቄ ጥንት ማኅበሩን መሥርተው በቅን መንገድ ቤተ ክርስቲያንን አገልግለው፤ የማኅበሩ አመራር ማኅበሩን ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ሲወስደውም እነርሱ በቤተ ክርስቲያናቸው ጸንተው ከቀጠሉትና አሁንም እያገለገሉ ካሉት እውነተኛ ልጆቿ ቀርቦ ቢሆን ኖሮ ምን ያህል ያስደስት ነበር። ስለዚህም እነዚህን አካላቱን ለስምና ለዝና ብቻ የሚፈልጋቸውና የተደበቀ ጅምር ዓላማውን /ፕሮቴስታንት የማድረግ ግቡን/ ይዞ ሲንቀሳቀስ የኖረው የማኅበሩ አመራር ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሓላፊ በኩልና ራሱም አድበስብሶ ያለ ማንም ሰው ፊርማ ያቀረበው ጥያቄ ዝም ተብሎ የሚታለፍ አይደለም።

ማእምረ ኅቡአት ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰወረውን ዓላማ የሚገልጥበት ጊዜው ሩቅ ባይሆንም እንዲህ ያለው ቀረቤታ ከይሁዳ ሰላምታ ተለይቶ የሚታይ ሊሆንም አይችልም። ይሁዳ ጌታችንን ሰላም ያለው በአይሁድ ለማስያዝና ቀረብኝ ያለውን ገንዘብ ለማግኘት እንደነበረው ሁሉ የዚህ ጥያቄ ዓላማም ያውቀሪ ሒሳቤን ላወራርድ የማለት ይመስላል። ለእርሱ ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችን የዚህን «ሰላምታ» ትርጉም ነግሮናል፤ መልእክቱንም አስተምሮናል። ምክንያቱም ጌታ ይሁዳን ንስሐም ሲገባ ያውቀዋል፤ ሊያታልለውም ሲመጣ ያውቀዋል። ይሁዳ አጥፍቶ ነው የወጣው፤ ስለዚህ ሲመለስ ንስሐ ይጠበቅበት ነበር። የእርሱ መልስ ግን ቀሪ ሒሳብ የማወራረድ ስለነበር ለንስሐ ፈቃደኛ አልነበረም። ስለዚህም በሰላምታው ሽንግሎ ቀሪ ሒሳቡን ለመውሰድ የመጨረሻ ዕድሉን ተጠቀመ።

የ«ሃይማኖተ አበው» መሪዎችም እውነተኞች ቢሆኑ ኖሮ ማኅበር እንደመሆኑ መጠን ያጠፉትን ጥፋት ራሳቸው ዘርዝረው አቅርበው፤ ለዚያ የዳረጋቸውን ምክንያቱን ለይተው ቤተ ክርስቲያንን ለበደሉበት ይቅርታ ጠይቀው አጥፍተዋቸው ለቀሩት ልጆቿ እውነተኛ ንስሐ ገብተው ቢመለሱ እንዴት ባማረባቸው ነበር። በዚህ ጊዜ ቢቻል ሌላ ሃይማኖት የገቡትን ለመመለስና ለንስሐ ለማብቃት ቢጥሩ በይፋ ስሕተታቸውን ገልጸው ጥፋታቸውን ነግረው ቢመለሱ ኑሮ አሁንም ያለው አገልግሎት እንኳን ለእነርሱ ሌላም ቢፈጠር የሚጋብዝ ነበር። ይህን ግን አላደረጉትም። ሊያደርጉት ሲጥሩም አይታዩም። ይልቁንም ውስጥ ለውስጥና በድብቅ እንደገና የጨለማ ሥራ፤ የይሁዳ ሽንጐ። ለሃይማኖተ አበው አመራርና ደጋፊዎቹም ሁልጊዜም ቤተ ክርስቲያን አልገባት /አልበራላት/ ብሎ እንጂ እነርሱማ አይሳሳቱማ። «እግዚአብሔር ሰማዩን ጠቅልሎ ሸሸ» እንዳለ ሰይጣን፡ «እኔ ወረድኩ» ማለትንማ አይሞክሩትማ። እንዲህ ካለማ እውነት ሊወጣው ነው። አሁንም ግን ለትክክለኛው መንገድ ጊዜው አልመሸም፡ ልቡ ካለ። ካለበለዚያ ግን ጥያቄው ከይሁዳ ሰላምታ ፍጻሜውም ከእርሱ ፍጻሜ አያልፍም። ለዚህ ጉዳይ የቀድሞ እውነተኞቹ አባላት ዛሬም እንደ ጥንቱ ሓላፊነት አለባችሁ። በጎውን ዓላማ ማጥፋትና መንገዱን ማሳታቸው ሳያንሳቸው ጥፋታቸውን በስማችሁ ለማሳት መምጣታቸውን መግለጥ ያለባችሁ እናንተ ናችሁና። የቤተ ክርስቲያናችን አባቶችም ጌታቸውን በመመሰል ይሁዳን እንደ አመጣጡ እንደሚመልሱት የታመነው ነው። ንስሐ ሲገባ ይቀበሉታል፡ አሳልፎ ሊሰጥ ሲመጣማ ጌታችን እንደጠየቀው «ለምን ነገር መጣህ?» ብለው ይጠይቁታል እንጂ ዝም አይሉትም። ስለዚህም ተጠየቅ፡ ለምን ነገር መጣህ? አብረውህስ ያሉት እነ ማን ናቸው? ሾተሉና ዱላውስ የማን ነው? ✥

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር።*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ አስታወሰኝ

በሐመር መጽሔት ፲፮ኛ ዓመት ቁጥር ፩ ከታተመው «የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥርዓት አፍሪካውያንን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ወደ ሃይማኖት የመሳብ አቅም አለው» በሚል ርዕስ ያቀረበው ጽሑፍ «ተዋሕዶ ታብባለች ታፈራለች ገና ...» የሚለውን መዝሙር ዕውነተኛነት ያረጋገጠልን።

ካሣ /ኬዝ ሌዛ ቤሪ/ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያለው እውቅና ክርስትናውን ከልጅነት ጀምረን ይዘነዋል ከምንለው ብዙዎቻችን የተሻለ ሕይወት ላይ እንደ ደረሰ የሰጠው ምስክርነትና የወደፊቱ ራዕዩ ይመሰክራል።

ሌሎች መረዳት በማይችሉበት ደረጃ ላይ ያሉ በመሆቸውና በሌላ በኩልም ከወጣን አይመልሰን ካላሉ በቀር! እርሱ ክርስቶስ ቤዛ የሆነላት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት እንደተባለው «ከመሳብ አቅም» በላይ በአንድ አቅፋ መያዝ የምትችል ነች። ሆኖም ቤተ ክርስቲያን በሥርዓቷ ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደትን... የያዘች በመሆኑ በዚህ መንገድ ለማለፍ ብዙዎች ከብዶባቸው ዓይናቸውን ገልጠው ልባቸውን የዘጉ በርካታ ናቸው።

ካሣ /ኬዝ ሌዛ ቤሪ/ ደግሞ ከኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የሚለየው በተወሰነ ደቂቃ ስብከት ፈጥኖ በማመን አለመግባቱ እንጂ ሃይማኖትን በመማርና በመረዳት ከዘለቀ በኋላ የሥላሴ ልጅነትን ማግኘቱ ታላቅ ተሰጥኦ /ዕውቀት/ በመሆኑ መታደል ነው። በዙዎች ምንም ሳያውቁ ፈጥነው ያምኑና እስከ መጨረሻው ሳይዘልቁ ወደ ነበሩበት ብልሹ ጉዳይ ሲመለሱ ይታያሉ።

ወንድም የሆነን ካሣ /ኬዝ ሌዛ ቤሪ/ የእግዚአብሔር ልጅነትን ለማግኘት! በእርጋታ በማስተዋል የፈጸመው በመሆኑ እጅግ ተደናቂ ነው። እንዲያውም እኛ የባእዳን እምነት እየናፈቀን ስንኮበልል፣ እነሱ ወደኛ ወደ እውነተኛይቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እየመጡና ስለ ሃይማኖታችን ጠንቅቀው አውቀው ሲገልጹልን ስንመለከት እኛስ የት ነው ያለነው ያስብላል። ወንድማችንንም ከጠላት ሰይጣን ጠብቆ ለመንግሥተ ሰማያት ያብቃልን።♦

*ጽዮን ታደሰ*
*ከዩናይትድ ዐረብ ኢምሬት ሻርጃ*
*እና*
*ሀጋዬ ዘውዴ*
*ከሰሜን ወሎ ወልዲያ*

## ሳይቃጠል በቅጠል

ከትናንት ወዲያ በነዮዲትና ግራኝ አሕመድ፣ ትናንት ዐረቦች አሠልጥነው ባሰማሯቸው አክራሪ እስላሞች ቅድስት ቤተክርስቲያን ከአጸዷ እስከ አገልጋይ ካህናቶቿ ድረስ አጥታለች። በዚህ ብቻ ቢበቃትም ጥሩ ነበር፤ እጅግ አሳሳቢ ሆኖ የአገኘሁት የወደፊቱን ስጋቴን ደግሞ እንዲህ ላዋያችሁ። የደሴ አክራሪ እስልምና ተከታዮች በቤቶቻቸው ላይ የሀማስን ሰንደቅ ዓላማ በመስቀል «ይህ የእስላም ቤት ነው» የሚል ጽሑፍ በቤቶቻቸው ላይ መጻፍ መጀመራቸውን የሰማሁት ሰሞኑን ነው። ለመሆኑ ምን አቅደው ይሆን? እግዚአብሔር እስራኤላውያንን አንለቅም ባሉት ግብጻውያንና በፈርዖን ላይ ያዘዘውን ሞተ በኩር በእስራኤላውያን ላይ እንዳይደርስ ጠቦት በማረድ ደሙን በበራቸው ላይ እንዲረጩ፣ ይህም የእነሱ መለያ እንደሚሆንና እግዚአብሔርም ትእዛዙን/ቁጣውን/ በግብጻውያን ላይ ብቻ እንደሚፈጽም ተነግሯቸው እንደነበር ታሪክ ጠቅሰው መምህራን አስተምረውኛል። ይህን ሳስታውስ ምናልባት የደሴ እስላሞች የራሳቸው መለያ አድርገውት ይሆን እንዴ? ብዬ አሰብኩ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ቅድመ ጥንቃቄ ልታደርግና ልታስብበት ይገባል። ደሴዎችንም ሳይቃጠል በቅጠል ነውና የራሳችሁን ጥንቃቄ አድርጉ በሉልኝ።♦

*ጌትነት አወቀ*
*ከምሥራቅ ጎጃም*
*ሞጣ*

## ወዴት ለመጠጋት!

በሐመር መጽሔት ፲፮ ዓመት ቁጥር ፪ በመዝሙሮቻችን ዓምድ ሥር ከሦስት ሰዎች ጋር የተደረገውን ቃለ ምልልስ አንብቤዋለሁ። ከጽሑፉ የሁለቱ ተመሳሳይ አቋም ሲኖረው ከዘማሪው ጋር ያለው ግን በይዘቱ ለየት ይላል። እንኳን ሌላው «ሁለት ድንጋይ ሲጋጭ» የሚፈጠረው ድምፅ የቅዱስ ያሬድ ነው ይላል። እዚህ ላይ የተራራቁ ዘመናትን አቀራርቧል። የድንጋይ ድምፅ ከቅዱስ ያሬድ ዜማ ጋር ከተመሳሰለ እስከ ቅዱስ ያሬድ ዘመን ድረስ ድንጋዮች አልተጋጩም ወይም ድምፅ አላሰሙም እንዴ? ያሰኛል። የሥነ ፍጥረት ጉዳይ ችግር ገጠመው። በሌላ አገላለጽ የፍጥረት ድምፅ ከቅዱስ ያሬድ ዜማ ጋር ከተመሳሰለ /የድንጋዩ፣ የወፉ፣ የአራዊቱ... ከቅዱስ ያሬድ መነሣት በፊት የነበረው ዘፈንና ዳንኪራ ሁሉ» የቅዱስ ያሬድ ዜማ ለእርሱ ብቻ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ነው የሚለውን አስተምህሮ ጥያቄ ውስጥ ያስገባዋል። ስለዚህ የሚጮህ ድምፅ በሙሉ የቅዱስ ያሬድ ነው የምንለው ... ወዴት ለመጠጋት ነው?...♦

*ሲአ*
*ከአ.አ ዩኒቨርስቲ ድኅረ ምረቃ*
*ሳይንስ ፋኩልቲ*

## ኅትመቶቻችንን እንጠብቃቸው

ሐመርና ስምዐ ጽድቅን ማንበብ ከጀመርኩ በርካታ ዓመታትን አስቆጥሬአለሁ። ታዲያ በእነዚህ ዓመታት ብዙ ቁም ነገሮችን ገብይቻለሁ። እነዚህንም ኅትመቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገሩ በመሆናቸው በሥርዓት ይዣቸዋለሁ። በክብርም አስቀምጫቸዋለሁ። በጣም ነው የምሳሳላቸው፤ ምክንያቱም ቃለ እግዚአብሔርን የያዙ ናቸውና። ብዕሬን ከወረቀት እንዳገናኝ ያስገደደኝ ነገር ምን መሰላችሁ እነዚህን ኅትመቶች በአንድ ሱቅ ውስጥ ለሸቀጣ ሸቀጥ መጠቅለያነት ሲጠቀሙበት አይቼ በጣም አዘንኩ። ከሱቁ ባለቤት ጋርም ተጣላሁ። ያንንም የተገነጣጠለ ጋዜጣና መጽሔት ወደ ቤቴ ይዤ ሔድኩ። ጋዜጣውና መጽሔቱ የሚታተሙት የእኛን ነፍስ ለማዳን፣ ያልሰማ እንዲሰማ፣ የሰማ እንዲያሰማ፣ ያላወቀ እንዲያውቅ ነው። በማወቅም ይሁን ባለማወቅ እነዚህ ቃለ እግዚአብሔርን የያዙትን ሕትመቶች እንዳይሸጡ በየቤታችን ቤተሰቦቻችንን ልንመክር፣ ልናስተምራቸው ይገባል።♦

*ተስፋዬ አበበ*
*አዲስ አበባ*

---

*ከዚህ በታች ስማችሁ የተዘረዘረው አንባብያን ደብዳቤዎቻችሁ ደርሰውናል። እናመሰግናለን። መልእክቶቻችሁንና የጥቆማ ሐሳቦቻችሁን ወደፊት እንደ አስፈላጊነታቸው እንጠቀምባቸዋለን። በተሳትፎአችሁ ቀጥሉበት።*

*ጥላሁን ያዜ-ምሥራቅ ጐጃም፣ አቶ ገበየሁ በላይ- አርባ ምንጭ፣ እሴተ ማርያም-አዲስ አበባ፣ ዲ/ን ደሴ ገላዬ- ጐንደር፣ ጌጡ ሲሳይ- ባሌ ጐባ፣ መዝገቡ ጌትነት- ምዕራብ ጐጃም፣ ዲ/ን ዳንኤል ተወዳጅ- ጋሞጐፋ፣ ዲ/ን ዓለምነህ ግዛው- ሚዛን ተፈሪ፣ መ/ር ሲሳይ አበበ- ደሴ፣ ደሳለው ተሻለ- አዊ ዞን፣ አስፋው ገብረ እግዚአብሔር- ዱራሜ፣ ተስፋዬ ከበደ- ጐንደር፣ ዲ/ን ብዙአየሁ በርሔ- አዋሳ።*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «የዕለት ምግባችንን ዛሬ ስጠን»

/ማቴ.፮፥፲፩/

/በሊቀ ትጉኃን ሙሉጌታ ስዩም/

ይህ ቃል ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ «አባታችን ሆይ ...» ብላችሁ ጸልዩ ብሎ ስለጸሎት ካስተማረው ትምህርት የተወሰደ አንዱ ክፍል ነው::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዕለት ምግባችንን ዛሬ ስጠን ብላችሁ ጸልዩ ብሎ ያስተማረን ስለምድራዊ ምግባችን ስንጸልይና እርሱንም ስንሻ ብቻ እንድንኖር አይደለም:: ይልቁንም ለነፍሳችንም የሚሆን መንፈሳዊ ምግብ እንዲያስፈልገን ዐውቀን ለእርሱም ጭምር እንድንጸልይ ነው:: ሰው በነፍስና በሥጋ ተዋሕዶ የተፈጠረ በመሆኑ ለሕይወቱ ሁለት ዓይነት ምግብ ያስፈልገዋል:: እነዚህም ሥጋዊና መንፈሳዊ ምግብ ናቸው:: ስለሆነም በዚህ የጌታ ትምህርት ተጠቅሶ የምናገኘው የሥጋን ምግብ ብቻ ሳይሆን የነፍስንም ምግብ ነው:: የዕለት ምግባችን የሚለው ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት::

፩. የዕለት እንጀራ /ምግበ ሥጋ/
፪. የእግዚአብሔር ቃል
፫. የክርስቶስ ሥጋና ደም

እነዚህ ሦስቱ ለአንድ ሰው የሚያስፈልጉት የነፍስና የሥጋ ምግቦች ሲሆኑ የመጀመሪያው ለዕለት /ለቁመተ ሥጋ/ የሚያስፈልግ ምድራዊ ምግብ ነው:: በሁለተኛና በሦስተኛ ደረጃ የተጠቀሱት ደግሞ ሰው ከእግዚአብሔር ተስፋ ለሚያደርገው ዘላለማዊ ሕይወት የሚያበቁ ሰማያዊ የነፍስ ምግቦች ናቸው::

ሰው ምድራዊ እንጀራ ካልተመገበ በሥጋው ቆሞ ለመሄድ የሥጋ ሥራውንም በተገቢው መንገድ ለማከናወን እንደማይችል ሁሉ ነፍሱም የሚገባትን መንፈሳዊ ምግብ ካላገኘች በነፍሱ ሕያው ሊሆን ዘላለማዊ ሕይወትም ወርሶ ከፈጣሪው ጋር በተገቢው መንገድ ሊኖር አይችልም:: ሰው ፍጹም ሕይወት እንዲኖረው ሦስቱም ምግቦች ያስፈልጉታል:: ይህንን ከመጀመሪያው የአዳም የገነት ኑሮና አመጋገብ ጋር አያይዘን ስንመለከተው ሰፊ ትምህርት አለው::

አዳም በገነት ሳለ እግዚአብሔር ሦስት ዓይነት ዕፅዋትን አዘጋጅቶለት ነበር:: ከነዚህም አንዱን ብላ አንዱን ደግሞ አትብላ ብሎታል:: አንዱን ግን ብላም አትብላም አላለውም:: ብላ ያለው ምግቡን ነው:: አትብላ ያለው ዕፀ በለስን ነው:: ብላም አትብላም ያላለው ዕፀ ሕይወትን ነው:: አዳም አትብላ የተባለውን ዕፀ በለስ ሳይበላ ጸንቶ የተፈቀደለትን ዕፅዋት ብቻ እየበላ ቢቆይ ኖሮ ሺሕ ዘመን በገነት ኖሮ ዕፀ ሕይወትን በልቶ ታድሶ መንግሥተ ሰማያት ይገባ ነበር:: /ውዳሴ ማርያም ትርጉም፣ ዘሐሙስ/

በዚህ ዓለምም ሲኖር በገነት በተዘጋጀለት ዕፀ ሕይወት ፈንታ ዘላለማዊ ምግብ ተዘጋጅቶለታል:: ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም እንደተረጎመው ዕፀ ሕይወት የተባለ ሥጋ ወደሙ ነው:: የሰው ልጅ በገነት በሠራው ስሕተት ያጣውን ዕፀ ሕይወትን መልሶ ያገኝ ዘንድ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ክሶለታልና:: ስለዚህም ፊተኛዋ ሔዋን ያልተፈቀደላትን ዕፅ በለስ በልታ ለአዳምም አብልታ ሞትን ለሰው ልጅ ብታተርፍም ዳግማዊት ሔዋን ድንግል ማርያም ዕፀ ሕይወት የሆነ የጽድቅ ምግብ ክርስቶስን ወልዳ ለሰው ልጆች የሕይወት ምግብ አስገኝታለች:: ይህንንም ቅዱስ ያሬድ በአንቀጸ ብርሃን ድርሰቱ «አንቺ የተባረክሽ ዕፅ ነሽ፤ የሕይወትና የደኅንነት ዕፅ ነሽ፤ በገነት ውስጥ ባለው ዕፀ ሕይወት ፈንታ በዚህ ዓለም የሕይወት ዕፅ ሆንሽ፤ ፍሬሽም የሕይወት ፍሬ ነው::» በማለት የሕይወት ፍሬ /ዕፀ ሕይወት/ የተባለ ክርስቶስ እንደሆነ አስቀምጦታል::

ሰው በዚህ ዓለምም ሲኖር የዕለት ምግቡ ምድራዊ እንጀራ ብቻ ሳይሆን፣ ቃለ እግዚአብሔርንና መንግሥተ ሰማያትን ይወርስ ዘንድ የተዘጋጀለትን የክርስቶስን ሥጋና ደም መመገብ እንደሚገባው እንረዳለን:: በጌታ ትምህርትም የዕለት ምግብ የሚለው የዕለት ምግብን፣ ቃለ እግዚአብሔርንና ሥጋወደሙን በመሆኑ እነዚህን በዝርዝር ቀጥሎ እንመለከታለን::

## ፩. የዕለት እንጀራ /ምግበ ሥጋ/

ሰው ለቁመተ ሥጋ የግድ የሥጋ ምግብ ያስፈልገዋል:: አባቶቻችን «እንበለ ሥጋ ኢትቀውም ነፍስ» እንዲሉ፤ የነፍስንና የሥጋን ሥራ ለመሥራት የዕለት ምግብ ያስፈልጋል:: ሰው የዕለት ምግቡን ካላገኘ የሥጋውንም ፈቃድ ቢሆን ማከናወን አይችልምና:: በመጽሐፈ ሲራክ ላይ እንደምናገኘው «የኑሮህ መጀመሪያ የምትበላው እህል ነው» ይላል:: /ሲራክ ፳፱፥፳፩/ ለመብላት ደግሞ በላብህ በወዝህ ወጥተህ ወርደህ ብላ ተብሎአል:: /ዘፍ.፫፥፲፱/

ሰው የዕለት ምግብ ካጣ ረሀብ ክፉ ነውና ለስደት ይጋብዛል:: ብዙ ሰዎች የዕለት ምግባቸውን ለማግኘት ተሰደዋል:: /ሩት ፩፥፩-፪፣ ዘፍ.፵፫፥፲፩፣ ዘፍ.፳፮፥፩/ የዕለት ምግብ ከጠፋ እናት የወለደችውን ሕፃን ቀቅላ እስከመብላት ትደርሳለች፤ ረሀብ ክፉ ነውና:: /፪ኛ ነገ.፮፥፳፮-፴፣ ሰቆቃ. ኤር.፬፥፲/ አባቶቻችን በረሀብና በችግር ዘመን የሚበላ ጠፍቶ የጫማ ሶል ሳይቀር እንደበሉ ሲተርኩልን ቀልድ ይመስለን ይሆናል:: ሰው የዕለት ምግቡን ካጣ ያንን ለማግኘት እስከ ዘረፋና ነፍስ ግድያ ሊደርስ ይችላል:: እነዚህ ደግሞ ክፉ ሥራዎች ናቸው::

ከተጠቀሱት ክፉ ነገሮች ሁሉ ለመዳን የዕለት ምግባችንን ስጠን ብለን ልንጸልይ ይገባናል:: ሰው በሰውነቱ የዕለት ምግብ ያስፈልገዋል:: ሆኖም ግን የሥራን ክቡርነት ተረድተን ጠንክረን ከመሥራትና በየዕለቱም በፈጣሪያችን ፊት የዕለት ምግብ እንዳይነሳን ከመጸለይ አልፈን መጨነቅ አይገባንም:: /ማቴ.፮፥፴፩/::

እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ መጋቢ ነው:: ድሀውንም ባለጠጋውንም የሚመግብ እግዚአብሔር ነው:: /መዝ.፻፵፮፥፰-፱፣ ፩ኛመቃብ.፴ ፥፲፪/ ያለእርሱ ቸርነት የዘራነው ሊያፈራ፣ የነገድነው ትርፍ ሊያስገኝ፣ የድካማችን ፍሬ ውጤት ሊኖረው አይችልም::

እርሱ በፈጠረልን እጅ ሠርተን እርሱ የባረከልንን ፍሬ ከተመገብን እንረካለን:: /ሰቆቃ.፫፥፮፣ ኢዮብ ፳፰፥፫/ እግዚአብሔር አምላካችንን መንግሥቱንና ጽድቁን ሽተን ከልብ ከተከተልነው የዕለት ምግብ እንዲያስፈልገን ዐውቆ ይሰጠናል:: እርሱንም አምነን ከተከተልነው ስንራብ፣ ስንጠማ ዝም የሚል አምላክ ሳይሆን ትንሹን አብዝቶ፣ ጥቂቱን አበርክቶ የሚሰጥ ነው:: ያስብልናል፤ ያዝንልናልም::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጥብርያዶስ ሲከተሉት የነበሩትን ሕዝቦች ባዶ ዋቸውን አልሸኛቸውም:: ሰባት እንጀራ ሁለት ዓሣ ባርኮና አበርክቶ ሕፃናትና ሴቶቹ ሳይቆጠሩ አራት ሺሕ ሕዝብ ተመግቦ ጠግቦ የተረፈውን ሰባት ቅርጫት አንሥተዋል:: /ማቴ.፲፭፥፴፪-፴፰/ ደቀ መዛሙርቱ ግን ይቺን ጥቂት





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ምግብ ለዛ ሁሉ ሕዝብ መመገብ ፈጽሞ የማይሆን፣ የማይታሰብ እንደሆነ ገምተው በዚህ በበረሀ ይህን ሁሉ ሕዝብ የሚመግብ ምግብ ከወዴት እናገኛለን ብለው ጭንቀታቸውን ለጌታ ገልጸው ነበር። እርሱ ግን ሰው በእምነት በእጁ ያለውን ነገር ካቀረበ በበረከት እንደሚ ትረፈረፍ በተግባር አሳይቷል።

እግዚአብሔር እንዲህ ትንሹን ብዙ አድርጎ በበረከት የሚያትረፈርፍ ሆኖ ሳለ እኛ ግን ብዙ ነገር እያለን በረከት ስናጣ ለምን ይሆን ብለን ራሳችንን ልንመረምር ይገባል። «በረከት ለማግኘት ምንድነው የጎደለኝ?» ማለት አለብን። ዛሬ ዛሬማ ብዙ ነገር ጎድሎናል፤ እምነት ፣መልካም ሥራ፣ ፍቅር ጎድሎናል። ስለዚህ በረከት ርቆናል። ይህ እንዲሆን ደግሞ የበረከት ሥራ እንሥራ ዘንድ አምላካችን ይሻል።

በችግር እና በረሀብ ዘመን ብንመላለስ እንኳ ለእግዚአብሔር ታዛዥ ከሆንን በበረከት እንጠግባለን። የሰራፕታዋን በዚያ በረሀብ ዘመን የምትመገበው በቂ ምግብ በቤትዋ አልነበራትም። ነገር ግን ያላትን ጥቂት ነገር ሳትሸሽግ ለእግዚአብሔር እንግዳ /ለኤልያስ/ ለማቅረብ ፈቃደኛ ሆና ተገኘች። በዚህም ድንቅ ሥራዋ ቤትዋ በበረከት ተሞልቷል። ኤልያስ ሴቲቱን «በእግዚአብሔር እመኚ፤ አትፍሪ፤ ሂደሽም እንዳልሽው አድርጊ፤ … የእስራኤል አምላክ እንዲህ ይላልና በምድር ላይ እግዚአብሔር ዝናብ እስከሚሰጥበት ቀን ድረስ ዱቄቱ ከማድጋው አይጨረስም፤ ዘይቱም ከማሰሮው አይጎድልም» እንዳላት ቤትዋ በእግዚአብሔር በረከት ሞላ። ያንን የረሀብ ዘመን ሳትቸገር አሳልፋለች። ምክንያቱም የእግዚአብሔርን በረከት ለማግኘት ነቢዩ እንዳላት በእምነት ጸንታ ያለጥርጥር ተገኝታለችና። /፩ኛ ነገ.፲፯፥፰-፲፮/

ብዙዎቻችን ከእግዚአብሔር የፈለግነውን ለማግኘት የማንችለው በእምነታችን እየዛልን በልቡናችንም ተጠራጣሪዎች እየሆንን ነው። እንደሰራፕታዋ ሴት ጉድለታችንን ግልጽ አድርገን በመናገር ምሕረት ብንለምን የጎደለንን እግዚአብሔር ይሞላልናል። ማዕዳችን፣ ኑሮዋችን ይባረካል። /ዘፍ. ፳፫፥፳፭/

እግዚአብሔር ጥቂቱን ማበርከት ብቻ ሳይሆን የሌለውንም እንዲኖር አድርጎ መመገብ ይቻለዋል፤ የሚሳነው የለምና።

እግዚአብሔር ኤልያስን በረሀብ ዘመን፣ ዳንኤልንም ደግሞ በአንበሳ ጉድጓድ ቁራዎችንና መላእክትን እያዘዘ እንደመገባቸው ከቅዱሳት መጻሕፍት እንረዳለን። /ተረ.ዳን.፲፫፥፴፫፣ ፩ኛ ነገ.፲፯፥፩-፯/ ኤልያስ ረጅም መንገድ ስለሚሄድ ብርታት እንዲያገኝ እግዚአብሔር ከእንቅልፉ ቀስቅሶ የበረከት ማዕድ መግቦታል። /፩ኛነገ.፲፱፥፭-፯/። የዕለት ምግብ ከረሀብ፣ ከድካም ለይቶ ኃይል ብርታት ይሰጣልና ኤልያስ ከተመገበ በኋላ ኃይል፣ ብርታት አግኝቶ አርባ ቀንና ሌሊት ሙሉ እንደተጓዘ እንረዳለን። በእምነት ጸንተን ከተገኘን እግዚአብሔር ምድራዊ የሆነ የዕለት ምግባችንን የሚገኝበትን ሥራ እንድንሠራ ጤናችንን አሟልቶ እየሰጠ፤ መልካም ነገርን እያመቻቸ፤ በተለያየ መንገድና ጥበብ መግቦቱን ሳያቋርጥ ያስተዳድረናል። ስለዚህ ሁልጊዜ በእምነትና በምግባር ጸንተን የዕለት ምግብ እንዳይነሳን መጸለይ ይገባናል። ይሁንና የዕለት ምግብ ስናገኝ ደግሞ በጾመ ልጓም እየተመራን መኖር አለብን። ስንጠግብም ማመስገን እንጂ መዘፈን፤ መፋቀር እንጂ መጣላት የለብንም። /መዝ.፵፰፥፳/

**ሰው በዚህ ምድር ላይ ሲኖር እንደ መላእክት ያለምግብ፣ እንደ እንስሳትም በምድራዊ ምግብ ብቻ ሊኖር አልተፈጠረም። ሰው ለሥጋ ምግብ ብቻ ከተሸነፈና መንፈሳዊ ምግቡን ከዘነጋ የመንፈስን ፍሬ ሊያፈራ አይችልም። ይህ ደግሞ ለዘላለማዊ ሞት ይዳርገዋል።**

## ፪. የእግዚአብሔር ቃል

ከቅዱስ ቃሉ እንደምንረዳው ሰው በምግበ ሥጋ ብቻ እንዲኖር የተፈጠረ ሳይሆን ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣ ቃልም የሚያስፈልገው ፍጡር ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር «ሰው ከእግዚአብሔር ቃል በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም» ብሏል። /ማቴ.፬፥፬/ ስለዚህ የዕለት ምግባችንን ስጠን ብለን ስንጸልይ ይህንን ሁሉ ማሰብ አለብን። ነፍስን ሕያው የሚያደርጋት የእግዚአብሔር ቃል ነው። የእግዚአብሔር ቃል ከማር ወለላ ይልቅ የሚጥም የሚጣፍጥ ሕይወትን የሚለውጥ ልዩ የነፍስ ምግብ ነው። /መዝ.፻፲፰፥፻፫፣ ሕዝ.፫፥፩-፫/ በየዕለቱ ይህን የጣፈጠ የሕይወት ምግብ ካገኘንና ከተመገብን ሕይወታችንም እንዲሁ የጣፈጠ ይሆናል።

ለሥጋችን የዕለት ምግብ እንደሚያስፈልገን ሁሉ በየዕለቱ ለነፍሳችን የእግዚአብሔር ቃል ያስፈልጋታል። ቃሉን በየዕለቱ የምትመገብ፣ የለመለመች ሕጉን በቀንና በሌሊት የምታስብ ናት። /መዝ.፩፥፪-፬/ የእግዚአብሔር ቃል ሕይወትን ይለውጣል። ቃሉ ክፉ ሥራን ከሰውነት ያርቃል። ሰውነትንም ይቀድሳል። ቃሉን በምንሰማበት ወቅት ምን ያህል መንፈሳዊነት እንደሚሰማን መገመት እንችላለን።

ሰው ከቃለ እግዚአብሔር ከራቀ፤ ነፍሱም ቃለ እግዚአብሔር ከተራበች ሕይወቱ ይመርርና ለኃጢአት የሚገዛ ደካማ ይሆናል። ሰይጣንን ድል የሚያደርግበትንም ኃይል ያጣል፤ የአምላኩን ሕግ ቸል ይላል። ስለዚህ በየዕለቱ የእግዚአብሔር ቃል ያስፈልገናል። በምግበ ሥጋ ብቻ መኖር አንችልምና። በነቢዩ በአሞጽ እግዚአብሔር እንደተናገረው የቅዱስ ቃሉ ረሀብ ከሁሉ የከፋ ነው። «በምድር ላይ ረሀብን የምሰድበት ዘመን ይመጣል» ይላል እግዚአብሔር። እርሱም የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት እንጂ እንጀራን ከመራብና ውኃን ከመጠማት አይደለም» ተብሏልና። /አሞጽ.፰፥፲፩/

ከዚህ ረሀብ ለመዳን መጸለይ፤ የዕለት ምግባችንን ስጠን፣ ቅዱስ ቃልህን በየዕለቱ አሰማን በማለት መማጸን አለብን። ቅዱስ ቃሉን ከእውነተኞቹ መምህራን፣ ከመጻሕፍት፣ ከተለያዩ መንፈሳዊ ምንጮች በመስማት ለመመገብ መትጋት ይኖርብናል። መስማት ብቻ ሳይሆንም በልቡናችን መጠበቅ በሥራ መተርጐም አለብን። /ሕዝ.፫፥፲/ እንደ ነዌ ሲያል ከገባን በኋላ መጸጸቱ አይጠቅምም። /ሉቃ.፲፮፥፲፱-፴፩/



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

## ፫. የክርስቶስ ሥጋና ደም

ጌታ የዕለት ምግባችንን ዛሬ ስጠን ብላችሁ ጸልዩ ሲል ምድራዊውን እንጀራ ብቻ እየተመገብን እንድንኖር ሳይሆን ስለሰማያዊው እንጀራ፣ ስለነፍሳችን ምግብ፣ ስለክርስቶስ ሥጋና ደምም እንድንጸልይ ነው:: ሰማያዊ ሕይወትን ለመውረስ ሰማያዊ እንጀራና ሰማያዊ መጠጥ ያስፈልገናል:: የክርስቶስ ሥጋና ደም የሕይወት እንጀራ ነው:: ጌታችንም ያስተማረን ይህንኑ ነው:: «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም:: በእኔ የሚያምንም ለዘላለም አይጠማም::» ብሎናል:: /ዮሐ.፮÷፴፭/ በምድራዊ ምግብ ምክንያት የመጣውን ፍርድ ክርስቶስ ያስወገደልን የሕይወት ምግብ የሆነውን ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶ፣ ክቡር ደሙን አፍስሶ የዘላለም ምግብና መጠጥ አድርጎ በመስጠት ነው::

የዕለት ምግብ ሲባል ግን ለእኛ የሚታየን ምድራዊ እንጀራ ነው:: ጭንቀታችንም ለእርሱ ነው:: ከሁሉ በላይ ሊያሳስበን የሚገባው ግን ዘላለማዊውና ሰማያዊው ምግብ የሆነው የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው:: /ዮሐ.፮÷፳፯/ ክርስቶስ ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ /የዘላለም ምግብ/ ነው:: /ዮሐ.፮÷፶፩/ ከክርስቶስ ጋር ለመኖር የእርሱን ሥጋ መብላት፣ ደሙንም መጠጣት አለበን:: እንደዛ ከሆነ እኛ በእርሱ እንኖራለን:: እርሱም በእኛ ይኖራል:: /ዮሐ.፮÷፶፮/ «ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው:: እኔም በኋለኛው ቀን አስነሣዋለሁ::» እንዳለ የዘላለምንም ሕይወት ለመውረስ ይህ ሰማያዊ ምግብ ያስፈልገናል:: /ዮሐ.፮÷፶፬/

ስለዚህ የዕለት ምግባችንን ዛሬ ስጠን እያልን በየዕለቱ ስንጸልይ፣ በየዕለቱ የክርስቶስን ሥጋና ደም ለመቀበል እየናፈቅንና እየተዘጋጀን መሆን አለበት:: የእርሱን ሥጋና ደም ለመቀበል በዕድሜና በፆታ፣ በመልክና በቋንቋ፣ በዘርና በጎሳ ልዩነት የለም:: ምድራዊ እንጀራን በውኃ እጃችንን ታጥበን እንደምንመገብ ሰማያዊ እንጀራ የሆነውን የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደምም በንስሐ ውኃ ታጥበን መመገብ ይገባናል:: ዳሩ ግን ሳናምንበት በንስሐም ራሳችንን ሳናዘጋጅ ዝም ብለን በድፍረት ብንቀበለው ዕዳ ፍዳ ይሆንብናልና መጠንቀቅ አለብን:: /፩ቆሮ.፲፩÷፳፯/

ስለዚህ በየዕለቱም ሆነ ዓመት በዓል በመጣ ቁጥር ስለምድራዊው ፍሪዳ ብቻ መጨነቅ የለብንም:: ይልቁንም የዕለት ምግባችንን ስጠን እያልን ስንጸልይ ስለ እኛ ደኅንነት ራሱን በመስቀል ላይ የሠዋውን፣ ፋሲካችን የሆነውን የክርስቶስን ሥጋና ደም ለመመገብ በማሰብ እየተዘጋጀን መሆን አለበት::

ሰው ከቃለ እግዚአብሔር ከራቀ፤ ነፍሱም ቃለ እግዚአብሔር ከተራበች ሕይወቱ ይመርና ስኃጢአት ተገዢና ደካማ ይሆናል፤ ሰይጣንን ድል የሚያደርግበትንም ኃይል ያጣል፤

ምድራዊው ፍሪዳ አቅምና ገንዘብ ይጠይቃል:: የምድራዊው ፋሲካ /ዓመት በዓል/ እንዲህ መድሎ አለው:: ሰውን በሀብት በአቅም ይለያያል:: ይህ ሁሉ ሆኖም አሁን ተመግበውት ትንሽ ቆይቶ ይጠፋል:: ለነፍስ የሚሆን ትርፍም የለውም:: የነፍስ ምግብ የሆነው ሰማያዊው ፍሪዳ የክርስቶስ ሥጋና ደም ግን በእምነት ለተቀበለው ሁሉ ያለዋጋ የሚታደል ዘላለማዊ ምግብ ነው:: ሁሉን እኩል ያደርጋል::

ለሚያልፈው ለሚጠፋው ምግብ ብቻ መሮጥ የለብንም፤ የዘላለም ሕይወት ለሚያስጠንም ምግብ እንጂ:: /ዮሐ.፮÷፳፯/:: ስለዚህ በየዓመት በዓሉ የሥጋ ገበያ ስናጣብብ፤ ስለዶሮ፣ ስለበግ፣ ስለሰንጋ በአጠቃላይ ስለምድራዊ ምግብ ዋጋ ብቻ ስንጨነቅ መኖር የለብንም:: ስለሰማያዊው ምግብ ልናስብ ልንጨነቅ ልንዘጋጅም ይገባናል:: ለምድራዊ ሕይወታችንም ቢሆን በረከት የሚኖረን ሰማያዊውን ምግብ ስንይዝ ነው::

ሰው በዚህ ምድር ላይ ሲኖር እንደ መላእክት ያለ ምግብ፣ እንደ እንስሳትም በምድራዊ ምግብ ብቻ ሊኖር አልተፈጠረም:: ሰው ለሥጋ ምግብ ብቻ ከተሸነፈና መንፈሳዊ ምግቡን ከዘነጋ የመንፈስን ፍሬ ሊያፈራ አይችልም:: ይህ ደግሞ ለዘላለማዊ ሞት ይዳርገዋል:: /ገላ.፭÷፲፱-፳፩/

እንግዲህ «የዕለት ምግባችንን ስጠን» እያልን ስንጸልይ ኖረናል:: አሁንም እየጸለይን ነው:: ግን ስንቶቻችን ነን ከሥጋ ምግብ መጨነቅ አልፈን ለነፍስ ምግብ የምናስበው? ለሥጋ ወደሙስ ስንቶቻችን በቅተናል? ዓመት በዓል ሲመጣ ለሥጋ ምግብ ከመባከን አልፈን ንስሐ ገብቼ ልቁረብ፣ ከቤተ ክርስቲያን ሔጄ ቃሉን ልማር የምንል? እስኪ አሮጌው ሰውነት ከአሮጌው ዘመን ጋር ይለፍና በአዲሱ ዘመን በምግበ ሥጋወነፍስ የተሟላ አዲስ ሕይወት ይኑረን:: በጾም በጸሎት ተወስነን «ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ» /ሮሜ.፲፪÷/ እንደተባለው ወጥተን ወርደን በላባችንና በወዛችን ብቻ የዕለት ምግባችንን እንመገብ:: በእግዚአብሔር ቃል እየታነጽን፣ ራሳችንን በንስሐ መርምረን፣ ሥጋወደሙን በመቀበል ለዘለዓለም መኖሪያችን ለመንግሥተ ሰማያት እንድንበቃ እግዚአብሔር ይርዳን፡ ወላዲተ አምላክ በምልጃዋ አትለየን::✣

*ስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር::*



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# ሰውም ጊዜውን አያውቅም

መክ.፱÷፲፪

## ሦስተኛውን ሺሕ ምን እንሥራበት?

*ዲ/ን ማለደ ዋሲይሁን*

ጊዜ ስለፍጡራን የሕልውና ዘመን /ቆይታ/ ስናስብ የምንናገርበት ትልቁ መለኪያ ነው:: ፍጡር የተፈጠረበት /የተገኘበት/ የመጀመሪያ እንዳለው ሁሉ ፈጣሪው የሚያውቀው መጨረሻ /ፍጻሜም/ አለው:: ሰው ይህን የእርሱንና የሌሎች ፍጡራንን የቆይታ ጊዜ ከ-እስከ ብሎ ይሰፍረዋል:: ለዚህም ከሰከንድ ድቃቂ /Micro second/ እስከ ሺሕ ዓመት /Millinia/ ድረስ ጥቅም ላይ ይውላል:: ፈጣሪም ለፍጡራኑ ይህን መስፈሪያ በራሳቸው በፍጡራኑ ባሕርይ እንዲወስን ማድረጉን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል:: «እግዚአብሔር ብርሃንና ጨለማን ለየ፤ እግዚአብሔርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው፥ ጨለማውንም ሌሊት አለው:: ... እግዚአብሔር አለ፡- ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ፥ ለምልክቶች ለዘመኖች ለዕለታት ለዓመታትም ይሁኑ:: ... እግዚአብሔርም መልካም እንደሆነ አየ::» /ዘፍ.፩÷፬-፲፬/ እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን የፍጡራን የፈረቃ ሥርዓት በፍጡራን ፊት አሠለጠነ::

በእግዚአብሔር ፊት ግን ጨለማ የለም:: እርሱ በባሕርዩ ብርሃን ነውና የተፈጠረ ብርሃንን አይጠቀምም:: በፊቱም የቀንና ሌሊት ፈረቃ ቦታ የለውም:: ዕድሜንም አይቆጥርለትም::

ሰው ግን እግዚአብሔር በፍጡራኑ አማካኝነት እንዲገለጽ ባደረገው የጊዜ ፈረቃ ሥርዓት መሠረት ትላንትና ዛሬን መረዳት፣ ነገን ተስፋ ማድረግንም ዐወቀ:: በዚህ በተፈጠረበትም ምድር ላይ የሚኖርበት ዘመን የተወሰነ መሆኑን ከበደል በኋላ ተረዳ:: «አዳም ሆይ አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ» እንደተባለ:: /ዘፍ.፫÷፲፱/ ስለዚህም በተሰፈረችለት ዘመኑ ክፉና ደጉን በነጻ ፈቃዱ ተጠቅሞ እየሠራ ያልፋል /የምድር ላይ ቆይታውን ይፈጽማል/::

የሰዎች ዕድሜ በየዘመኑ በነበሩ ሁኔታዎች ይለያይ ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስ በኖኅ ዘመን ከነበረው ጥፋት በፊት የሰው ልጆች ዕድሜ ረጅም እንደ ነበረ ይነግረናል:: ከዚያ በኋላ አብርሃም መቶ ሰባ አምስት ዓመት ሲኖር ይስሐቅ ደግሞ መቶ ሰማንያ ዓመት ኖሮ ነበር:: ያዕቆብ የኖረበት ዘመን መቶ አርባ ሰባት ዓመት ሲሆን በግብጽ ሳለ ፻፴ ዓመቱ ነበር:: «የእንግድነቴ ዘመን መቶ ሠላሳ ዓመት ነው:: የሕይወቴ ዘመኖች ጥቂትም ክፉም ሆኑብኝ:: አባቶቼ በእንግድነት የተቀመጡበትንም ዘመን አያህሉም» /ዘፍ.፵፯÷፱/ ንጉሡ ክቡር ዳዊት ደግሞ «ዘመናችንም በምድር ላይ እንደ ጥላ ናት» ብሏል:: /፩ዜና.፳፱÷፲፭/ እንዲሁም «ዕድሜያችን ሰባ ነው ቢበዛ ሰማንያ ነው» በማለት የሰዎች ዕድሜ በዚህ ደረጃ መቀነሱን ያሳየናል:: /መዝ.፹፱÷፲/ ይህ የዕድሜ ጣሪያ ዛሬ ዛሬ ደግሞ በብዙ ሀገሮች ቀንሶ ይታያል::

ዋናው ቁም ነገር ግን እያደር እየቀነሰ በመጣው የዕድሜ ጣሪያ ውስጥ የሰው ልጅ በምድር ላይ እንዴት ይኖራል? ምንስ ይከውናል? የሚለው ነው::

በእርግጥ ሰው ወደ ሌላ ዓለም የሚሻገርበት ሞት በፊቱ እንዳለ ያውቃል:: መቼ እንደሚጠራ ባያውቅም ከአባቶቹ በላይ እንደማይኖር ግን ይገነዘባል::

ለክርስቲያኖች ሞት አስፈሪ ሳይሆን ሽግግር ነው:: ለእነርሱ ታላቁ ጭንቀት የወዲያኛው ዓለም የእውነትና የዕውቀት ዓለም በመሆኑ ከዚያ መገለጥ በፊት በምድር ላይ ስለሚሠሩት በጎ ሥራ ነው:: ሥራቸው ይከተላቸዋልና:: ሰዎች የተወሰነ ዘመን እንደሚኖሩ፣ በወተሰነው ዘመን የሚሠሩት ሥራም በወዲያኛው ዓለም እንደሚከተላቸው በተወሰነው ዘመን የሚሠሩት በምድር ላይ በቀሩት ወገኖቻቸው ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽዕኖ እንዳለው ከተረዱ ታላቁ ጭንቀታቸው የሚሆነው በተመጠነች ዘመናቸው በምድር ላይ የሚያከናውኑት ተግባር ነው::

በጥምቀት የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ በዓለም ያሉ በክፋት የሠለጠኑ ሰዎች እንኳ ዘመናቸው የተወሰነ መሆኑን፥ ሁኔታዎችም ያሰቡትን እንዳይፈጽሙ ሊያግዷቸው እንደሚችሉ በመገመት ክፉ ሥራቸውን ባሰቡት ጊዜ ለመፈጸም ይዝታሉ:: እንዲህ በማለት «ኑ ለእኛ ከተማና ራሱ ወደሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ በምድር ላይ ሳንበተንም ስማችንን እናስጠራው» እያሉ:: /ዘፍ.፲፩÷፬/ ስለ ሰይጣን ትልምም ጌታ እንዲህ ብሎናል፡- «ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው ዐውቆ በታላቅ ቁጣ ወደእናንተ ወርዷልና::» /ራእ.፲፪÷፲፪/ ክፉዎች ለሐሳባቸው በጊዜው መፈጸም ትልም ሲያወጡ ክርስቲያኖችስ ለበጎ ሥራ እንዴት ማሰብ አለባቸው?

ክርስቲያኖች ስለ ነገ እንዳይመኩ እንጂ እንዳያቅዱ አልተከለከሉም:: ቅዱስ ያዕቆብ «አሁንም ዛሬ ወይም ነገ ወደ ዚህ ከተማ እንሔዳለን፤ በዚያም ዓመት እንኖራለን፤ እንነግድማለን፤ እና ተርፍማለን የምትሉ እናንተ ተመልከቱ፤ ነገ የሚሆነውን አታውቁምና:: ሕይወታችሁ ምንድር ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁና:: በዚህ ፋንታ ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያንን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል» ማለቱ ይህንኑ ለማስገንዘብ ነበር:: /ያዕ.፬÷፲፫-፲፭/ ማቀድን፣ ስለነገ አስበን መሥራትን ካልተከለከልን ደግሞ ዘመናችን ጥቂት መሆኗን ዐውቀን ሳንታክት መሥራት ከክርስቲያኖች ይጠበቃል::

በተለይ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ላለን የክርስቲያን ወገኖች በሦስተኛው ሺሕ ንጋት ላይ ሆነን ማለትም በአዲሱ ዓመት፣ በአዲሱ ምዕተ ዓመት፣ በአዲሱም ሺሕ ዓመት መግቢያ ላይ ሆነን ስለጊዜ፣ ስለዕድሜያችን፣ በዕድሜያችንም የሚገባውን ነገር ስለማከናወን ለማሰብ ታላቅ አጋጣሚ /ዕድል/ ነው:: ይህ የአዲሱ ሺሕ ዓመት መግቢያ ተመጥና በተሰጠችን ዕድሜ ውስጥ መልካሙን ሠርተን እንድናልፍ፣ በእግዚአብሔር የታዘዝነውን ለመፈጸም አስበን እንድንፈጥን ራሱን የቻለ ደወል ነው::

ለአንዳንዶች በዕድሜያችን ውስጥ ማድረግ የሚገባንን ያደረግን፣ አሁንም እያደረግን ያለን፣ ቀሪውን የዕድሜያችንን ክፍልም ልናደርግ ያሰብነውን ለመፈጸም በቂ ዝግጅት ያደረግን እንኖራለን:: በአንፃሩ ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት የሚታይ መልካም ነገር ወይም በሰዎች ፊት የሚታይ ተጨባጭ የሆነ ደግ ወይም ክፉ የሚባል ሥራ እንኳን ሳይኖረን እስከዛሬ ያለውን ዕድሜያችንን ለብ ባለ ሕይወት ያሳለፍን፤ ዛሬም በዚህ መንገድ የምንመላለስ፤ ለነገም ሐሳብ የሌለን እንኖራለን::

የሕይወት ፍልስፍናዎቻችን ቀና ሆነውልን፤ ለልባችን ዕረፍት አግኝተን፤ ሲመሽ ሲነጋ ሳንደነግጥ፤ ሳንቆጭ፤ ያሰብነውን ፈጽመን «ጌታ ሆይ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ ...» /ሉቃ.፪÷፳፱/ ለማለት የተዘጋጀነውን የጀመርነውን ያስፈጽመን ከማለት በላይ ምክር ላያስፈልገን ይችላል:: ነገር ግን ቀን አልፎ ቀን ሲመጣ፤ ወር አልፎ ወር ሲተካ፤ ዓመትም አልፎ ዓመት ሲቆጠር በጽናት ተገኝተን ላለንና ለራስ፣ ለባልንጀራና ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝን ተግባር ለመፈጸም በምክንያተኝነትና በስንፍና ለምንመለስ ከተኛንበት እንድንነቃ የሦስተኛው ሺሕ የመጀመሪያዎቹ ደቂቃዎች፣ ሰዓታት፣ ቀናትና ወራት



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ደወል ሊሆኑልን ይገባል፡፡ ለዚህ ካልታደልን ግን እንዳናስተውል የተበተ በንን አዚም ማን እንዳደረገብን መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ በሁለቱ መሠረታዊ የሕይወት ጉዳዮቻችን ማድረግ ያለብንን ለምን አላደረግንም?

## ፩ኛ/ ለሥጋዊ ሕይወታችን

በተሰጠን የጊዜ ጸጋ ተምረን የማናልፈው፣ አልፈን የማንሠራው፣ ሠርተን የማናተርፈው፣ አትርፈን የማንጠቀመው፣ ተጠቅመንም የማናመሰግነው ለምንድነው?

ስንማርም በትጋት፣ ስናልፍም በመዓርግ፣ ስንሠራም ባለን ኃይል ሁሉ፣ ስናተርፍም ትርፋን መጉተት ወይም መሸከም እስኪያቅተን፣ ስንጠቀምም በአግባቡ፣ ስናመሰግንም ከልብ የማይሆነው ለምንድነው? ከምንም በላይ ደግሞ የጥያቄዎቻችን ራስ የሚሆነው ባለችን አጭር ዕድሜ ውስጥ እነዚህን ነገሮች በጊዜያቸው ሳንፈጽም የምንቀረው ሳንረካም በሰቀቀን የምንሞተው ለምንድነው? የሚለው ነው፡፡

ነገሮች ሁሉ ከላይ ባልናቸው ተገቢ መንገዶች ቢፈጸሙ ምናልባትም ጊዜያችንን በአግባቡ መጠቀም ያቀድነውንም በጊዜው መፈጸም ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ለራሳችን ሥጋዊ ሕይወት የምንበላው፣ የምንለብሰው፣ የምንኖርበት፣ የምንከብርበት፣ የምንደሰትበት ዕድል ሰፊ ይሆናል፡፡ ከዚህ አልፈን ደግሞ ለሰበሰብነው ቤተሰብ ለወለድናቸው ልጆች ተርፈን ያለሰቀቀን እንዲኖሩ፤ ፍላጐታቸው በጊዜው እንዲሟላ፤ እነርሱም ጊዜያቸውን /ዕድሜያቸውን/ በጊዜው እንዲጠቀሙ ለማስቻል አቅም እናገኛለን፡፡ በዚህ መንገድ ብዙዎቻችን መመላለስ ከቻልን ድምር ውጤቱ የበለጸገች፣ የተከበረች፣ ምሳሌ የምትሆን አገርን ማግኘት ነው፡፡ ራስንና ቤተሰብን በጊዜ /በዕድሜ/ መጠቀምን ማለማመድ ከተቻለ በሀገር ደረጃም ትወልድ በጊዜው አስደሳች ታሪክን ሠርቶ፤ ዘመኑን ወርቃማ /Golden Age/ አሰኝቶ፤ በተፈጥሮ የተቀ በለውን የቤት ሥራ ፈጽሞ ያልፋል፡፡ ለቀ ጣይም ትውልድ ዘላቂ በሆነ መልክ የሚወጣበትን ደረጃ አንጸለት ያልፋል፡፡ እርሱም በዚያ ደረጃ ላይ ተግባሩን ከፍ ከፍ አድርጐ ይገነባል፡፡ ቀጣዩም በዚያ ላይ ይደርባል፡፡ ዕድገትና ብልጽግናም ይመጣል፡፡

ካልሆነ ግን ትውልዱ ያለፈበትን ጊዜ የጨለማ ዘመን /Dark Age/ አሰኝቶ፤ የራሱን የቤት ሥራ ሳይጨርስ ለቀጣይ ትውልድ /ለልጆቹ/ ዕዳ የሚያቆይ ከንቱ ትውልድ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በሥጋዊ ሕይወት ያለ ስኬታችንም ከመልካም ኑቶቻችን ጋር ጊዜያችንን በአግባቡ ከመጠቀም የሚመነጭ /የሚገኝ/ ነው፡፡

## ፪ኛ/ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን

የክርስትና ሃይማኖታችን ገና በሕፃንነት ወራታችን በመንፈሳዊ ልደት /በጥምቀት/ ይቀበለናል፡፡ በሜሮን ያትመናል፡፡ በቁርባን የነፍስ ኃይልና ሕይወትን ይሰጠናል፡፡ በቃለ እግዚአብሔርም አሳድጐ የታደልን ስንሆን በክህነት መንፈሳዊ አገልጋይ ያደርገናል፡፡ በሥርዓተ ተክሊል ቀጣዩን መንፈሳዊ ትውልድ የሚቀላቀል ዘር የሚሰጥ ሕጋዊነት /ጋብቻን/ ያጸናልናል፡፡ በንስሐና በቀንዲል የበለጠ ኃይልና ከሥጋና ከነፍስ ደዌ መዳንን ይሰጠናል፡፡ ገደብ በሌለው የእግዚአብሔር ብዙ ጸጋ ውስጥ ተመላልሰን፣ መንፈሳዊ ጠላት ከሆነው ከዲያብሎስ ጋር ተዋግተን ባለድል በመሆን፤ ሽልማት /አክሊል/ የሆነች መንግሥተ ሰማያትን እናገኛለን፡፡ ይህ ሁሉ ግን የሚሆነው ሁሉ በጊዜው /አስፈላጊ በሆነበት ወቅት/ ሲፈጸም ነው፡፡

በእርግጥ በዚህ ዘመን ለሚታይ፣ ለሚሰማ፣ ለሚዳሰስ፣ ለሚቀመስ፣ ለሚሸተት ሥጋዊ ኑሮአችን እንኳን ጊዜያችንን መጠቀም ካልቻልን በእምነት ለሚኖርበት ስውር /ረቂቅ/ ዓለም አቅም ማግኘት እንዴት ይቻላል? በር ግጥም ጊዜውን ለመጠቀም ለሚፈልግ እምነት መንፈሳዊ ሰው ጉልበት ነው፡፡ የማያምን ሰው በሚሠራቸው መንፈሳዊ ሥራዎች በሕሊናውም በሚመላለሱ መንፈሳዊ ሐሳቦች ሁሉ የሚጸጸት ይሆናል፡፡ ጊዜውንም ያባክነ፣ በከንቱም የሚደክም እንደሆነ ያስባል፡፡ ለምናምን ሰዎች ግን ዓለምና ሰይጣን ከሚፈጥሩብን ድንዛዜና መዘናጋት ራሳችንን ጠብቀን፣ ከወደቅንም ፈጥነን ተነሥተን እግዚአብሔርንና ባልንጀራን ደስ ወደሚያሰኙ የነፍስ ፈቃዳት ማተኮር አስፈላጊ ነው፡፡

ለክርስቲያኖች ከሥጋችን ኑሮ ይልቅ የነፍሳችን ጉዳይ የበለጠ አሳሳቢ ነው፡፡ ይኸኛው ዓለም እጅግ የተመጠነ ዘመንና በሞትም የምንለየው ነው፡፡ ይህንንም ያለ ነጋሪ ያለምስክር ሰው የሆነ ሁሉ ይረዳዋል፡፡ ድካማችን በዚህ ዓለም እስካለን ድረስ ብቻ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ግን በምድር የሠራችው ተከትሏት ዕጣ ፈንታዋን የሚወስንላት ነፍስ የጊዜው ወሰን ለማይታወቅ ዘመን በደስታ ወይም በስቃይ መኖሯን ትቀጥላለች፡፡ ስለዚህ ለሚያምኑ ፀሐይ ዕድሜያቸው ጠልቃ ነፍስና ሥጋ ሳይለያዩ፣ ባለቻቸው ጊዜ ሳይሰለቹ መንፈሳዊ ሥራን ማከናወን ግዴታቸው ነው፡፡ አምነዋልና በምድር ቢኖሩም ቢያልፉም የጌታ ናቸውና ሁሉንም ቀን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራን በመሥራት ያለ ቀጠሮ ይኖራሉ፡፡ /ሮሜ ፲፬÷፰/ በምድር የሚኖሩበት ጊዜ ጥቂት በመሆኑና ከወዲያኛው ዓለም ዘላለማዊነት ጋር ሲነጻጸር ከንቱ መሆኑን ስለሚረዱ መልካሙን ለማድረግ ይተጋሉ፤ ከመልካሞችም ጋር ይኖራሉ፤ ክፉዎችንም ያስተምራሉ፤ ያርማሉ፤ ወደ እውነትም ይጠራሉ እንጂ. ነገ እንሞታለንና እንብላና እንጠጣ አይሉም፡፡ የማይታየውን ነገር ግን እውነት የሆነውን ይናፍቃሉና «ጊዜያችንን ለመንፈሳዊ ሥራ አናውልም» አይሉም፡፡ /፩ቆሮ. ፲፭÷፴፫/ በሚኖሩት መንፈሳዊ ሕይወት ምክንያት ስለጐደለባቸው፣ ስላጡት ወይም ስለተቀበሉት መከራ አይጸጸቱም፡፡ «... አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል፡፡ እርሱንም ሳታዩት ትወዱታላችሁ፡፡ አሁንም ምንም ባታዩት በእርሱ አም ናችሁ የእምነታችሁን ፍጻሜ እርሱም የነፍሳችሁን ማዳን እየተቀበላችሁ በማይነገርና ክብር በሞላበት ሐሴት ደስ

> **ይህ የአዲሱ ሺሕ ዓመት መግቢያ ተመጥና በተሰጠ ችን ዕድሜ ውስጥ መልካሙን ሠርተን እንድናልፍ፣ በእግዚአብሔር የታዘዝነውን ለመፈጸም አስበን እንድንፈጥን ራሱን የቻለ ደወል ነው፡፡**



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ይላችኋል» በማለት የተናገሩትን ያመኑ ሐዋርያትን ትምህርት ያምናሉና:: /፩ጴጥ.፩÷፱/

ስለዚህ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚገባውን፣ ያቀድነውንም በጊዜው መፈጸም ይገባል:: ይህንንም ከፈጣሪያችን እና ከተፈጥሮ ልንማር እንችላለን:: እግዚአብሔር ለሰዎች ያሰበውን ሁሉ በነቢያት አናግሮ ቸኩሎ ከጊዜው በፊት፣ ዘግይቶ ከጊዜው በኋላ ሳያደርግ በጊዜው /በቀጠሮው/ ፈጽሟል፤ ይፈጽማልም:: በቅዱሳት መጻሕፍትም «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ...» የሚሉት ቃላት አምላካችን ፈቃዱን የሚፈጽምበት የራሱ ጊዜ እንዳለው ያስረዱናል:: /ገላ.፬÷፬/ በተፈጥሮም ዕፅዋት ተዘርተው የሚበቅሉበት፤ በቅለውም በሚያረካ መልኩ ፍሬያማ የሚሆኑበት ተስማሚ ጊዜ፣ ተስማሚ አየር፣ ይፈልጋሉ:: ያንን ባገኙ ጊዜም የሚሆኑትን ይሆናሉ:: ለሰውም ለእንስሳትም ደስታን ይሰጣሉ:: መጽሐፍም ደግሞ «ለሁሉ ዘመን አለው፤ ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው፤ ለመወለድ ጊዜ አለው፤ ለመሞትም ጊዜ አለው፤ ለመትከል ጊዜ አለው፤ የተተከለውንም ለመንቀል ጊዜ አለው፤ ...» ይለናል:: /መክ.፫÷፩/

ስለዚህ ክርስቲያኖች የምንሆነውን መሆን ባለብን ሰዓት እንድንሆን፣ ያሰብነውንም ልንፈጽም ባሰብንበት ጊዜ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንድንፈጽመው የሚገባ ነው:: ቀጠሮ የማይሰጥባቸው የጽድቅ ሥራዎች በሁሉም ጊዜያት የተወደዱ እንደሆኑና መቼ እንደምንቆምበት በማናውቀው የእግዚአብሔር የፍርድ ችሎት ፊት የሚያድኑን በመሆናቸው ዘወትር ሊሠሩ የሚገቡ ናቸው:: «እነሆ የተወደደ ሰዓት አሁን ነው እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው::» እንደተባለ:: /፪ቆሮ.፮÷፪/

የሚገባውን ከማድረግ አልፈን በብዙ ትሩፋት ለመመላለስም ለጊዜው በሚስማማ ትጋት ውስጥ መገኘት ያስፈልጋል:: ማድረግ እየፈለግን ጊዜው በማለፉ ሳንፈጽማቸው የሚቀሩ መልካም ሥራዎች አሉ:: በሕፃንነት ወራታችን ወይም በወጣትነት ወራታችን ማድረግ የሚገባንን ሳናደርግ በሽምግልና ወራት ውስጥ ሆነን ብናደርጋቸው ደስ የሚያሰኙን ነገሮች አሉ:: ነገር ግን ጊዜው በማለፉ በቁጭትና በጸጸት እንመላለሳለን:: በሽምግልናችን ምክንያት ወገባችን ጸንቶ ለመስገድ፤ እግሮቻችን በርትተው ሮጠን በዱር በገደል ያሉ ገዳማትና አድባራትን ለመሳለም፤ ወገባችን ለዘበረጅም ጊዜ ቆሞ ለማስቀደስ፤ ዓይኖቻችን በርትተው ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማንበብ፤ በሌትና ቀን እንደፈለጉ ለመመላለስ፤ ጆሮቻችን ነቅተው ቃለ እግዚአብሔርን ለመስማት ... ወዘተ የማንችልበት ዕድል ሰፊ ነው:: እነዚህን ትሩፋቶች ገንዘብ ለማድረግ ጊዜውን መጠቀም ያስፈልጋል:: መጽሐፍም «የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፤ ደስ አያሰኙም የምትላቸው ዓመታት ሳይደርሱ ...» ይለናል:: /መክ.፲፪÷፩-፪/

## የሚገባውን ከማድረግ አልፈን በብዙ ትሩፋት ለመመላለስም ለጊዜው በሚስማማ ትጋት ውስጥ መገኘት ያስፈልጋል:: ማድረግ እየፈለግን ጊዜው በማ ለፉ ሳንፈጽማቸው የሚቀሩ መልካም ሥራዎች አሉና::

ጊዜውን በመጠቀም ለራሱ ነፍስ መድኃኒት የሆነ ሰው ለሚመራው ቤተ ሰብና ለወለዳቸው ልጆች መድኃኒት የመሆንም አቅም ይኖረዋል:: የትዳር ጓደኛን በተገቢው መንገድ ላይ ወደፊት እንድትሄድ /እንዲሄድ/ የሚያስችል መንፈሳዊ ብርታት ይኖረዋል /ይኖራታል/:: ከተማረው በማካፈል፤ በተጋድሎ በመርዳት፤ ትሩፋት መሥራትን በማለማመድ የእግዚአብሔር ወደ ሆነው ፍጹም /እውነተኛ/ ዕውቀት ያደርሳታል /ታደርሰዋለች/:: የዓለምን ፈተና ምንነትና ትርጉም ይረዳሉ:: በዚህ ጊዜ ለሚሆንላቸው መልካም ነገር ማመስገንን፣ የሚሆንባቸውን ክፉ ነገር ወደ ጸጋ የሚያሸጋግር መሆኑንና /ለበጎ የመጣ ነው ብሎ በእውነት ማመንን/ መታገሡንም መማር ይቻላል:: የወለዳቸውን ልጆችም የእርሱን ውድቀት ሳይደግሙ፤ የእርሱን ስኬት ተጋርተው የበለጠ ጸጋ እንዲያገኙ ተንከባክቦ ማሳደግን ያውቅበታል::

ከዚያም አልፎ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና በተለያዩ መንፈሳዊ ማኅበራት ውስጥ ጊዜን በአግባቡ ተጠቅሞ ሐሳባዊ ሳይሆን ተግባራዊ ለውጥን ለማምጣት ይጥራል:: እቅዱን መሥራትን ብቻ ሳይሆን አትርፎ መሥራት ንም ያሳያል:: ከአቅሙ በላይ ሳያቅድ በጊዜው የእርሱን ድርሻ እንደችሎታው አስቦ ይፈጽማል እንጂ. አሥር አባርሮ፣ አንዱን ሳይዝ በመቅረት መጸጸትን አይፈልግም፤ ጊዜው ላይመለስ ያልፋልና:: ጸጸቱ እንዳይከፋ የእርሱ ትውልድ ድርሻ ምን እንደሆነ ለይቶ ከባልንጀሮቹ ጋር የድርሻውን ይወጣል:: ቀሪውን ለቀጣዩ ትውልድ በአደራ ያወርሳል:: በዚህም ለውጥን ብቻ ሳይሆን ማየት ያለበትን ለውጥ በዕድሜው እንዲያይ ለፈጣን ለውጥ ይሠራል::

ጊዜውን በአግባቡ እንዲጠቀም፣ የአጋንንትን አሠራር፣ የዓለማውያንንና የአጽራሬ ቤተ ክርስቲያንን እርምጃዎች መርምሮ /ዘመኑን ዋጅቶ/ ሥራዎቹን ይቀምማል:: ፈጣን ለውጥን ማየት ሽቷልና ሥራን ሳያግበሰብስ ማካፈልን ያውቅበታል:: ብዙ ሥራ አግበስብሶ አንዱን ሳይፈጽም ትውልዱን እንዳያሳዝን ብዙውን ሥራ በብዙዎች ፈጽሞ የተመኘውን በእርግጥም ያያል:: የሁሉ ሥራ የማይጥመው ራስ ወዳድ ከመሆን ነጽቶ ያሰበው በጊዜው እንዲፈጸም ሌሎችን ያለማም ዳል እንጂ እኔ ካልሠራሁት ይበላሻል ብሎ ሁሌ አያስብም:: ሥራ ሁሉ በፍጥነት እንዲፈጸም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሥራውን ለሚችሉ ዕድል ይሰጣል እንጂ አልሸነፍም በሚል እልከኝነት ትውልድን አይበድልም:: በዚህ ፈጣን እርምጃው የአጋንንትን ሴራ ፈጥኖ ያከሽፋል:: የቤተ ክርስቲያን ዓላማም በዚያው መጠን ይሳካል:: መፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞን «ሰውም ጊዜውን አያውቅም» የሚለን ስለዚህ ነው:: /መክ.፱÷፲፪/ ታዲያ በጊዜያችን ምን እንሥራ?... እንል ይሆናል:: በርግጥም ይህ ጥያቄ ከአማኞች የሚጠበቅ ስለሆነ ይህንኑ በተመለከተ በሦስት ክፍለን እንደሚከተለው እንመልከታለን::

### ስለዚህ ምን እናድርግ

*ለወጣቶች፡-* ዕድሜያችን የነገ ሀገር ተረካቢነታችንን በግልጽ ይነግረናል:: ልጅነትን ተሻግረን ወደ ዕውቀት እየቀረብን ነው:: ጭላንጭሎች አይተናል:: ችኩልነት ቢፈትነንም በፍጥነት ነገርን የመጸፈም ዕድል አለን:: ታናሽነታችንን ማንም ሳይንቀው ሥጋ ለባሾች መሆናችንን ሳንረሳ፣ የጐደለንን እየሞላን የተቻለንን ሥራ መሥራት መጀመር አለብን:: እርሱም የራሳችን፣ የቤተሰባችን የቤተክርስቲያናችንና የሀገራችን ሓላፊነት ነው:: ወጣቶች ጊዜያችንን በአግባቡ መጠቀም ያለብን ለቀጣይ ትውልድ አይደለም:: እንደ አምላክ ፈቃድ እየተመላለስንባት ያለችው የዚህች ዓለም ረጅም ጊዜ ነዋሪዎች ስለሆንን ነው:: የዚህች አንድ ዓለም ጤናማነት የእኛ የረጅም ጊዜ ጤናማነት ነው:: ሁከቷም የእኛ የረጅም ዘመን ስቃይ ነው:: ከአባቶቻችን ይልቅ ለሀገራችንና ለቤተክርስቲያናችን በመጓጓት ፈጥነን ለመልካም ለውጥ መሥራት ያለብን እኛ ነን:: ነገም በሓላፊነት፣ ከነገ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ወዲያም በተጧሪነት ክፉውንም ደጉንም ለመቀበል በተፈጥሮ ታጭተናልና። ስለዚህ ወጣቶች በጥንቃቄ፣ በፍጥነትና በትጋት ቢያንስ ለራሳችን በማሰብ ዛሬ ውኑ መሥራት መጀመር አለብን።

ታሪክ የመሥራት በቂ ጊዜ፣ ጉልበትና ሰፊ ዕድል ያለን እኛ ነን። ወጣትነታችን ብዙ ዘመን እንዳለን አስበን እንድንዘናጋ ሳይሆን ያሉንን የዕድሜና የጉልበት ምቹ ሁኔታ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ተጠቅመን ሰውና ፈጣሪን የሚያስደስት ለውጥ የምናስመዘግብበት ሊሆን ይገባል። በዕድሜ የሚበልጡንን በድክመቶቻቸው ሳንንቅ፣ ካሳለፉት አስደሳችና አስከፊ ልምድ ተምረን ስኬትን በአጭር ጊዜ ለማግኘት መጸለይና መሥራት አለብን። ችግሮችን መቻል ሳይሆን አጥንቶ፣ መሠዋዕትነትን ከፍሎ በፍጥነት መፍታትን መርሕ ማድረግም ይገባል። ክርስቲያን ወጣቶች ሁሉ ነገር በእግዚአብሔር እንደሚቻል ያምናሉና እንደ ጎልያድ ከፍ ከፍ ባሉብንና በሚገጥሙን ጠላቶቻችን /አጋንንትና የአጋንንት አሠራሮች/ ላይ ጠጠር መወርወርን ከእግዚአብሔር ትሑታን መማር ያስፈልጋል። ጠላቶቻችን በወጣትነታችን ከጣልን በጉልምስናችንና በሽምግልናችን በዙፋን ከብረን በጠላቶቻችን ፊት እንታያለንና።

*ለጐልማሶች፡-* ዛሬ በርግጥም ሀገርና ቤተክርስቲያን በእጃችን ናቸው። የራስና የቤተሰቦቻችን ሕይወት በእጃችን ነው። የሚታመንብን፣ ድርሻችንን የያዝን፣ ሀብትና ዕውቀትን ገንዘብ ያደረግን ነን። የዛሬው ዓለም የዕለት ከዕለት ሁኔታ የሐሳቦቻችንና የሥራዎቻችን ነጸብራቅ ነው። ክፉ የሆነውን የጐልማሳነት ምኞት የምንይዝ የምንጨብጠውን የሚያሳጣን ጊዜ ቢኖርም አሁን ዕውቀት አለን። ቢያንስ ከወጣትነት ዕድሜያችን ወደዚህ በሳልነት ስንሻገር የፈተኑን ውጣ ውረዶች በርግጥም ዕውቀት /ልምድ/ ናቸው። ምናልባትም ብዙ ስሕተቶች ሠርተናል። እነዚያን ለማረም እየጣርን ወይም ደግሞ ባመጡት ቀውስ እየተናጥን ነው። ምናልባትም ሥጋዊ ሕይወታችን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የተመቸ ሆኖልን ይሆናል። ወይም ደግሞ በወጣትነታችን ባልሠራነው የቤት ሥራ ምክንያት የጐደለንን ለመሙላት ሁሉን ትተን ፍትወታችንን እየተከተልን ይሆናል።

ዞሮ ዞሮ አሁንም በድጋሚ አንድ ታላቅ ነገር እናስብ፤ አሁንም በፍጥነት ማቀድን፤ ካቀድን ደግሞ መፈጸምን። ለምን?

በመጀመሪያ ደረጃ አሁን ልጆቻችን መጠየቅ ጀምረዋል። እንዲህ እያሉ?

ሀ. በሥጋ፡- ለምን ደሀ ሆንክ? ለምን መሐይም ሆንክ? ለምን ሰላም አጣህ? ለምን ጭፍራ ሆንክ? ለምን አልቻልክም? ... ወዘተ

ለ. በመንፈስ፡- አምላካችን ማነው? እንዴት አመንከው? ምን ሠራልህ? ከዚህ /ከዚያ/ በምን ይለያል? ለምን እነ እገሌ እንዲህ ይላሉ? ለምን ለዚህ መልስ አትሰጠኝም? ለምን ታዲያ አንተ የሥነ ምግባር ችግር ታየብህ? የአምላካችን የማዳን /የረድኤት/ ስሜት እንዴት እናገኘዋለን? ወዘተ እነዚህ ሁሉ ልጆቻችንና ትውልዱ ዛሬ የሚጠይቃቸው፣ ነገም የሚጠይቀን፣ መመለስ ያለባቸው ጥያቄዎች ናቸው። እነዚህን ሁሉ አሟልተን መልስ ለመስጠት ግን ጊዜያችንን በአግባቡ መጠቀም፤ በፍጥነት ወደ ተገቢው የሥራና የዕውቀት ኃይል መድረስ አለብን።

ከላይ ከጠቀስነው ሌላ ደግሞ ነገ ስንሸመግል የምንጦርበት ተገቢ የማኅበረሰብ ሥነ ልቡና፣ የኢኮኖሚ መሠረት፣ ፖለቲካዊ መረጋጋት ... ወዘተ እያጣን እንዳንሔድ ነው። አምላክ ከፈቀደ የነገው ዓለም አረጋውያን እኛ ጐልማሶች ነን። በሽምግልና ደግሞ የምንሠራበት ጉልበት፣ ለነገ ብለን በተስፋ የምናድርበት ሥነ ልቡና አይኖረንምና። ስለዚህ በነገው ዓለም ላይ የሚኖረን ድርሻ ከፍተኛ ነው። ጥሩ ብንሆን ጥሩ የምናደርገው ክፉ ብንሆን ከፍቶ የምናገኘው እኛ ነን። ስለዚህ ዛሬ ቅር የምንሰኝባቸውን ጉዳዮች ሁሉ ፈጥነን ማስተካከል፤ መለወጥ ያለብን እኛ ጐልማሶች ነን። ሥራና ሓላፊነት ካመጡብን የባካናነት ፈተና በተቻለ መጠን ለመዳን እየጣርን፤ ኃብቻችንን ለንስሐ ሕይወት፣ ገንዘብና ዕውቃችንን ለጽድቅና ለትሩፋት እንደ ዕድል መጠቀምን ለራሳችንና ለመጪው ትውልድ ማስጨበጥ ይገባናል።

*ለአረጋውያን፡-* ሐሳብ አያረጅም፤ ሥጋ ግን ይደክማል። ስለዚህ ማሰብን ባናቆምም የምናስበውን ያህል ማድረግ ባለመቻላችን ሊሰማን ይችላል። በመሆኑም ዕድሜያችን ትናንትን ብቻ በማሰብ በትዝታ እንድንዋጥ ማለትም በሠራናቸው መልካም ነገሮች እርካታን ስናገኝ፣ በጐደለብን ደግሞ ቁጭት ሲጫነን ይገኛል። በተለይም ማድረግ እየቻልን በስንፍናና ባለአዋቂነት ሳናደርግ ባለፍናቸው፣ አድርገንም በአግባቡ ባለመፈጸማችን በከሠርንባቸው ነገሮች መጸጸት አይቀርም። ነገር ግን አሁንም ቢሆን ሞት ባይቀርም ቁጥራቸውን የማናውቃቸውን ጊዜያት መኖርን ቀጥለናል።

ስለዚህም በሽምግልና ወራታችን ልንሠራቸው የሚገቡ ወሳኝ ጉዳዮች ይኖራሉ።

፩ኛ/ በክፉም ይሁን በደግ ያገኘናቸውን ጥሩ ልምዶች በጉብዝና ወራታቸው ሌሎች /ቤተሰቦቻችን ባልንጀሮቻችን .../ እንዲጠቀሙበት ማድረግ፤

፪ኛ/ የነበርንባቸው ተገቢ ያልነበሩ ርምጃዎችን ትውልዱ /ቤተሰባችን፣ ጉረቤታችን .../ እንዳይደግመው እስከተማጽኖ የሚደርስ ምክር መስጠት፤

፫ኛ/ ትውልዱን ከመርገም ይልቅ መመረቅ /በጸሎትና በይቅርታ ማሰብ/፤

፬ኛ/ ያቀዱትን በጊዜው መፈጸምን፣ ጊዜና ገንዘብን በአግባቡ መጠቀምን አበክሮ ማስረዳት፤

፭ኛ/ በወጣትነት ወራት ጠቃሚ /ጣፋጭ/ የሚመስሉ በጉልምስናና በሽምግልና ወራት ለጸጸት የሚዳርጉ አካሄዶችን ደጋግሞ መጠቆም፤

፮ኛ/ የሥነ ምግባር ጉዳዮች ለነፍስና ለሥጋ የሚሰጡትን ጥቅም ማስገንዘብ፤

፯ኛ/ በሽምግልናችን ወራት በአቅማችን ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ፈጣሪን ደስ የሚያሰኙ ተግባራትን መፈጸም፤ የተጣሉትን ማስታረቅ፣ በጸሎት መጋደል፣ ወዘተ።

በሃይማኖት ጸንቶ፤ በንስሐ የታደሰ ሰውነት ይዞ፤ በሥጋውና በደሙ ከብሮ ሁሌም መገኘትንና ሌሎች ተገቢ ነገሮችን በመፈጸም በመልካም ሽምግልና ይህን ዓለም ለመሰናበት መዘጋጀት ይኖርብናል። ቅዱስ መጽሐፍ ጊዜያቸውን በአግባቡ ተጠቅመው በክብር ስላለፉ አባቶች ሲናገር «ዕድሜም፣ ባለጠግነትም፣ ክብርም ጠግቦ በመልካም ሽምግልና ሞተ።» እንዳለ ለዚህ በሚያበቃ መንፈሳዊ ንቃት እንንገዝ። /፩ዜና.፳፱÷፳፰፤ ዘፍ.፳፭÷፲/

*በነገው ዓለም ላይ የሚኖረን ድርሻ ከፍተኛ ነው። ጥሩ ብንሆን ጥሩ የምናደርገው ክፉ ብንሆን ከፍቶ የምናገኘው እኛ ነን። ስለዚህ ዛሬ ቅር የምንሰኝባቸውን ጉዳዮች ሁሉ ፈጥነን ማስተካከል፤ መለወጥ ያለብን እኛ ጐልማሶች ነን። ሥራና ሓላፊነት ካመጡብን የባካናነት ፈተና በተቻለ መጠን ለመዳን እየጣርን፤ ኃብቻችንን ለንስሐ ሕይወት፣ ገንዘብና ዕውቃችንን ለጽድቅና ለትሩፋት እንደ ዕድል መጠቀምን ለራሳችንና ለመጪው ትውልድ ማስጨበጥ ይገባናል።*

ዕድሜያችን በሰጠን ልምድና ዕውቀት፣ ለማከናወን አቅማችን ለሚፈቅዳቸው ተግባራት ባለን በቂ ጊዜ ከችኩልነት የጸዳ ነገረ ገብነታችንን በመጠቀም፣ ያለንን ተሰሚነትና ክብር እንደ ዕድል በመቁጠር በዚህ በሦስተኛው ሺሕ ጀማሪ ትውልድ ስኬት ውስጥ እጃችን እናስገባ። መጪው ጊዜ ሳይቀድመን እንነሣ።✤



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# መዝሙራችን ወዴት

*በ፲፮ኛ ዓመት ቁጥር ፪ ዕትማችን በዘማርያን የዜማና ግጥም ድርሰት ላይ ከሚመለከታቸው የዜማ ሊቃውንትና ደራስያን ጋር ቃለ ምልልስ ማድረጋችን ይታወሳል። በዚህ ዕትም ደግሞ በካሴትና በሲዲ ተዘጋጅተው በሚወጡ መዝሙሮች ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለማስተካከል ያልተቻለበትን ምክንያትና ሊወሰድ የሚገባውን መፍትሔ በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋራ ቃለ ምልልስ አድርገናል፤ እነሆ።*

## «ለችግሩ መፈጠር ሁላችንም ተጠያቂ መሆናችንን መረዳት አለብን»



*መ/ር ዘመድኩን በቀለ*
*የጌልጌላ መንፈሳዊ መዝሙር ቤት ባለቤት*

*መ/ር ዘመድኩን በቀለ የጌልጌላ መንፈሳዊ መዝሙር ቤት ባለቤትና አሳታሚ ናቸው። የበርካታ ዘማርያንን መዝሙር አሳትመዋል። በአሁኑ ወቅት ስለሚያሳትሙት የመዝሙር ኅትመቶች ይዘት የሚሉት እንደሚከተለው ቀርቧል።*

*ሐመር፦* መዝሙር ሲያሳትሙ መስፈርትዎ ምንድን ነው?

*መ/ር ዘመድኩን፦* መዝሙር ማሳተም የጀመርኩበት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ገና ባልበሰልኩበት የዕድሜ ክልል በስሜታዊነት በመነሣት ነበር። ለግጥሙም፣ ለዜማውም ብዙም አልጨነቅም፤ ነበር። ከበሮ እስከገባበት፣ ጭብጨባ እስካለበት፣ ዕልልታ እስከተሰማበት ድረስም ለእኔ መዝሙር ነበር። በኋላ ግን ማንበብ፣ መማር፣ አንዳንድ ወቀሳዎችን መስማት ስጀምር ሁኔታዎች ተቀየሩ። በሥራዎቼ ላይ ፍርሃት እየታከለበት ጥንቃቄ እያደረኩ መጣሁ። ግጥሞቹም፣ ዜማዎቹም ላይ ጥንቃቄ መውሰድ ጀመርኩ። እንደ መዝሙር ቤቱ ስም /ትልቅነት/ ያሳተምኳቸው የመዝሙር ኅትመቶች በጣም ጥቂት ናቸው። ምክንያቱ ደግሞ የአቅም ማነስ ሳይሆን ጥንቃቄ ለመውሰድ ስል ነው።

በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም 'ቋንቋዬ ነሽ' የሚለውን መዝሙር ካሳተምኩ በኋላ እስከ አሁን ድረስ መዝሙር አላሳተምኩም። ምክንያቱም ፍራቻ ስላለብኝ ነው። በአሁኑ ወቅት ጩኸቱም እየበዛ ስለመጣ የግድ መጠንቀቅ አለብኝ። የመጀመሪያ ዓመታትና ከዚያ በኋላ ያሉት ሥራዎቼ የተለያዩ ናቸው። እኔ ጋ ዘማሪው ግጥሙን ይዞ ሲመጣ ግጥሞቹን አያለሁ። በኋላም ከእኔ በላይ ለሆኑት መምህራን አሳያለሁ። ግጥሙ ከሐዲስ ኪዳን የተወሰደ ከሆነ ለሐዲስ ኪዳን መምህራን፣ ግጥሙ ከብሉይ ኪዳን ከተወሰደ ለብሉይ ኪዳን መምህራን፤ ከገድል ከመልኮች ላይ የተወሰደም ከሆነ ሌሎች ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እንዲያዩት አደርጋለሁ። እንደዚህም ጥንቃቄ ተደርጎበት፣ እነዚህ ሰዎችም አይተውት አንዳንዴ የሚሾልኩ ግጥምና ዜማዎች አሉ። እነዚህ ከወጡም በኋላ ደግሞ ስሕተታቸውን ስረዳ የምሸማቀቅባቸው መዝሙሮች አሉ።

በዜማም በኩል ያለውን ስናይ ይመስላል ነው እንጂ በግእዝ፣ በዕዝል ወይም በአራራይ ውስጥ ክፍል አለው ብዬ የመወሰን ሥልጣኑ፣ ዕውቀቱም የለኝም። በአሁኑ ወቅት በየአውቶብሱ፣ በየመሥሪያ ቤቱም የትም ሆነህ የምትሰማው መዝሙር የኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ነው። ስለዚህ ዜማውን ለዜማ ሊቃውንት አሳያለሁ። ቤተክርስቲያን ለዚህ ብላ ያቋቋመችው


ወደ ገጽ ፲፬ ዞሯል




©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# እያመራ ነው?

## «መንበረ ፓትርያርኩ ባልፈቀደበት ተጠያቂ ሊሆን አይችልም»





መ/ር ዕንቈ ባሕርይ ተከስተ
በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ም/ሓላፊ

መምህር ዕንቈ ባሕርይ ተከስተ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ምክትል ሓላፊ ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት በገበያ ላይ ስለሚገኙ መዝሙራት መምሪያው ምን ይላል? ወደፊትስ ማዕከላዊነቱን በጠበቀ መልኩ መዝሙራት እንዲዘጋጁ መሆን አለበት በሚሉትና በሌሎችም ጥያቄዎች ዙሪያ አስተያየታቸውን ሰጥተውናል፤ እነሆ፡፡

*ሐመር፡- የሰንበት ትምህርት ቤት ማደራጃ መምሪያ ለሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎችና ለምእመናን መዝሙሮችን አደራጅቶ በማቅረብ ረገድ ምን ሠርቶ ነበር?*

መ/ር ዕንቈ ባሕርይ፡- መዝሙርን በተመለከተ ጠልቀን ሔደናል፡፡ የተጀመረው እኔ ወደ መምሪያው ከመምጣቴ በፊት በ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ነው፡፡ በወቅቱም ነባር የሆኑትን በሊቃውንት የተዘጋጁ የቤተክርስቲያን መዝሙሮች ከየአብያተ ክርስቲያናቱ እንዲሰባሰቡ ተደረገ፡፡ በዚያ መሠረት የተሰባሰበው ብቻ ሳይሆን አዲስም መጨመር አለባቸው ተብሎ የበለጠ ተሔደበት፡፡ ከግእዝ አንጻር መታየት ያለባቸውን በመለየት የቤተክርስቲያን ሥርዓት የጠበቁ መዝሙሮች የማዘጋጀት እንቅስቃሴ ነበር፡፡ እነ ሊቀ ትጉኃን ኃይለ ጊዮርጊስ፣ ከዚያ በኋላ በእነ መ/ር ኃይለ ማርያምና አቡነ መርሐ ክርስቶስ ባሉበት ኮሚቴ ታይቶ ጸደቀ፡፡ በኋላም ዜማውም መታየት አለበት ተብሎ ንቡረ ዕድ ኤልያስ አብርሃ፣ እኔና መሪጌታ ጌራ ወርቅ /ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ/ እንዲሁም መሪጌታ ሐዲስ /በለንደን የሚኖር/ ባለበት የተጠናከረ ሰፊ ጥናት ተደርጎ ዜማው ተስተካክሏል፡፡

ያ ብቻ አይደለም፤ ከእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ሁለት ወጣቶች ተውጣጥተው መዝሙር እንዲያጠኑ ወይም ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ይኸው ሥራ ቢያንስ ሁለት ጊዜ ወደ ሊቃውንት ጉባኤ ቀርቧል፡፡ ከዚያም መዝሙረ ማኅሌት ባለ ፫፻፴፮ ገጽ መጽሐፍ ተዘጋጅቷል፡፡ ካሜራ ሬዲ ከሆነ እንኳ ዘመናት ተቆጥሯል፡፡ ዛሬ በአዲስ አበባ የምታዩት ለውጥ በዚያን ጊዜ መሠረቱ የተጣለና እስከ አሁን ድረስ የደረሰ ነው፡፡ አሁን ፫፻፴፫ ማዕከላዊ መዝሙራን ይገኛሉ፡፡ እነዚህ የሠለጠኑት ወደ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቸው በመሔድ የሰንበት ትምህርት ቤት እና ግቢ ጉባኤያት ወጣቶችን ለማስተማር ነው፡፡

ወደ ገጽ ፲፮ ዞሯል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## «ለችግሩ መፈጠር ...»

ተቋም ስለሌለ አሁንም የምንሠራው በራሳችን ነው::

*ሐመር፡-* ለመሆኑ የምትመርጧቸው ሊቃውንት እንዴት ያሉ ናቸው?

*መ/ር ዘመድኩን፡-* በመጀመሪያ መታወቅ ያለበት ቤተክርስቲያኒቷ የመሠረተችው ማዕከል የለም:: ይሄ አለመኖሩ በራሱ ችግር ነው:: ቤተክርስቲያኒቷ የመደበቻቸው ተጠያቂነት ያለባቸው ሰዎች የሉም:: ይህ ሥራ በፍቅር የሚሠራ ነው:: ከንግድ እንቅስቃሴ /ከገቢ ምንጭነቱ/ አንፃር ብቻ መታየት የለበትም፤ ለቤተ ክርስቲያን የሚያበረክተው አስተዋጽኦም መታየት አለበት::

ስለዚህ እኔ ከመፍራቴና ከመጠንቀቄ የተነሣ በግሌ እከሌ ቢያየው ብዬ መዝሙራቱን እሰጣለሁ እንጂ እነ እከሌ ይዩ ተብሎ ቤተክርስቲያን የመደበቻቸው አካላት የሉም:: በዚህም ምክንያት ማዕከላዊነቱን የጠበቀ ሥራ መሥራት አልተቻለም:: እኔ እንደ ብቸኛ አማራጭ የወሰድኩት ግጥምና ዜማውን ለማውቃቸው ሊቃውንት ማሳየት ነው:: እነዚህ መምህራን ግን መዝሙር እና ግጥም እንዲመለከቱ ቤተክርስቲያኗ ውክልና የሰጠቻቸው አካላት አይደሉም::

*ሐመር፡-* መዝሙር ስታሳትሙ በአሠራር ከቤተ ክህነቱ ጋር ያላችሁ ግንኙነት እንዴት ነው?

*መ/ር ዘመድኩን፡-* እኛ ግንኙነታችን የጠነከረ እንዲሆን የተለያዩ ጥረቶች አድርገናል:: ዘማርያኑ፣ መዝሙር ቤቶች ቤተክህነቱ ዕውቅና ሰጥቶን በማኅበር ለመደራጀት ደጋግመን ጥያቄ አቅርበናል:: ይህንን መንገድ ለማስያዝ የሚፈልጉ እንዳሉ ሁሉ፣ ከግንዛቤ ጉድለት የተነሣ ፈቃደኞች ያልሆኑ አሉ:: የመተዳደሪያ ደንብ ቀርጸን ጫፍ ደረስ በምንልበት ጊዜ በተለየ አንፃር አይተውት እስከ አሁን ያልተሳካበት ሁኔታ ነው ያለው::

በተለይ ከላይ ያሉት ሰዎች እኔ ከጎጃም ጎንደር፣ ከጎንደር ወሎ፣ ከወሎ ሸዋ በባዶ እግሬ ውሻ እየበላኝ በ፬፻ እና በ፮፻ ብር ደመወዝ እየኖርኩ የማንም ዘፋኝ እዚህ መጥቶ በመኪና እየተንደላቀቀ፣ ቪላ ቤት እየሠራ የሚል የቅናት መንፈስ ያለባቸው ሰዎች ናቸው:: እነዚህ ሰዎች ነገሩን ከኑሮ ጋር በማዛመድ፤ ያላቸውን ሥልጣን ተጠቅመው ልጆቹን በመሰብሰብ ሓላፊነትን መወጣት ያልቻሉ አካላት አሉ:: ይሄ ትልቁ እንቅፋት ነው:: ሌሎች ደግሞ በሓላፊነት ደረጃ ተቀምጠው ውጤታማ ባይሆኑም ጥረት የሚያደርጉ ሰዎች አሉ:: ስለዚህ እነዚህ የሚጋጩ ነገሮች በመፈጠራቸው ተሰብስበን በተደጋጋሚ ብንጮህም ይህ

ከገጽ ፲፪ የዞረ

ነገር እኮ ለቤተክርስቲያኒቷ ይጠቅማል ብለው ከአባቶችም ከመምሪያ ሓላፊዎችም ለጉዳዩ ጆሮ በመስጠት ፈር ለማስያዝ የፈለገ የለም::

*ሐመር፡-* በእርስዎ መዝሙር ቤት የሚያወጧቸው መዝሙሮች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓትና ደንብ ጠብቀው የወጡ ናቸው ማለት ይቻላል?

*መ/ር ዘመድኩን፡-* እኔ ፍርሃት ያልኩት የሚጀምረኝ እዚህ ላይ ነው:: በመጀመሪያ «ናና አማኑኤል» የሚለውን የዘማሪ እንግዳወርቅን መዝሙር ስሠራ ግጥሙ እንዲህ የሚል ነበር፡-

«ናና አማኑኤል ናና መድኃኒቴ ·
አትርሳኝ ብሎኛል እኔም አልረሳውም
ጣርማ በር ላይ ያለው ቅዱስ
ጊዮርጊስ ነው ...
ናና አማኑኤል ናና መድኃኒቴ...»

ይላል::

ይህን ግጥም ስናየው በስሜት የሠራ ነው ነበር:: ቢሆንም ግን በወቅቱ መዝሙሩ ተሸጧል:: በየጉባኤው፣ በየዐውደ ምሕረቱ ተዘምሯል:: ካሴቱ ላይ ለጥፈን የሸጥነው ግን «በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓትና ደንብ መሠረት የተዘጋጀ» የሚል ነበር:: ይህን ለማለት መነሻችን ደግሞ ምንድን ነው? ያልን እንደሆን ከእኛ በፊት የነበሩት ዘማርያን መዝሙር ካሴት ላይ ተመሳሳይ ጽሑፍ ስላየን ነው::

እኛ የሠራነው በ፲፱፻፹ዎቹ አጋማሽ ላይ ነው:: ከዚያ በኋላ እኔ የሠራኋቸውን ኅትመቶች ብትመለከቷቸው «በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓትና ደንብ መሠረት የተጠዘጋጀ» የሚል ጽሑፍ የላቸውም:: በዛምትክ ያልኩት በተቻለ መጠን የቤተ ክርስቲያንን ትውፊቷን፣ ቀኖናዋን የጠበቀ ሥራ እንድንሠራ በጸሎታችሁ አግዙን፤ ነው:: ከዚህ ውጭ ምንም አማራጭ የለኝም:: ስለዚህ ካሴት ሳዘጋጅ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓትና ደንብ መሠረት የተዘጋጀ ነው ብዬ የማውጣት አቅሙ የለኝም:: ፈቃዱን የሰጠኝ ማነው? ስለዚህ የዚህ ሁሉ ድክመት ማንም በማንም ላይ ቢያሳብብ ከተጠያቂነት አያመልጥም:: እኔም በቅንነት የሠራሁት ተጠያቂነት ሲመጣ እጠየቅበታለሁ:: ነገር ግን መታየት ያለበት ቅን ፈራጁ ከየት ይመጣል ነው? ስለዚህ መዝሙር እነዚህን የመሰሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮች አሉበት::

*ሐመር፡-* ሥርዓት የጠበቁ መዝሙራት እንዲወጡ አሳታሚዎች ያደረጋችሁት የጋራ ጥረት አለ?

*መ/ር ዘመድኩን፡-* ጥረት አድርገናል:: የመዝሙር አሳታሚዎች ኅብረት አቋቁመናል:: ይህ ኅብረት ወደሚመለከታቸው አካላት ሄዶ አነጋግሯል:: እናንተ ብቻ ሳትሆኑ ሌሎችንም አሰባስባችሁ ዘማርያኑንም አካቱበት ተብሎ መልስ ተሰጠን:: ይህንንም አድርገን አንድ ርምጃ ሳንራመድ ነው በመንገድ የቀረነው::

ኅብረቱ እንዳለ ሆኖ ዘፋኞችን፣ ፕሮቴስታንቶችን፣ የመንዙማ አሳታሚዎችን በአንድ ላይ ይዞ የተመሠረተ «የኢትዮጵያ ኦድዮ ቪዥዋል አሳታሚዎች ማኅበር» የሚባል አለ:: መዝሙር ቤቶችም ይህ ድርጅት መብታችንን ያስጠብቅልናል በማለት በማኅበሩ ውስጥ ተሳታፊ ሆነናል:: በየወሩም መዋጮ እናዋጣለን:: እርግጥም ነው በመጠንከሩ እስከ ምክር ቤት ድረስ ልዩ ችሎት ተቋቁሟል:: መንግሥትም ጆሮ እስኪሰጥ ድረስ ኮፒን /ኦርጅናል ያልሆኑ/ በማስቀረት ረገድ ጥረት እያደረገ ነው::

ወደ እኛ ቤት ስንመጣ ደግሞ የተለየ ነው:: ፈር ማስያዝ አልተቻለም:: ለዚህ ተብሎ የተመደበ አካል የለም:: እነዚህ ሰዎች ያቀረቡት ሐሳብ ይጠቅማል ወይስ አይጠቅምም ተብሎ ያለንን ነገር እንኳን አቅርበን እንድንናገር አልተፈቀደልንም:: በአሁኑ ወቅት እንደምንመለከተው ያለውን የመዝሙር አገልግሎት እንቆጣጠረው ቢሉም እንኳ የማይቻል ነው:: በየጉባኤው እከሌ እከሌ የሚባል ዘማሪ እንዳይመጣብን ያሉ ደብሮች እንዳሉ ሁሉ ዛሬ እነርሱ ካልመጡ ጉባኤ አናደርግም የሚሉ አብያተ ክርስቲያናትም ተፈጥረዋል:: ይህ ምንድን ነው የሚጠቁመን? እዚህ መጥቶ የሚጫነን፣ የሚቆጣጠረን የለም:: ቢመጡም ችግር የለም በሚል ይቀበሏቸዋል:: በሌላ ጎኑ ደግሞ የእከሌ መዝሙር የያሬድን አይመስልም ተብሎም እንኳ ሰዎች እየተቀበሉ እየተዘመሩ ነው:: ስለዚህ ልዩነቱ እየሰፋ መጥቷል:: ይህ ደግሞ ከላይም ከታችም እየሰፋ የሚሄድ ነው:: ስለዚህ እኔ ከላይ የጠቀስኳቸው ነገሮች እስከሌሉ ድረስ የመዝሙር ቤቶች በራሳችን ተሰብስበን የምናመጣው ነገር የለም:: ነገር ግን ማዕከላዊነቱን የጠበቁ መዝሙራት እንዲወጡ አስቀድሞ እውቅና እንዲኖረው ሞክረናል ለማለት ነው::

*ሐመር፡-* እፈራለሁ ብለውን ነበር፤ ፍርሃትዎ ምንድን ነው? ልኩን ቢነግሩን?

*መ/ር ዘመድኩን፡-* ልምድ ሲቆይ ሕግ ይሆናል:: ያንን ልምድ የሚያስቀርና የሚመክር መስመር የሚያስይዝ እስከሌለ ድረስ ሕግ ሆኖ ይቀራል:: መዝሙር ከመጀመሩ በፊት የተወለዱት

ወደ ገጽ ፴፮ ዞሯል

## መዝሙራችን ወዴት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## «መንበረ ፓትርያርኩ... ...

ከገጽ ፲፫ የዞረ

*ሐመር፡- አሁን ባለው ሁኔታስ መምሪያው ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን የጠበቁ መዝሙሮች በገበያ ላይ የሉም የሚል አስተያየት አለው?*

**መ/ር ዕንቈ ባሕርይ፡-** ጥያቄው ትክክል ነው:: አንደኛ መዝሙራቱ በባለሙያ ደረጃ ተመርምረው በቤተክርስቲያን ደረጃ ማለፍ ነበረባቸው:: ሁለተኛ በቤተክርስቲያኗ ዕውቅና መስጠት ነበረባት:: ሦስተኛ መዝሙሮቹ ተራ ጩኸት ሳይሆኑ የቅድስና መዝሙሮች መሆን አለባቸው:: ለምሳሌ በቤተክርስቲያናችን አንድ ንዋየ ቅድሳት ሲገዛ ለዚያ የሚገባ ጸሎት ካልተጸለየበት በስተቀር ወደ ቤተክርስቲያን አይገባም:: እንደዚሁ ሁሉ በአሁኑ ወቅት ያሉ መዝሙሮች ዝም ብሎ ገጣሚ ስለገጠመው ብቻ መዝሙር ልንላቸው አንችልም:: ሌላ ስም ካልተሰጣቸው በቀር::

*ሐመር፡- ሥርዓት አለመጠበቃቸውን ስትረዱ ምን አደረጋችሁ?*

**መ/ር ዕንቈ ባሕርይ፡-** እኛ የምንለው በየመድረኩ በተደጋጋሚ የሚዘመሩትን ማደራጃ መምሪያው ለሚመለከታቸው አካላት ጽፎ መስመር እንዲይዙ፣ ሊያሳርሙ የሚገባቸው ካሉም እየመጡ እንዲያሳርሙ ነግረናቸዋል:: ምናልባት ለእነዚህ ሰዎች ማደራጃ መምሪያው የሚያስቸግራቸው ቢሆን እንኳን ሊቃውንት ጉባኤ እንዲሔዱ በስብሰባም ነግረናል:: በደብዳቤም አሳውቀናል:: ነገር ግን ለምን እንዳልተሰማን እኔ አላውቅም:: ምናልባት ጠንካራ ርምጃ ባለመውሰዳችን ይሆናል:: ከአቅማችን በላይ ነው ብለን ግን አናስብም:: ሰዎች ግን ይህን ሊረዱ እንኳ የቻሉ አይመስልም:: እኛም ርምጃ ለመውሰድ አልተጣደፍንም::

*ሐመር፡- አንዳንድ ምእመናን «መዝሙሩን» ዕውቅና እንደተሰጠው አድርገው ይጠቀሙበታል፡ ለዚህ ምን አስተያየት አለዎት?*

**መ/ር ዕንቈ ባሕርይ፡-** ቤተክርስቲያን ስላልገመገመችው ዕውቅና አይኖረውም:: ለምሳሌ እንደማሳያ ያህል ብጠቅስ በየቤተክርስቲያን የሚሰበከው ምስባክ፣ የሚነበበው ወንጌል አንድ ጊዜ የተዘጋጀ ሥርዓት ያለው ሕጋዊነቱን የጠበቀ ነው:: በቤተክርስቲያን የሚማረው መዝሙር፣ የሚቀደሰው ቅዳሴ በቤተክርስቲያን ዕውቅና ተደርጎለት ነው:: ሥልጣን ያለውም ቢሆን አያሻሽለውም:: ካህኑም አቅም የለኝም ብሎ ሊያልፈው አይችልም:: ይህ በሕግና በቀኖና በሥርዓት የሚኬድበት ነው:: ሕዝቡ ጤነኛውን መዝሙር መጠየቅ ነበረበት:: አብዛኛው ተቃውሞ የሚቀርበው ከወጣቱ አካባቢ ነው:: አንዳንዶች ቤተክርስቲያን ልትቆጣጠር በምትሔድበት ሰዓት እንደ ምቀኛ ወይም እንደ ተቃዋሚ አድርጎ የመመልከት ሁኔታ ይታያል:: በተሳሳተ አመለካከት የሚሔዱ ምእመናን ከሚከፋቸው በማለት በየጊዜው ሁኔታዎቹን ታግሰናል::

*ሐመር፡- አንዳንድ ዘማርያንና አሳታሚዎች በአሁኑ ወቅት ስለተፈጠረው ሁኔታ ተጠያቂው ጠቅላይ ቤተክህነት ነው ይላሉ:: የእርስዎ መልስ ምንድን ነው?*

**መ/ር ዕንቈ ባሕርይ፡-** መንበረ ፓትርያርኩ ባልፈቀደበት ተጠያቂ ሊሆን አይችልም::

*ሐመር፡- «በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓትና ደንብ የተዘጋጀ መዝሙር» የሚሉ ጽሑፎች በካሴትና በፖስተር ላይ ይለጠፋሉ:: መምሪያው ሳይፈቅድ በዚህ ስያሜ መጠቀም ይችላሉ?*

**መ/ር ዕንቈ ባሕርይ፡-** አይችሉም:: በመሠረቱ ይህን ከመንበረ ፓትርያርኩ የሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር የተነጋገርንበት ጉዳይ ነው:: ከእንግዲህ በዚህ አቅጣጫ ለሚሔዱ ሰዎች መምሪያው በዝምታ የቆየውና የዘገየው ትኩረት ባለመስጠት ሳይሆን ሰዎቹ ከዛሬ ነገ ከስሕተታቸው ይመለሳሉ፣ ይታረማሉ፣ ይማራሉ በማለት ቤቱ በትዕግሥት ለመጠባበቅ ነው:: አሁን ግን ቤቱ ባላወቀው መንገድ በቤቱ ስም መንቀሳቀስ አይችሉም:: ጉዳዩም ወደ ሕግ ተመርቷል::

*ሐመር፡- ችግሩን ለመቅረፍ ወይም ገምግማችሁ ትክክል ያለመሆናቸውን ለማሳየት የተጓዛችሁባቸው ሂደቶችን ቢዘረዝሩልን?*

**መ/ር ዕንቈ ባሕርይ፡-** በመጀመሪያ ደረጃ ከአንዴም ሦስት ጊዜ ስብሰባ ጠርተናቸዋል:: ሐሳባቸውን እንዲያስተካክሉ፣ አብረው ከቤቱ ጋር እንዲመካከሩ፣ የጎደለባቸው ነገር ካለ እንዲሟላ እና መስመርም ይዘው እንዲሔዱ ተነጋግረናል:: እነርሱ የሚያነሡት ጉዳይ ወደ ቤተክህነት ስንመጣ ቶሎ መልስ የሚሰጥ አካል የለም የሚል ነው:: ይሔ ግን ተጨባጭ የሆነ ነገር አይደለም:: ዝም ብሎ የተቀላቀለ በመሠረቱ መዝሙርም የማይባል የአማርኛ ግጥም መጥቶ መዝሙር ነውና በአስቸኳይ ካልፈቀዳችሁልኝ እኔ አወጣለሁ የሚል አመለካከት ከሕግ አንጻርም አያስኬድም::

በሁለተኛ ማደራጃ መምሪያው በመዝሙር ዙሪያ ምን መሆን አለበት በማለት ለሊቃውንት ጉባኤና ለተለያዩ መምሪያዎች ሐሳብ አቅርቧል:: ችግሮች እስኪቀረፉ እንደ አማራጭ በመዝሙረ ማኅሌት በኩል ያለውን ዝግጅት ማጠናከር ነው:: በመጀመሪያ የመዝሙረ ማኅሌት መጽሐፍ በአስቸኳይ እንዲታተም፣ በሁለተኛ ደረጃ ካሴት በጥራትና በብዛት በማሳተም እንዲሠራጩ፣ በሦስተኛ ደረጃ ቤተክርስቲያን ሳትፈቅድ በየመድረኩ አንዳችም ነገር እኔ ዘማሪ ነኝ ብሎ እንዳይወጣ ማድረግ እና በአራተኛ ደረጃ ደግሞ ለሕዝቡ ግንዛቤ መስጠት እንዳለብን ተገንዝበናል::

*ሐመር፡- አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች መንበረ ፓትርያርክ ልቆጣጠር የሚለው ሥርዓት ለማስከበር ሳይሆን ዘማርያን በሚያገኙት ገንዘብ ላይ ትኩረት በማድረጉ ነው ይላሉ:: የእርስዎ አስተያየት ምንድነው?*

**መ/ር ዕንቈ ባሕርይ፡-** በመሠረቱ ቤቱ የመቆጣጠር መብትና ሥልጣን አለው:: ለምሳሌ የግል መንፈሳዊ ጋዜጦች ነበሩ:: ከሥርዓት ውጪ ሲሔዱ ያቆማቸው ይሔ ቤት ነው:: መምሪያው የማስቆም ሥልጣን አለው:: እኛ የምናስበው ግን እንደዚህ አይደለም:: ሥርዓት እንዲይዙ፣ እንዲማሩ ነው:: በመሠረቱ ማደራጃ መምሪያው ከእነርሱ ገንዘብ ልሰብስብ ቢል እንኳን ከቅዱስ ሲኖዶስ ሕግና ፈቃድ አግኝቶ ከሆነ ነው:: ከአባላቱ ገንዘብ አይሰበስብም፣ ምክንያቱም ሥልጣን ስለሌለው ነው:: ይህን የማስፈጸም አቅም ያለው ሰበካ ጉባኤ ነው::

በሌላ በኩል ጉዳዩን በቅንነት ካየነው በቤተክርቲያን እስከተጠቀሙና እስከተገለገሉባት ድረስ መምሪያው ገንዘብ ቢጠይቅ ምንድን ነው ችግሩ? ለመምሪያቸው ገቢ ቢያደርጉለት ምን ያስከፋል? ከዚህ እኮ ነው የወጡት:: እኛ ያልናቸው ግን እነርሱ እንደሚያስቡት አይደለም:: ቢያንስ ለአሳደጋችሁ፣ ለአስተማራችሁ ሰንበት ትምህርት ቤት ከምታገኙት ላይ እስከ ዐሥር ፐርሰንት ስጡ ብለናቸዋል:: ያ ማለት ደግሞ ትተውት የወጡትን ሰንበት ትምህርት ቤት ለማጠናከርና ለማንቀሳቀስ እንጂ ለመምሪያው አስገቡ አልተባለም::

አለበለዚያ ግን እነርሱም በገንዘብ ገዝተውት አይደለም:: ካሴቶቻቸውን እየሸጡ ያሉት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ስም ነው ብለዋል:: ከተባለም የምናፍርበት ጉዳይ አይደለም:: እንደውም ይህ ከተባለ ዘንድ አንድ ነገር ሲሠራ እያንዳንዱ የአገልግሎት ዋጋ መክፈል አለበት:: ወደዚህ አቅጣጫ እየመጣን ነው፡ ግን አላልናቸውም:: እስከአሁን ድረስ የምንለው ግን ቢያንስ በሐሳብ እንግባባ ነው:: ለማቆምም ችግሮን አይደለም::

ወደ ገጽ ፴፯ ዞሯል

## እየመራ ነው?



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# የ«ሃይማኖተ አበው» ሚጠት /መመለስ/ የእሪያ እጥበት

*አሥራት ከበደ*

በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ግቢ ውስጥ ወደ አዳራሹ በሚወስደው መንገድ ዳር በአንደኛው ዛፍ አጠገብ ትክዝ ብለው ቆመዋል፡ የቀጠሩትን ሰው ጥበቃ፡፡

በራሳቸው ላይ ከደፉት ጥቁር ቆብ ሥር ዳር ዳሩን ብቅ ብሎ ዙሪያውን የሚታየው በአጭሩ የተቆረጡት በሽበት የታጀበው ጸጉራቸው ያብረቀርቃል፡፡ ከላይ ከደረቡት ረዥም ጥቁር ካባቸው ጋር ግርማ ሞገሳቸው የብዙ ዘመናት ሥልጣነ ክህነታቸውንና የቤተክርስቲያን አገልግሎታቸውን ይመሰክራል፡፡ አሁንም በቤተክርስቲያን ከፍተኛ የሓላፊነት ቦታ ላይ ተመድበው ያገለግላሉ፡፡

በአንድ እጃቸው የያዙትን በግማሽ ታጥፎ የተገለጠ የሐምሌ ወር ፳፻ ዓ.ም «ዜና ቤተክርስቲያን» ጋዜጣ እትም በሌላው እጃቸው በጨበጡት ዕፀ መስቀል በቀስታ እየጠበጠቡ በሐሳብ ተመስጠዋል፡፡ በጋዜጣው ላይ ስለ «ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» የወጣውን ዘገባ ሲያነቡ ቆይተዋል፡፡

እድገታቸው ከልጅነታቸው ጀምሮ በቤተክርስቲያን እቅፍ ከአባቶች እግር ሥር ሳይርቁ ነው፡፡ ከፊደል ቆጠራ እስከ ግብረ ዲቁና ከዚያም በየደረጃው መዝገበ ቅዳሴን ጠንቅቀዋል፡ ቅኔውንም አስመስክረዋል፡፡ ጊዜና ዕድል ገጥሚቸው የመጻሕፍቱን ትርጓሜ ታላላቁን ሊቃውንት በማግኘት ብሉያቱን መርምረዋል፡፡ በተለይም መጻሕፍተ ሐዲሳቱን አኺደዋል፡፡ እስከዚህ ዕድሜያቸው ድረስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከመመልከት ቦዝነው አያውቁም፡፡

በመደበኛው ዘመናዊ ትምህርትም በወጣትነት ዕድሜያቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው በሀገር ውስጥ በአዲስ አበባ ከሚገኙ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአንደኛው የከፍተኛ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል፡፡ ከሀገር ውጪም ወደ አውሮፓ ተሻግረው የከፍተኛ ትምህርታቸውን ለመከታተል ዕድል አግኝተዋል፡፡

በአዲስ አበባ የኮሌጅ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ወቅት የሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር አባል በመሆን በመንፈሳዊ አገልግሎት እንቅስቃሴው ተሳትፈዋል፡፡ በተለይም በወቅቱ በዩኒቨርስቲዎችና በየኮሌጆቹ የነበሩ ፕሮቴስታንት መምህራን በሚያስፋፉት የኑፋቄ ትምህርት የሚያስኮበልሏቸውን ወጣት ተማሪዎች ለመታደግ የቤተክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት በማስተማር ረገድ ማኅበሩ ያከናወነውን በጎ ተግባር ያስታውሳሉ፡፡

ከዚያም በኋላ ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት በማፈንገጥ የሚያደርገውን የተሳሳተ አካኼድ አስተውለዋል፡፡ በማኅበሩ እንቅስቃሴ ተሳታፊ የነበሩ እውነተኛ ኦርቶዶክሳውያን እርሳቸውም ጭምር ከዚህ ማኅበር ርቀው ዛሬም በቤተክርስቲያን ልጅነታቸው አገልግሎታቸውን በቅንነትና በትጋት የሚያበረክቱ እንዳሉ ያውቃሉ፡፡

በሌላም በኩል የማኅበሩን የተሳሳተ አካኼድ ተከትለው ከቤተክርስቲያን እቅፍ በመውጣት ወደ መናፍቃን አዳራሽ የኮበለሉ በጣም ብዙዎች እንዳሉም ያውቃሉ፡፡ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሀገር በተለያዩ የመናፍቃን ድርጅቶች ውስጥ በፓስተርነትና በተለያዩ ደረጃዎች የሚሠሩ በርካቶች ናቸው፡፡

ማኅበሩ የተመሠረተበት በጎ ዓላማ ከጊዜ በኋላ በዩኒቨርሳሊዝም አመለካከትና በፕሮቴስታንቲዝም ተጽዕኖ ሥር ወድቆ፡ በበጀት ድጎማና በጥቅማ ጥቅም ተንበርክኮ፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን እምነት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ ከማስከበር ይልቅ ምእመናን ልጆቿን እየሠለጠነ ወደ መናፍቃን አዳራሽ ማስኮብለሉ፡ እንዲሁም ተሐድሶ ያስፈልጋታል በማለት ለዚህ አፍራሽ ተልዕኮ መትጋቱን ሲያስቡ ውስጣቸው በሐዘን ይኮማተራል፡፡ እናም ራሳቸውን ይጠይቃሉ፡፡

በእርግጥ የዚህ ማኅበር አባላት በነበሩ እውነተኛ የቤተክርስቲያን ልጆች ማኅበሩ ከተሳሳተ አካኼዱ እንዲታረም እንዲስተካከል የተደረገው ጥረት ምንድነው? አሁንስ ቢሆን እንደለመደው እንደገና ወደ ቤተክርስቲያን ለመመለስ ያቀረበው ጥያቄ እውነት ከተሳሳተ መንገዱ ተመልሶ በቅድስት ቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት መሠረት አካኼዱን አስተካክሎ ይሆን? ወይስ እንደተለመደው ለማስመሰል ነው?

ከዚህ ቀደም የማኅበሩ አባል ሆነው በአገልግሎቱ ሲሳተፉ የነበሩ እውነተኛ የቤተክርስቲያን ልጆችስ አሁንም ቢሆን ማኅበሩ የተሰወረ ዓላማና አፍራሽ ተልዕኮ ካለው እንዲታረምና እንዲስተካከል የማድረግ ሓላፊነት የለብንም ወይ? በዝምታቸው ውስጥ ራሳቸውን እየደጋገሙ ይጠይቃሉ፡፡

እዚያው በቆሙበት እንዳሉ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ዋናው በር ነጭ 504 ፔጆ የቤት መኪና ፍጥነቱን ቀንሶ ወደ ውስጥ ገባ፡፡ መኪናው በስተቀኝ በኩል ባለው መንገድ አቅጣጫ ትንሽ ከሔደ በኋላ ጥግ ይዞ ቆመና ከውስጡ በሃምሣዎቹ መጨረሻ ዕድሜ ላይ የሚገኙ አባት ወጡ፡፡ የመኪናቸውን በር ቆልፈው መቀመጫ ያጨማደደውን ኮታቸውን እያስተካከሉ ወደ ቤተክርስቲያኑ ዓውደ ምሕረት አመሩ፡፡

አዲስ አበባ ሀገረስብከት ከሚገኙት አድባራት በአንዱ አጥቢያ የሰበካ ጉባኤ ምክትል ሊቀመንበር ሆነው ቤተክርስቲያንን በቅንነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ በ፲፱፻፶፱ ዎቹ መጨረሻና በ፲፱፻፷ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ በነበሩበት ወቅት በሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር አባል ሆነው በአገልግሎት ተሳትፈዋል፡፡ እርሳቸውና ሌሎችም የቅርብ ጓደኞቻቸው አሁንም በቅድስት ቤተክርስቲያን ልጅነታቸው እንዳሉ ሁሉ፤ በማኅበሩ የተሳሳተ ጎዳና ተጉዘው ከቤተክርስቲያን የኮበለሉና በፕሮቴስታንት የተለያዩ ድርጅቶች የሚገኙ በርካታ ሰዎችን ያውቃሉ፡፡ ከማኅበሩ ቢርቁም ወደ ቤተክርስቲያን ለመመለስ በየጊዜው በተደጋጋሚ የሚያቀርባቸውን ጥያቄዎች ያስታውሳሉ፡፡ ዛሬም በዜና ቤተክርስቲያን ጋዜጣ፤ ስለ ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር እንደገና ወደ ቤተክርስቲያን ለመመለስና የቢሮ ጥያቄ የወጣውን ዘገባ ሲያነቡ ብዙ ጥያቄዎች በአእምሮአቸው ይመላለሱባቸው ጀመር፡፡

ችላ ብለው የሚተውት ጉዳይ አልሆነም፡፡ እንደ ቤተክርስቲያን ልጅነታቸው ማድረግ ስላለባቸው ነገር ለመወያየት አሰቡ፡፡ የኮሌጅ ተማሪ በነበሩበት ወቅት አብረው የተማሩትና ቀድሞ በሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በአባልነት አብረው ይሳተፉ የነበሩ የቅርብ ጓደኛቸው ዘንድ ስልክ ደውለው ቀጠሮ ያዙ፡፡ በቀጠሮዋቸው መሠረት በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን ተገኝተው ከተሳለሙ በኋላ በአእምሮአቸው የሚመላለስባቸውን ጥያቄ እያሰላሰሉ ወደ ካቴድራሉ አዳራሽ የሚወስደውን መንገድ ይዘው አመሩ፡፡

የሃይማኖተ አበው ኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር አባል የነበሩት ዛሬም በቅንነትና በትጋት ቤተክርስቲያንን የሚያገለግሉ በአጠቃላይ እውነተኛ የቤተክርስቲያን ልጆች ሁሉ ይህን ጥያቄ በአጽንዖት የሚያስቡበት ጉዳይ ሆኗል፡፡

ሃይማኖተ አበው ኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም ሲመሠረት መልካም ሐሳብና ዓላማ ይዞ ነበር፡፡ በወቅቱ በዩኒቨርሲቲና ኮሌጆች ከውጭ ሀገር መጥተው ያስተምሩ የነበሩ ፕሮቴስታንቶች ሚሲዮናውያን ከመደበኛው የትምህርት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሥራቸው ውጪ ኑፋቄያቸውን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ዘንድ ያስፋፉ ጀመር:: ይህንን የመናፍቃን ሴራ ለመግታት በእውነተኛ የቤተክርስቲያን ልጆች ጥረት በቤተክህነት ድጋፍ ጭምር ማኅበሩ ተቋቁሞ ትክክለኛውን የቅድስት ቤተክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት በማስተማር እንቅስቃሴውን ቀጠለ::

ይሁን እንጂ ይህ በበጎ ዓላማ ላይ የተመሠረተ መልካም አግልግሎት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በማስከበር ሊዘልቅ አልቻለም:: ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም የዓለም ክርስ ቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን /World Christian Students Federation/ አባል ሆነ::

ማኅበሩ በስያሜው፣ በደብዳቤ መጻጻፊያ ወረቀቶቹ አናት/ከላይ/ በሚቀመጠው ሙሉ ስሙ፣ አድራሻውና ዓርማው እን ዲሁም ማኅተሙ ላይ፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥር ያለ መንፈሳዊ ማኅበር መሆኑን የሚያሳይ፣ የሚገልጽ ወይም የቤተክርስቲያኒቱ አካል መሆኑን የሚያመለክት ነገረ የለውም:: ሆኖም «የዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ቋሚ አባል ነው» በማለት በጉልህ ይገልጻል::

የዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን የቆመለት የተለየ ዓላማ ያለው ሲሆን፤ በተለይም በዓለም የሚገኙትን ክር ስቲያኖች አንድ ለማድረግ የተሐድሶ/ Reformation/ እንቅስቃሴን የሚያራምድ ነው:: ስለዚህ እያንዳንዱ የእምነት ተቋም አንድ የሚሆንበት የእምነት መገለጫ /Universalism/ መኖር አለበት ይላል:: ከሁሉም እምነት በመውሰድ የሚፈለገው አንድነትና የተውጣጣ እምነት እስኪ መጣ ድረስ አንድነት በልዩነት / Unity with Diversity/ የሚል አቋም አለው::

ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበርም የዚህ ድርጅት አባል ሲሆን የፌዴሬሽኑን ዓላማ ተቀብሎ በተግባር ማዋል ነበረበት:: በዚህም ምክንያት በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ ፫፤ «ለ/ተባባሪ አባልነት፦ ፩/ ማናቸውም የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አባል ያልሆነ ለክርስትና እምነትና ሕይወት ደንታ ያለው ከሆነ በተባባሪ አባልነት ከማኅበሩ ሊገባ ይች ላል::» የሚል አንቀጽ አስገባ:: እንዲ ሁም «ተባባሪዎቹ አባሎች በልዩ ልዩ እምነት ተከታዮችና በክርስትና ወገኖች መካከል አንድነትንና መግባባትን ያጠና ክራሉ ያስፋፋሉ::» የሚል መርሕ በደ ንቡ በማካተቱ በተለይም «ሙሉ ወን ጌል» ከሚባለው የፕሮቴስታንት የእም ነት ድርጅት በብዛት ወደ ሃይማኖት አበው ኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በአ ባልነት ተቀላቀሉ:: እነዚህ በተባባሪ አባልነት ስም ወደ ማኅበሩ የተቀላቀ ሉት የመናፍቃን መልእክተኞች ቀስ በቀስ ማኅበሩን ተቆጣጠሩት::_ሃይማኖተ አበው የተመሠረተበትን በጎ ዓላማ እየ ለቀቀ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን እም ነት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ ከማገ ልገል ይልቅ በተሳሳተ ጐዳና በመሔድ የፕ ሮቴስታንትን እምነትና ዓላማ እንዲያ ስፈጽም አድርገው ለወጡት::

ይህ ሁሉ ሲሆን ሥራዎቻቸውን ሁሉ የሚከናወኑት በስውር በመሆኑ በየደረጃው የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚመለከታ ቸው አባላትና ቅዱስ ሲኖዶስ ጭምር በጊዜው የሚያውቁት ነገር አልነበረም:: እጅግ ብዙ የዋሐን ምእመናን «ሃይማ ኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅ በር» ቀድሞ የነበረውን የተመሠረተበ ትን በጎ ዓላማ የለወጠ መሆኑን በውል ሳይገነዘቡት ቆይተው የመናፍቃን ሰለባ ሆነዋል:: በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ በሰንበት ት/ቤቶች አዳራሽ በወቅቱ ከሙሉ ወንጌል፣ ከመሠረተ ክርስቶስ፣ ከቤቴል መካነ ኢየሱስ ከሌሎችም የፕሮቴ ስታንት ድርጅቶች ፓስተሮችና መዘም ራን እየመጡ በሃይማኖተ አበው ጉባኤ «ያስተምራሉ»፣ «ይዘምራሉ»:: በጣም በርካታ የዋሐን ምእመናንና ወጣት የቤተ ክርስቲያን ልጆች በሃይማኖተ አበው ጉባኤና አዳራሽ የኑፋቄ ትምህርት ሥል ጠና እየተሰጣቸው ከቤተ ክርስቲያን እቅፍ እየወጡ ወደ ፕሮቴስታንቶች ጐራ እን ዲኮበልሉ ተደረገ:: የሃይማኖተ አበው መዘምራንም ወደ ፕሮቴስታንት የእም ነት ድርጅቶች አዳራሽና ጉባኤ በመሔድ መዝሙር ያቀርቡ ነበር::

ይህንኑ አስመልክቶ በ«ሬማ ወንጌል» ጋዜጣ ፩ኛ ዓመት ቁ.፱ ሰኔ ፲፱፻፺፫ ዓ.ም እትም ገጽ. ፰ ላይ ፓስተር እሸቱ ወርቁ በኢትዮጵያ «የሬማ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን» መሥራች፤ «ታዲያ በወቅቱ ስናደርግ የነበረው ከተለያዩ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናት ወጣት ዘማርያንን በየቅዳሜው ከሰዓት በኋላ በነበረን ግልጽ ስብሰባ /ሪቫይቫል/ እንጠራ ነበር:: ብዙ ወጣቶችም ወደ ጌታ ተመልሰዋል፡፡ ድነ ዋል:: … በዚያን ጊዜ አራት ኪሉ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የወጣቶች ሃይማ ኖተ አበው ማኅበር ውስጥ… በዛው ከነ በሩ ዘማርያንም ውስጥ… ወደ ሆስቴሉ ስብሰባችን ስንጠራቸው ከነበሩት እነ ሱም ነበሩበት:: አንዴ ጠርተናቸው የራሳቸውን ያሬዳዊ መዝሙር ከዘመሩ በኋላ በሚቀጥለው ሳምንት ያለጥሪ ነው ወደ ስብሰባችን ይመጡ የነበረው» በማ ለት የገለጸውን መጥቀስ አስፈላጊ ነው::

ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪ ዎች ማኅበር የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት በመጣስ ከቅዱስ ሲኖዶስ መመ ሪያ ውጪ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ለመቀየር ሲንቀሳቀስ ቆይቷል:: «የቅዳሴ ሰዓት ረዝሟል፣ ማጠር አለበት» «በያሬ ዳዊ ዜማ መዘመር አጓጉል ፈሪሳዊነት ነው» በማለት ከያሬዳዊ ዜማና ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ውጪ የሆኑ መዝ ሙሮችን በመዘመር፤ «የቤተ ክርስቲያን የዜማ መሣሪያዎች ወደ ጊታር፣ ኦርጋን፣ ፒያኖ፣ ሲንትሳይዘር፣ ሳክስፎን… ወዘተ መለወጥ አለበት» በማለት ብዙዎችን አሳስቷል:: ጥቂት አባላቱም የቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖትና ሥር ዓት የሚቃወም የኑፋቄ ትምህርታቸ ውን ሲያስፋፉ ቆይተዋል:: ይህን ሁሉ የሚያደርጉት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆነው ነበር:: በዚህም ብዙዎች የዋሐን ምእመናንን እያሳሳቱ ወደ ፕሮቴስታን ቶች አዳራሽ ለማስኮብለል ችለዋል:: እነዚህን ሰዎች ከስሕተታቸው እንዲ መለሱ ለማድረግ በጠቅላይ ቤተ ክህነት በተለያዩ ጊዜያት መመሪያዎች ተሰጥ ተው ነበር:: የማስተካከያ እርምጃዎች ተወስደዋል:: ሆኖም «ሃይማኖተ አበው

**በእርግጥ የዚህ ማኅበር አባላት በነበሩ እውነተኛ የቤተክርስቲያን ልጆች ማኅበሩ ከተሳሳተ አካሄዱ እንዲታረም እንዲስተካከል የተደረገው ጥረት ምንድነው? አሁንስ ቢሆን እንደለመደው እንደገና ወደ ቤተክርስቲያን ለመመለስ ያቀረበው ጥያቄ እውነት ከተሳሳተ መንገዱ ተመልሶ በቅድስት ቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት መሠረት አካሄዱን አስተካክሎ ይሆን?**




©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» ሊታረም ባለመቻሉ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት በተላለፈ ውሳኔ በ፲፱፻፸፬ ዓ.ም ተዘጋ:: ምንም ለውጥ ሳያደርግ በቀደመ አቋሙ ጸንቶ ከመናፍቃን ድርጅቶች ጋር እየሠራ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ቆየ::

ከዚያም ስሕተታችንን አርመን ራሳችንን አሻሽለናልና ተመልሰን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንድንገባ ይፈቀድልን፤ በማለት በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም ለቅዱስ ሲኖዶስ ጥያቄ አቀረቡ:: ቅዱስ ሲኖዶስም የቀረበውን ጥያቄ በማየት ኮሚቴ ሰይሞ ጉዳዩ እንዲጠና አደረገ:: ኮሚቴውም የጥናቱን ውጤት በዐሥራ አራት ገጽ ሪፖርት አቀረበ::

ቅዱስ ሲኖዶስ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሰብሳቢነት ሃያ ሰባት ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት ጉባኤ የኮሚቴውን ሪፖርት አዳምጦ በጉዳዩ ላይ በሰፊው ተወያየበት:: በመጨረሻም፤

፩/ ከዚህ በፊት «ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» ይባል የነበረው በቃለ ዓዋዲው መሠረት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ጽ/ቤት የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ተጠቃሎአል::

፪/ ሲየሚውና ሌላውም ቀደም ሲል ይመራበት የነበረው የውስጥ ደንብና መመሪያ ሁሉ በዚህ ውሳኔ ተሽሮአል:: በማለት ውሳኔ ሰጠ::

ከ፲፱፻፹፫ ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ በኋላ በተለይም በወቅቱ የነበረውን የሽግግር ጊዜ በቤተ ክርስቲያን የነበረውን ክፍተት በመጠቀም «ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» ወደ ቤተ ክርስቲያን ልመለስ የሚል ጥያቄዎች እንደተለመደው አቀረበ:: በዚህም መሠረት ጥቅምት ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ.ም በተሰጠው ውሳኔ፤

፩ኛ/ በማዕከል ደረጃ አንድ ጠንካራ አስተማሪ፣ መሪና የበላይ አባት እንዲመደብለት

፪ኛ/ በየሀገረ ስብከቱ የሚቋቋሙ የዚሁ ቅርንጫፍ ማኅበራትም ተጠሪነታቸው ለየሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ሆኖ የበላይ ጠባቂ አባት የየሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳት እንዲሆኑ

3ኛ/ የማኅበሩን መተዳደሪያና የውስጥ የሥራ መመሪያ ከቃለ ዓዋዲውና ከቤተ ክርስቲያናችን መመሪያዎች ጋር በሚጣጣም ሁኔታ በጥንቃቄ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ እና በቅዱስ ሲኖዶስ ታይቶና ጸድቆ ሲሰጣቸው የትምህርት ፕሮግራሙን እንዲቀጥል ውሳኔውን መሠረት ያደረገ መመሪያ ተሰጠ::

ሆኖም ማኅበሩ ከቅዱስ ሲኖዶስ በተሰጠው ውሳኔ እና መመሪያ መሠረት፤ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፤ ቃለ ዓዋዲና መመሪያ ጋር በማጣጣም የማኅበሩን መተዳደሪያና መመሪያ አዘጋጅቶ ሊያቀርብ አልቻለም:: ከሁለት ዓመታት በላይ መመሪያውን ለቅዱስ ሲኖዶስ አቅርቦ ሳያስወስን፣ በሕጋዊ መንገድ አገልግሎቱን እንዲቀጥል መመሪያ ሳይሰጠውና የቀድሞ አቋሙን ሳይለውጥ፤ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና መመሪያ ውጭ በተለያዩ አህጉረ ስብከትና አጥቢያዎች የኑፋቄ ትምህርቱን በማሠራጨት፣ በዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች መዝሙሮችን እያዘጋጀ በማስፋፋት የኑፋቄ ሥራውን ቀጠለ:: ይኸው ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የጣሰ ድርጊት ሊቀጥል እንደማይገባ የቅዱስ ሲኖዶስን ውሳኔ በመግለጽ በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽሙ በወቅቱ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ኅዳር ፪ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ መመሪያ ተሰጥቶ ነበር:: ይኸው መመሪያ ለሁሉም አህጉረ ስብከትም እንዲተላለፍ ተደርጓል::

በዚህ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው እርምጃ በመውሰድ በቅዱስ ሲኖዶስ የተወሰኑ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ቢተላለፉም፤ «ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» በትክክለኛ የቤተ ክርስቲያን ልጅነት ውሳኔውንም ሆነ መመሪያውን ተቀብሎ ተግባራዊ በማድረግ ራሱን ሊያርምና አካኼዱን ሊያስተካክል አልቻለም:: ቤተ ክርስቲያን አውግዛ የለየቻቸው «የተሐድሶ መነኮሳት ኅብረት» አባላት የሃይማኖተ አበውን እንቅስቃሴ ተረድተው በመደገፍ አብረው ይሠሩ እንደነበረ ጭምር፤ «መነኩሴ» ነኝ የሚል የተሐድሶ መናፍቃን እንቅስቃሴ አራማጅ፤ ለ «መጽናናት» ጋዜጣ ፩ኛ ዓመት /፲፪/ ቁጥር ፶፣ ሐምሌ ፲፫ ቀን ፲፱፻፹፱ እትም ላይ በሰጠው ቃለ መጠይቅ ገልጿል::

ይህ ማኅበር በቀደመ አቋሙ ጸንቶ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥርዓት ባፈነገጠው ከተሳሳተ አካኼዱ ሊመለስ ባለመቻሉ ለፕሮቴስታንት ዓላማ ማስፈጸሚያ መሣሪያ ሆኗል:: ቤተ ክርስቲያንም በተለያዩ ጊዜያት በየደረጃው በወሰደችው እርምጃ በሕጋዊ ደብዳቤ ብታግደውም ውሳኔውን በመጣስ ከእንቅስቃሴው ሊታቀብ አልቻለም:: ስለዚህ ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት፤ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት፤ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በቁጥር 821/2900/88፣ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም፤ እንዲሁም ለኢትዮ ጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፍትሕ ሚኒስቴር መስከረም ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም በቁጥር /443/2900/92 በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ በተጻፈ ደብዳቤ፤ በቤተ ክር ስቲያን ላይ እያደረሰ ያለውን ጥፋት የሚገልጽ ማስረጃዎችን በማያያዝ፤ ማኅበሩ ያለ ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም የሚያደርገው እንቅስቃሴ እንዲታገድ ወደፊትም በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ምንም ዓይነት ፈቃድ እንዳይሰጠው በማስታወቅ እንዲዘጋ አደረገች::

«ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» «የዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌደሬሽን» ቋሚ አባል ከሆነ በኋላ በተባባሪ አባልነት ስም ወደ ማኅበሩ በተቀላቀሉ የፕሮቴስታንት እምነት ድርጅቶች መልእክተኞች ሴራና ተጽዕኖ የተመሠረተበትን በጎ ዓላማ እየለቀቀ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖትና ሥርዓት በመጣስ የመናፍቃኑን ዓላማ ሲያስፈጽም ቆይቷል:: በተለይም ከ፲፱፻፷፱/፸/ ዓ.ም ወዲህ በተደጋጋሚ ቤተ ክርስቲያን በማኅበሩ ላይ እርምጃ ወስዳለች፣ ውሳኔ አሳልፋለች፤ መመሪያ አውጥታለች:: ሆኖም ከሠላሳ ዓመታት በላይ ማኅበሩ በተግባር ባይገልጸውም እታረማለሁ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንድመለስ ይፈቀድልኝ በማለት በየጊዜው ተደጋጋሚ ጥያቄ ሲያቀርብ ቆይቷል:: ብዙዎቹ አባላቱ በኮበለሉባቸው የተለያዩ የፕሮቴስ ታንት እምነት ድርጅቶች ተበታትነዋል:: የማኅበሩን ከቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥርዓት ያፈነገጠ ሥራና የተሳሳተ አካኼድ ተረድተው የራቁት እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ጸንተው በአገልግሎት ይገኛሉ:: ስለዚህ ማኅበሩ አሁንም በቅርቡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ልመለስ የሚለውን ጥያቄ ሲያቀርብ ዓላማው ምን ሊሆን ይችላል? በኑፋቄው ያልተበረዙት ጤና ማዎቹ አባላቱን ሳይይዝ በድብቅና በውስጥ ለውስጥ ጉዞ ማንም ባልፈረመበት ደብዳቤ ደጅ መጥናቱስ ለምን ይሆን? ምናልባትም በመናፍቃን ጉራ ያሉትን አባላት ይዞ እና እንደገና ተመልሰን ከዚህ ቀደም ያላጠናቀቅነውን የተሐድሶ ኑፋቄ ሥራ እንቀጥላለን በማለት አድብተው የሚጠባበቁ አባላቱን ይዞ እንደሚመጣ መገመት አያስቸግርም::

---

ስሁን ራሱም ሆነ ቀደም ብሎ በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሓላፊ በኩል በዓመት ከሰራት ጊዜ በላይ ጥያቄውን ስያቀረበ ያለው የ«ሃይማኖተ ስበው የተማሪዎች ማኅበር»ን የመመለስ ጥያቄ «ሚጠት» ያል ነውም ቀደም ብለን ካየነው ጠባዩ በመነሣት ነው:: ሚጠት ስንደ ሙሴ በትር ስንዴ «ስባብ» ስንዴ «በትር» ስየሆኑ መኖር ነው:: የሃይማኖተ ስበውም ስመራርም ሲነቃበት ስየወጣ ደግሞም ስየተመለሰ ከሁለት ጊዜያት በላይ ተመልሶ ወጥቷል:: የስሁኑም ጥያቄው ከቀድሞው ግብሩ ሲመለሰው ስይችልም:: በዚህ ጠባዩም ከዕፊያዋ ጋር ይመሳሰላል::

---





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ማኅበሩ አሁን በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል? በአግባቡ የተጠና እና አስተማማኝ መረጃ ሊኖር ይገባል:: አሁንም ባቀረበው ወደ ቤተ ክርስቲያን ልመለስ የሚል ጥያቄው «ታርሜአለሁ» እንኳ ቢል የሚገልጸውን ብቻ አምኖ መቀበል ተገቢ እንዳልሆነ ሁሉም የሚገነዘበው ነገር ነው::

ቀድሞ የተመሠረተበትን በጎ ዓላማና የአገልግሎት መድረክ እንዲለውጥ ያስገደደው ግንኙነት፣ ከሠላሳ ስድስት ዓመታት በላይ ጠብቆ የቆየው የዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌደሬሽን የአባልነት ስምምነትና ውሎች ዛሬ በቀላሉ አቋርጦ ሊተዋቸው አይችልም:: በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው አሠራር መዋቅርና የግንኙነት መስመር ምን እንደሚመስል ማጥናትና ማረጋገጥ፤ በእርግጥ የአንዲት ቤተ ክርስቲያንን ሥርዓትና መመሪያ ጠብቆ መዋቅርና አሠራሯን ተከትሎ መገኘቱን ማረጋገጥ የግድ ይሆናል::

የፕሮቴስታንት እምነት ድርጅቶች መልእክተኞች የነበሩትን በተባባሪ አባልነት ስም የሚያሳትፍ ማኅበር፤ ቤተ ክርስቲያንን እናድሳለን የሚሉ በገሐድ ይንቀሳቀሱበት የነበረ ማኅበር፤ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርትና ሥርዓት ይነቅፍ የነበረና በሃይማኖት ምክንያት ችግር የነበረበትን ማኅበር፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመለስ በተለመደው ጠባዩ አሁንም እንደገና ጥያቄ ሲያቀርብ በጥንቃቄ መታየት እንዳለበት ሁሉም የሚገነዘበው ጉዳይ ነው::

ማኅበሩን ለብዙ ተጽዕኖ የዳረገው ሁሉን አቀፍ የሆነ እምነት መገለጫ /Universalism/ ከተሐድሶ /Reformation/ እንቅስቃሴ ጋር አንድነት በልዩነት /Unity with Diversity/ የሚለውን አመለካከትና መርሕ ከአንድ ትውልድ ዕድሜ በላይ ይዟቸው ዘልቋል:: እስከአሁን ድረስ ሲንቀሳቀስበት የነበረው የበጀት ምንጭ አሁንም እንዳለ መቀጠሉ ብዙዎች የሚናገሩት የአደባባይ ምስጢር ነው::

*ብዙዎቹ አባላቱ*
*በኮበለሉባቸው የተለያዩ*
*የፕሮቴስታንት እምነት*
*ድርጅቶች ተበታትነዋል::*
*የማኅበሩን ከቤተ ክርስቲያን*
*ትምህርትና ሥርዓት ያፈነገጠ*
*ሥራና የተሳሳተ አካኼድ*
*ተረድተው የራቁት*
*እውነተኛ የቤተ*
*ክርስቲያን ልጆች ደግሞ*
*በቤተ ክርስቲያን ጸንተው*
*በአገልግሎት ይገኛሉ:: ስለዚህ*
*ማኅበሩ አሁንም በቅርቡ ወደ*
*ቤተ ክርስቲያን ልመለስ*
*የሚለውን ጥያቄ ሲያቀርብ*
*ዓላማው ምን ሊሆን ይችላል?*

መሠረታዊ ዓላማውና መተዳደሪያ ደንቡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት፣ ሥርዓትና ትውፊት የጠበቀና ከመመሪያዎቿ ጋር የተጣጣመ መሆኑም በአግባቡ ሊመረመር የሚገባው ነው::

ሰዎቹስ በሚገባ ተምረውና ታርመው ከልብ ተጸጽተው በንስሐ ተመልሰው ይሆን? ወይስ እንደተለመደው ማኅበሩ እንደገና ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመለስ የማስመሰያ ሽፋን ነው? ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮችን በየአቅጣጫው በጥንቃቄ መመርመርና ማጥናት ያስፈልጋል::

የተሐድሶ መናፍቃን እንቅስቃሴዎች የተለያየ መልክና አቀራረብ እንዳላቸው ይታወቃል:: ራሳቸውን በገሐድ የገለጡት የፕሮቴስታንት እምነት የተለያዩ ድርጅቶች በራሳቸው ስትራቴጂ ዕቅድ ይዘው ሚሲዮኖቻቸውን በግልጽ በማስማራት ጭምር ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናኗን እየነጠቁ ሲወስዱ ቆይተዋል:: በተለያዩ ጊዜያት የሚከሰቱ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎችን ምክንያት በማድረግ በርዳታ እና በትምህርት ሰበብ እየደለሉ ልጆቿን ሲያስኰበልሉ ኖረዋል::

በሌላም በኩል የቤተ ክርስቲያኒቷን ትምህርት ተምረው ያደጉትንና በቤተ ክርስቲያኒቷ በተሰጣቸው ሥልጣናዎች ተዘጋጅተው በተለያዩ የአገልግሎት መስኮች የተሰማሩትን አንዳንድ አገልጋዮች በተለያዩ ዘዴዎች በመያዝና መሣሪያ በማድረግ ቤተ ክርስቲያንን እናድሳት በማለት ወደ ፕሮቴስታንት ለመለወጥ እንደሚንቀሳቀሱ በተለያዩ ጊዜያት በእግዚአብሔር ፈቃድ ከተገለጠው ሥራቸው ለመረዳት ይቻላል:: ታዲያ ከዚህ ተግባራቸው መመለሳቸው በምን ታየ?

እንዲሁም ደግሞ በተለያዩ አካባቢዎች የሚካኼዱ የቤተ ክርስቲያን ወጣቶችን እንቅስቃሴና አገልግሎት መግቢያ መንገድ በማድረግ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ለማወክና ስውር ዓላማቸውን ለማስፈጸም እንደሚተጉ ይታወቃል:: ለዚህ እንደ «ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» የመሳሰሉ ማኅበራት የሚጠቀሱናቸው:: አሁንም ቢሆን በዚህ ዓይነት ዘዴ በወጣቱ እንቅስቃሴ ስም መልካም ዓላማቸውን ሽፋን በማድረግ የ«ተሐድሶ» ነን ባዮችን ሥራ ለመሥራትና ቤተ ክርስቲያንን ለመለወጥ ለሚያደርጉት ጥረት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ መሣሪያ ላለመሆን በሚገባ መመርመርና ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው::

በተለይም በአሁኑ ጊዜ ምሥራቃውያኑን /ኦሪየንታል/ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አኀት አብያተ ክርስቲያን ለመከፋፈልና ለመለወጥ የሚያደርጉትን የተሐድሶ እንቅስቃሴ ስልት በሚገባ ተረድቶ በጥንቃቄ መራመድ የግድ ነው::

ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ በሕንድ ደቡባዊ ምዕራብ የባሕር ዳርቻ፤ የመካከለኛው ምሥራቅና የሩቅ ምሥራቅ የንግድ መተላለፊያ ማዕከል በነበረችው ማላባር በምትባለው ግዛት በ፶፪ ዓ.ም የመሠረታት የማላባር ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተሐድሶ መናፍቃን እንቅስቃሴ እስከመከፋፈል የደረሰባትን ፈተና ለግንዛቤ እንዲረዳ መጥቀሱ ጠቃሚ ነው::

በብዙ ፈተና ውስጥ ስትናጥ የቆየችው የሕንድ ማላባር /ማላንካራ/ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በ፲፰ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ሕንድ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሥር ስትወድቅ፤ በየአካባቢው ገዥ ሆነው የሚቀመጡት የእንግሊዝ ጦር አዛዦች በመንፈሳዊነት ካባ ወደ ቤተ ክርስቲያኒቷ በመሔድ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ርዳታ መስጠት ጀመሩ:: ወንጌል መሰበክ አለበት፤ በሚል ሰበብ በማላያላም /Malayalam/ የአካባቢው ቋንቋ የአንግሊካኑ ሚሲዮናዊያን ተጽዕኖ ያረፈበትን መጽሐፍ ቅዱስ አስተርጉመው በማሳተም አሠራጩ:: ከእንግሊዝ አገር ከለንደን ሚሲዮናውያንን አስመጥተው ሕዝቡን እንዲያስተምሩና ቀስ በቀስ እንዲለውጡ አደረጉ:: በዚህ ሁኔታ ከጊዜ በኋላ ጥቂት የቤተ ክርስቲያኒቷን አገልጋዮችና መምህራን ተከታዮቻቸው ለማድረግ ቻሉ::

ዶክተር አሌክሳንደር ማርቶማ ሜትሮፓሊታን /Alexander Mar Thoma Metropolitan/ የተሐድሶ እንቅስቃሴያቸውን ፻፶ኛ ዓመት ለመዘከር፤ «የማርቶማ ቤተ ክርስቲያን- ቅርስ እና ተልእኮ» /የሕንድ ተሐድሶ ቤተ ክርስቲያንን ነው/ /THE MAR THOMA CHURCH - Heritage and Mission/ በሚል ርእስ ባዘጋጁት መጽሐፋቸው ከገጽ. ፳፬-፳፺ እንደገለጹት፤ በቤተ ክርስቲያኗ የቀድሞ ሴሚናሪ ያስተምሩ የነበሩ መምህራን /ፕሮፌሰሮች/፤ ፓላኩናቱ አብራሃም ማልፓን ከማራሞን እና ካይታይል ፒቫ/ ሻ/ርግሒስ ማልባን ከኰታያም፤ «ቤተ ክርስቲያኗ ተሐድሶ ያስፈልጋታል» በማለት በትኩረት ይንቀሳቀሱ ጀመር:: በተለይም ማቬሊካራ በሚባለው አካባቢ የነበሩት የቤተ ክርስቲያኗ ጳጳስ /ሜትሮፖሊታን/ ከእንግሊዛውያኑ ሚሲዮናውያን ጋር የነበረውን ግንኙነት እንዲቋረጥ ሲያደርጉ አብራሃም ማልፓን /ፕሮፌሰር አብራሃም/ የተባለው የሴሚናሪው መምህር /በሕንድ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ እንቅስቃሴ መሪነት ይጠቀሳል/፤ በማላባር /ማላንካራ/ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ክርስቲያን መምጣት አለባቸው የሚላቸውን አስፈላጊ የተሐድሶ ለውጦች በመዘርዘር ሐሳቡን ገለጸ። ከዚያም አሥራ ሁለት የቤተ ክርስቲያኒቷን አገልጋዮች አስከትሎ ከቤተ ክርስቲያን በመውጣት ከእንግሊዞቹ ሚሲዮናውያን ጋር አብሮ ለመሥራት ጥያቄ አቀረበ። ነገር ግን በዚህ ሁኔታ ከቤተ ክርስቲያኒቷ በአንድ ጊዜ ተለይቶ በመውጣት በተሐድሶው እንቅስቃሴ የሚፈለገውን ለውጥና ውጤት ለማምጣት አልቻለም።

ስለዚህ ከቤተ ክርስቲያን ሳይለይ በውስጥ ሆኖ በመቆየት ተመሳስሎ የተሐድሶ እንቅስቃሴውን ማራመድ እንዳለበት በማመን እንደገና ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመመለስ ወሰነ። አስቀድሞ በነበረበት የማርሞን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን /Church at Maramon/ በጥንታዊቷ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የነበረውን የቅዳሴና ጸሎት ሥርዓት ሽፋን አድርጌ ቀጠለ። ቀስ በቀስ የተሐድሶ ኑፋቄውን ሥራ እያከናወነ ሕዝቡም ኑፋቄውን እየተላመደው እንዲሔድ አደረገ።

ለቅዱሳኑ፣ ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሚሰጠው ክብርና የሚደርሰው ጸሎት ቀስ በቀስ እየተቀነሰ እየተሰረዘ እንዲወጣ በማድረግ በሌሎች ቃላት እየተተካ መጣ። ይህ ሁሉ የሚደረገው ቀድሞ የነበረው የቅዳሴው ቅርጽ ሳይለወጥ አገልግሎቱ ሳይቀየር፣ ካህናቱ የሚያደርጉት አልባሳት ሳይቀር ወይም ሳይለወጥ፣ ሻማ ማብራቱ፣ ጧፍ እጣኑ ሳይቀር እንደቀድሞው ሁሉ ሳይጓ ደል ለሽፋን እየተከናወነ ነው። ከላይ ቅርጹ ብቻ ያለውን ሥር ዓተ ቅዳሴ ውስጡን ይዘቱን ብቻ በመቀየር ሌሎቹንም ለውጦች ከጊዜ ወደ ጊዜ ሕዝቡን እያላመዱ የተሐድሶው እንቅስቃሴ ሥር እየሰደደ ሔደ።

ሕዝቡም ከጊዜ ብዛት ለውጡን እየተ ላመደው አዲስ ትውልድ በተተካ ቁጥር ኑፋቄውን እየተቀበለው መጥቶ፣ ይኸው ዛሬ ጥንታዊቷ የሕንድ ማላባር ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከፍላ ተሐድሶ መናፍቃኑ የሕንድ ማርቶማ ቤተ ክርስቲያን /The Mar Thoma Church/ በመባል በሕንድም ሆነ በመላው ዓለም እየተስፋፉ ፻፶ኛ ዓመታቸውን አክብረዋል።

ርትዕት የሆነችውን ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት ለመቀስጥ አጽራረ ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም አቀራረባቸውን እየለዋወጡ ጥረት ማድረጋቸውና ጥቃት መፈጸማቸው ከአባቶቻችን የሚሰወር ጉዳይ እንዳልሆነ እናምናለን። ሆኖም በሃይማኖተ አበው የቀረበውን እንደገና ወደ ቤተ ክርስቲያን የመመለስ የተለመደ ጥያቄ፣ እንደየዘመኑ አኳኋን ከተለያየ አቅጣጫ በጥንቃቄ እንዲመረምሩት ለማሳሰብ ነው።

ማኅበሩ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርትና ሥርዓት በመጣስ በየጊዜው በፈጸማቸው ጥፋቶች ምክንያት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በየደረጃው የወሰደችው እርምጃ፣ በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ድረስ እንዲዘጋ የተወሰነው ውሳኔ እየታወቀ፣ በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሓላፊ «ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር» ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመለስ በደብዳቤ በተደጋጋሚ መጠየቁ ለምን ዓላማ ሊሆን ይችላል? የዚህ ማኅበር ችግር የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖትና ሥርዓት የመጣስ፣ ልጆቿን በኑፋቄ እያሠለጠኑ ወደ መናፍቃን አዳራሽ የማስኰብለል፣ የፕሮቴስታንት እምነት ድርጅቶች ዓላማ ማስፈጸሚያ መሣሪያ ሆኖ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ በደል የማድረስ የሃይማኖት ችግር መሆኑ ተግባሩ በገሐድ የገለጠው ነው። ይህ ሆኖ ሳለ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ ተልእኮ ለማስፈጸም የቆመ አካል ይህንን ሁሉ በደልና ጥፋት ያደረሰና በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ የተዘጋን ማኅበር «ይመለስልኝ» ብሎ ጥያቄ ማቅረቡ፣ በሚመለከተው የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ጉዳይ ቀርቦ በአግባቡ ታይቶ የሲኖዶሱ ውሳኔ ያላረፈበትን ጉዳይ በቤተ ክርስቲያኒቷ ልሳን በሆነው «ዜና ቤተ ክርስቲያን» ጋዜጣ መዘገብ በቤተ ክርስቲያን ልጆች ዘንድ ትልቅ ጥያቄን የሚፈጥር በአጽንዖት ሊመረመርና ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ነው። ምናልባትም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆነው ለማኅበሩ ዳግም ተመልሶ የቀረውን የተሐድሶ ኑፋቄ ሥራ እንዲሠራ መንገዱን የሚያመቻቹለት ይኖሩ እንደሆነ ማስተዋልም ጠቃሚ ነው።

**ማኅበሩ በስያሜው፣ በደብዳቤ መጻጻፊያ ወረቀቶቹ አናት /ከላይ/ በሚቀመጠው ሙሉ ስሙ፣ አድራሻውና ዓርማው እንዲሁም ማኅተሙ ላይ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥር ያለ መንፈሳዊ ማኅበር መሆኑን የሚያሳይ፣ የሚገልጽ ወይም የቤተክርስቲያኒቱ አካል መሆኑን የሚያመለክት ነገረ የለውም። ሆኖም «የዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ቋሚ አባል ነው» በማለት በጉልህ ይገልጻል።**

አሁን ራሱም ሆነ ቀደም ብሎ በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጀ መምሪያ ሓላፊ በኩል በዓመት ከአራት ጊዜ በላይ ጥያቄውን እያቀረበ ያለው የ«ሃይማኖተ አበው የተማሪዎች ማኅበር»ን የመመለስ ጥያቄ «ሚጠት» ያልነውም ቀደም ብለን ካየነው ጠባዩ በመነሣት ነው። ሚጠት እንደ ሙሴ በትር አንዴ «እባብ» አንዴ «በትር» እየሆኑ መኖር ነው። የሃይማኖተ አበውም አመራርም ሲነቃበት እየወጣ ደግሞም እየተመለሰ ከሁለት ጊዜያት በላይ ተመልሶ ወጥቷል። የአሁኑም ጥያቄው ከቀድሞው ግብሩ ሊመልሰው አይችልም። በዚህ ጠባዩም ከዕሪያዋ ጋር ይመሳሰላል። ዕሪያ እንደ ታጠበች ፈጥና ጭቃ ውስጥ ገብታ እንደ ምትንከባለለው የሃይማኖተ አበውም ጥያቄ ፈጥኖ ወደ ቀደመ ግብሩ በሰፊው ለመግባት ያቀረበው ነው። እንዳያውም ዕሪያስ ጭቃ ውስጥ የምትንከባለለው ከታጠበች በኋላ ነው። የሃይማኖተ አበው መሪዎች ግን «ተሳስተናል» የሚለውን የንስሐ ጥያቄ ባለማቅረባቸው ከምሳሌያቸውም ያንሣሉ። ስለዚህ የሚከተላቸው ሁሉ ዕንቁ ሥርዓታችንና ቤታችን ከዕሪያዎቹ ፊት ማንሣትን የተቀደሰውንም ከመስጠት መቆጠብን መዘንጋት አይገባውም።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

በማኅበረ ቅዱሳን የሰሜን አሜሪካ ማዕከል
መካነ ድር /website/
www.tewahedomedia.org



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# ክህነት በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርት

ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ

*ባለፉት ተከታታይ እትሞች ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለክህነት ካስተማራቸው ትምህርቶች On Priesthood ከሚለው ባለ ሦስት ቅጽ መጽሐፍ ውስጥ እየመረጥን ለጊዜያችን ያስፈልጋሉ የምንላቸውን ስናቀርብ መቆየታችን ይታወቃል። ተከታይ ክፍሉ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል።*

## የክህነትን ሥልጣንና ክብር አለመፈለግ

አንድ ካህን ሊኖሩት ከሚገቡት ከላይ ከተገለጹት ጋር ሌሎች ብዙዎች አሉ፣ ከእነዚህም በላይ በተለይ አንድ ሰው ሊኖርው የሚገባው ክህነትን ከመሻትና ከመፈለግ ፈጽሞ ነጻ ሊሆን ይገባዋል። ለክህነት ሹመት ምኞትና ፍላጎት ያለው ሰው ከመሾሙ በፊት /ለመሾም/ ብዙ አስቸጋሪ መንገዶችን ይሄዳል። ከተሾመም በኋላ ሥልጣኑን ላለማጣትና አጥብቆ ለመያዝ ሲል ስፍር ቁጥር የሌለው ስሕተትና ወንጀል ውስጥ ይገባል፤ ቁልምጫን እስከ መጠቀም፣ ብዙ ገንዘብ እስከ ማውጣት፤ . . . ይደርሳል። ፩ጢሞ. ፫፥፩

መጥፎ የሚሆነው ሥራውን መፈለግ ሳይሆን ሥልጣኑንና ክብሩን መፈለግ ነው። የክህነት ሥልጣን ምኞቱ የሌለው ሰው ሥራውን በፍጹም ነጻነት ያከናውናል። ሥልጣኑንና ሹመቱን የማይመኝ ሰው ቢሾምም ያንን ከማጣትና ከመውረድ አይፈራም፤ አይሳቀቅም። በዚህም ያለ ፍርሃትና ያለ ሥጋት ማንኛውንም ነገር ለክርስቲያኖች እንደሚገባ ያከናውናል።

ሹመታቸውን እንዳያጡ የሚፈሩና የሚጨነቁ ግን ሰውንም እግዚአብሔርንም የሚያሳዝን ድርጊት ወደ ማድረግ ይሄዳሉ። ከዚህ ፍቅረ ሲመት ነጻ የሆኑ ሰዎች ቢሾሙም፣ ከመንበራቸው ቢባረሩም ለክርስቲያን እንደሚገባ እኩል ደስተኞች ሊሆኑ ይገባል። ስለ እውነት ሲሉ መውረድና መባረር ቢደርስባቸው ይህ የክህነትን ሥራ በአግባቡ ከመፈጸም ያላነሰ ክብርና ዋጋ ያለው መሆኑን ሊረዱ ይገባል። እንዲህ ያለ ነገር ቢደርስበት በሐሰት ለሚከሱትና ለሚያባርሩትም ቅጣት ይሆንባቸዋል፤ ያመጣባቸዋል፤ ለእርሱም ታላቅ ዋጋ ያገኝበታል። /ማቴ.፭፥፲፩/።

ከቁጣ፥ ከስድብ፥ ከሻካራ ንግግር፥ ራሱን ነጻ ማድረግ ከበላይም ሆነ ከበታች ከሕዝቡም ሆነ ከባለሥልጣናት የሚነገርን ስድብ፣ ተግሣጽ አግባብ የሆነም ይሁን ያልሆነ መታገሥ ይገባዋል። ብዙ ጊዜ ተማሪዎች የመሪዎቻቸውን ስብእና፥ ንግግር... እንደ አብነት የመውሰድ ዝንባሌ አላቸው። ወደ እነዚህም ራሳቸውን ይስባሉ። ታዲያ መሪው ካህኑ ራሱ የማይገባ ቁጣ የሚቆጣ ከሆነ ሕዝቡን እንዴት አድርጎ አትቆጡ ሊላቸው፤ ቁጣቸውንስ ሊያስተዋቸው ይችላል? መሪው ቁጡ ሆኖ እያየ ማን ታጋሽ ሊሆን ይመኛል? የካህናት ሕጸጽ /ጉድለት/ ሊደበቅ /ሊሠወር/ አይቻልምና። ይልቁንም በጣም ተራ የሆነው ነገር እንኳ ሳይቀር በቶሎ ይፋ ይሆናል። ስለሆነም መልካም ሥራቸው ብዙዎችን ወደ እነርሱ በመሳብና እንደ እነርሱ ለመሆን እንዲነሣሡ በማድረግ እንደሚጠቅም ሁሉ ድክመቶቻቸው ደግሞ እንዲሁ ሰዎችን ለምግባርና ለትሩፋት የበለጠ ግዴለሾችና ስነፎች እንዲሆኑ፤ ጥሩ የሆነውን በመፈለግ ሂደት እንዲሰንፉ ያደርጋቸዋል።

> *የተቀደሰውንና አስፈሪ የሆነውን ነገር ክፉዎች ወይም ምናምንቴዎች ለሆኑ ሰዎች ከመስጠት የበለጠ የእግዚአብሔርን መዓት መጥራት ምን አለ? አንዳንዶች ለእነርሱ የማይገባቸውን ነገር፣ ሌሎች ደግሞ ከአቅማቸውና ከችሎታቸው በላይ የሆኑትን ነገሮች እንዲመሩና እንዲያስተዳድሩ ሲሰጣቸው የቤተ ክርስቲያን ነገር በሁሉም አቅጣጫ የተበላሸና የተምታታ ይሆናል።*

ስለዚህም እንደ አባት፣ እንደ መሪ የሚያዩትን ነፍሳት ብሩህ ያደርጋቸውና ይስባቸው ዘንድ ካህን በሁሉም አቅጣጫ ነፍሱ ብርህትና ንጽሕት ልትሆን ይገባል። የተራ ሰው ስሕተት ብዙ ሰው በማያየው ሁኔታ ስለሚፈጸም የሚያጠፋው ፈጻሚውን ብቻ ነው። በታወቀና በሚታይ ቦታ የተቀመጠ ሰው ስሕተት ግን በሁሉም ላይ ጉዳት ያደርሳል፤ የወደቁትን ለማንሣት በሚያደርጉት ጥረት ያሳንፋቸዋል። ለራሳቸው ለመጠን ቀቅ የሚሞክሩትን ተስፋ ወደ ማጣት ይመራቸዋል።

ከዚህም ባሻገር የተራ ሰዎች ስሕተቶች ቢገለጡና ቢታወቁ እንኳ ያን ያህል እዚህ ግባ የሚባል ጉዳት አያደርሱም። ታላቅ ቦታ ላይ የተቀመጡ ሰዎች ግን ለሁሉም በግልጽ ይታያሉ፤ በትንሽ ተራ ነገር ቢሳሳቱ እንኳ ይህ ለሌሎች ታላቅ ነገር መስሎ ይታያቸዋል። ሰዎች ኃጢአትን የሚለኩት በጥፋቱ መጠን ሳይሆን በሥራው ምንነትና ደረጃ ነውና።

ስለሆነም ካህን በሁሉም አቅጣጫ በጸና ግንብ በብረት አጥር መጠበቅ አለበት። የራሱን ሕይወትና አኗኗር ሁልጊዜ መመርመርና በጥንቃቄ መምራት አለበት። በዙሪያው የሚከቡት ሁሉ ደካማ ጎን፣ ቀዳዳ ፈልገው ለመውጋትና ድል ለማድረግ የሚያደቡ ናቸውና። ጠላቶችና ባላንጣዎች ብቻ ሳይሆኑ ጓደኞች፣ ወዳጅ መስለው በሚቀርቡት ብዙዎችም እንጂ። በምክንያት የሚደግፍ ሳይሆን በምክንያት የሚጥል ይበዛልና።

የካህን ሕይወት በሁሉም አቅጣጫ በሚገባ የተጠበቀ ከሆነ ለጠላት አይጋለጥም። ነገር ግን ትንሽ ለሆነ ነገር እንኳ ትኩረት ሳይሰጥ ቢቀር በሰው ጠባይ ዘንድ እንደሚታየው ሌሎቹ መልካም ሥራዎቹ ከከሳሾቹ አፍ እንዲያመልጥ አይረዱትም። ነገር ግን ያ ትንሽ ሕጸጽ ሌላውን ሁሉ ይሸፍነዋል፤ ጥላውን ያጠላበታል። ሁሉም ሰው በካህኑ ላይ ለመፍረድ የሚዘጋጀው ካህኑ ሥጋ ለባሽ እንደመሆኑ ወይም የሰው ባሕርይ ያለው እንደመሆኑ ሳይሆን መልአክ እንደሆነና ከሰብአዊ ድካምና ሕጸጽ ሁሉ ነጻ እንደ ወጣ አድርጎ ነው።

ክፉና ኃይለኛ የሆነን ሰው ጥንካሬው እስካለ ድረስ ሁሉም ቢፈሩትና ቢያቆላምጡትም (ምክንያቱም ሊቃወሙት ስለማይችሉ) ኃይሉ ደክሞ ነገሩ ሁሉ ተበላሽቶበት ቢያዩት ግን ወዳጆቹ የነበሩት ሁሉ ጭምብላቸውን ያወልቃሉ። ፈጥነውም ጠላቶቹና ባላንጣዎቹ ይሆናሉ። ደካማ ጎኖቹን ሁሉ እየፈለጉ ያጠቁታል፤ ከግዛቱም ያወርዱታል፤ በካህናትም እንዲሁ ነው።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

**መሐንዲስ ያልሆነ ሰው የቤትን ግንባታ ሥራ ለመሥራት ሓላፊነት አይወስድም፡፡ ችሎታ ያለው ሐኪም ካልሆነም በስተቀር የታመመን ሰው ለማከም አይሞክርም፡፡ ምንም ያህል ብዙዎች ቢለምኑትና ቢገፋፉትም እንኳ አለማወቁንና አለመቻሉን ለመግለጽና አይሆንልኝም ለማለት አያፍርም፡፡ ታዲያ ይህ እንዲህ ከሆነ የብዙዎች ነፍሳት አደራ በእርሱ ላይ የሚሆነው እርሱ ከሁሉ አስቀድሞ ራሱን ይመረምር ዘንድ አይገባውምን? ምንም ልምድና ችሎታ የሌለው ቢሆንም እንኳ እገሌ ስላዘዘው ወይም ሌላው ስላስገደደው ወይንም ሌላውን ሰው ላለማስቀየም ሲል የክህነትን አገልግሎት ይቀበላልን? እንዲህ ከሆነስ ከእነርሱ ጋር አብሮ ተያይዞ ግልጽ ወደ ሆነ ጥፋት ከመውደቅ እንዴት ሊያመልጥ ይችላል?**

ጠንካራ ሳለ ትንሽ ጊዜ ቀደም ብለው ያከብሩት፤ ያመሰግኑትና ይታዘዙት የነበሩት እርሱን ለመክሰስና ከሥልጣኑም ለማውረድ ትንሽ መግቢያ ቀዳዳ፣ መጨበጫ እጀታ ሲያገኙ ወዲያውኑ ራሳቸውን በጠላትነት ያሰልፋሉ፡፡ እንደ ክፉ መሪ ብቻ ሳይሆን ከዚያ በባሰ ሥዕል በመሣል ጥቃታቸውን ሁሉ ይሰነዝራሉ፡፡ «አንድም አካል ቢሰቃይ አካላት ሁሉ ከእርሱ ጋር ይሰቃያሉ፤ አንዱም አካል ቢከበር አካላት ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል፡፡» ያለው የሐዋርያው ቃል በዚህ ነገር ተገልብጦአልና፡፡ /፩ቆሮ.፲፪፥፳፮/፡፡

በካህኑ ጉድለት አብሮ የሚሰቃይ፥ በመከበሩ ደግሞ አብሮ ደስ የሚሰኝ ብዙም የለምና፡፡ ስለዚህ ካህኑ ራሱን በጥንቃቄ ከነገሮች ሁሉ መጠበቅ አለበት፡፡ እስካል ጠበቀ ድረስ በውድቀቱ የሚያዝንለት የለም፡፡ ሌላው ቀርቶ አንድ ሰው ፍጹም ሃይማኖተኛ ቢሆን እንኳ/ ይህ ለክህነት አገልግሎት ታላቅና አስፈላጊ ነገር ቢሆንም/ ከዚህ ጋር ተገቢ ችሎታና አስፈላጊውን ክህሎት አብሮ ካልያዘ ለክህነት በቂ አይሆንም፡፡

ራሳቸውን በመግዛት ብዙ የተጋደሉ፣ በጾም ራሳቸውን ያደከሙ፣ ብቻቸውን ሳሉ በእግዚአብሔር ተቀባይነት ያገኙ፣ በየቀኑም በዚሁ ተግባራቸው እየጨመሩ የሄዱ፣ ወደ ሕዝብ አገልግሎት ገብተው ከሰው ሲደባለቁና የብዙዎችን ስሕተት ማስተካከል ግድ ስሆነባቸው ለዚህ ታላቅ ተግባር የማይበቁ መሆናቸውን ገና ከመጀመሪያው በግልጽ የታዩ ብዙዎች አሉና፡፡ በዚሁ መቀጠል ግድ የሆነባቸው ሌሎች ደግሞ የቀደመውን የታረመና ጥብቅ የሆነ አኗኗራቸውን በመተው ሌሎችን በምንም ሳይጠቅሙ፥ በራሳቸው ላይ ታላቅ ጉዳትን አስከትለዋል፡፡

## ዕድሜ /ዕርግና/

አንድ ሰው በታናሽ የአገልግሎት ክፍል በማገልገል ዕድሜውን ቢገፋና ቢሸመግል ዕርግናውን በማክበር/ከዕርግናው የተነሣ/ ብቻ ከፍ ወዳለው መዓርግ እንዲሸጋገር ማድረግም እንዲሁ ተገቢ አይሆንም፡፡ እዚያ ዕድሜ ቢደርስም አሁንም የማይበቃ ከሆነስ? ይህ ማለት አረጋውያንን ወይንም ከገዳም የመጡ አይሹሙ ማለት አይደለም፡፡ ከገዳም መጥተው በዚህ ተልእኮ ያበሩና ያሸበረቁ አባቶች አሉና፡፡

ከዚህ የባሰ ሰበቦችን የሚያቀርቡ ሰዎችም አሉ፡፡ አንዳንዶች ክህነት የተሰጡት ከተቃዋሚዎች/ከጠላቶች/ ጎራ እንዳይሰለፉ ነው የሚሉ ሌሎች ደግሞ አሉ፡፡ ክፉን ነገር የሚሠሩ ሆነው ሳሉ ባይሾሙ በቤተክርስቲያን ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ በሚል ክህነትን ይሰጣሉ፡፡ ከዚህ የከፋ ስሕተት ምን ይኖር ይሆን? በክፋትና በዓመፃ የተሞሉ ክፉ ሰዎች ሊቀጡበት ስለሚገባው በደል ሲከበሩ፥ ክህነት ብቻ ሳይሆን ከቤተክርስቲያን አጥር ሊከለከሉበት ስለሚገባው ምክንያት ወደ ክህነት መዓርግ ሲወጡ ከዚህ የበለጠ ከአግባብነት የወጣ ምን ነገር ይኖር ይሆን?

የተቀደሰውንና አስፈሪ የሆነውን ነገር ክፉዎች ወይም ምናምንቴዎች ለሆኑ ሰዎች ከመስጠት የበለጠ የእግዚአብሔርን መዓት መጥራት ምን አለ? አንዳንዶች ለእነርሱ የማይገባቸውን ነገር፣ ሌሎች ደግሞ ከአቅማቸውና ከችሎታቸው በላይ የሆኑትን ነገሮች እንዲመሩና እንዲያስተዳድሩ ሲሰጣቸው የቤተክርስቲያን ነገር በሁሉም አቅጣጫ የተበላሸና የተምታታ ይሆናል፡፡

የክርስቶስ የሆኑት የክርስቶስን ገንዘቦች /በጎችን/ ከጠላቶች በበለጠ ያጠፋሉ፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን ቸሩ አምላክ ሳይቀስፋቸው ወደ ንስሐ ይጠራቸዋል ምስጋናና ክብር ላንተ ይሁን፤ ጌታ ሆይ በእውነት ክብር ላንተ ይሁን፤ የፍቅርህ ጥልቀት ምን ያህል ዕመቅ /የማይደረስበት/ ነው!? የትዕግሥትህ ብዛት እንዴት ታላቅ ነው! ከአንተ ስም የተነሣ ከማይታወቅበትና ከተራ ሰውነት ተነሥተው ወደ መታወቅና መከበር ቦታ የመጡ ሰዎች ያገኙትን ክብር ባከበራቸውና የክብራቸው ምክንያት የሆነውን እርሱን ለማሳዘን ማዋል፥ የተቀደሰውን ነገር ማቃለልና ማንቋሸሽ፥ ተገቢው ቅንዓትና ችሎታ ያላቸውን ማባረር፥ክፉዎች ያለ ስጋት ደስ እንዳላቸው መጠን ሁሉንም ነገር በነጻነት ሲያጠፉ ታግሰሃልና፡፡

## በሰው ፊት ስለመሾምና ተጠያቂነት

አንድ ሰው እርሱ ሳይፈልግ በሰዎች ግፊት ወይም አስገዳጅነት ሲሾም ከተጠያቂነት ነጻ ይሆናልን? የቂስ ልጅ ሳኦል ንጉሥ ለመሆን አለመፈለግ ብቻ ሳይሆን በሕልሙም አይቶ አያውቅም፡፡ ስለጠፉት አህዮቹ ለመጠየቅ ወደ ነቢዩ ሄደ፡፡ ነቢዩ ግን እንደሚነግሥ ይነግረው ጀመር፡፡ ሆኖም ከነቢዩ አንደበት ስለ መንግሥት ነገር ቢነገረውም እሰይ ብሎ ደስ ብሎት አልተመኘም፤ አልተቀበለም፡፡ «እኔ ማነኝ? የአባቴስ ቤት ምንድነው? እንዲህ ያለውን ነገር ለምን ነገርኸኝ?» አለ እንጂ፡፡ /፩ሳሙ.፱፥፳፩/፡፡

ነገር ግን በእግዚአብሔር የተሰጠውን ክብር ያለአግባብ በተጠቀመ ጊዜ ካነገሠው ከእግዚአብሔር ቁጣ ሊድን ችሏል? ሳሙኤል በገሠጸውስ ጊዜ «እኔ አንግሡኝ ብዬሃለሁን? የፈለግኹት የራሴን የብቻ ሕይወት መኖር ነበር፡፡ ነገር ግን ወደዚህ የክብር ቦታ ያመጣኸኝ ሳላስበውና ሳልፈልገው አንተ ነህ፡፡ በቀደመው በተራ ሰውነቴ ሆኜ ቢሆን ኖሮ ከእነዚህ መሰናክሎች ሁሉ በቀላሉ ማለፍ እችል ነበር፤ ከሕዝቡ አንዱ ብሆን ኖሮ ከእነዚህ መሰናክሎች ሁሉ በቀላሉ ማለፍ እችል ነበር፤ ወደዚህ ዘመቻም አልላክም ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ከአማሌቃውያን ጋር ለሚደረገው ጦርነት ሓላፊነት በእኔ ላይ አያደርግም ነበር፡፡ ሓላፊነቱ በእኔ ላይ ባይሆን ኖሮ ደግሞ ይህንን ኃጢአት ባላደረግሁ ነበር» ማለት ችሏልን?

ሆኖም ግን እንዲህ ያሉ ምክንያቶች ከቅጣት ነጻ ሊያደርጉ የማይችሉ ደካማዎች ናቸው፡፡ ደካማዎች ብቻ ሳይሆኑ ጎጂዎችና አጥፊዎችም ናቸው፤ የእግዚአብሔርን ቁጣ ያቀጣጥላሉና፡፡ በእግዚአብሔር ታላቅ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



ጽሕሙ ለአሮን [ካህን] ዘይወርድ ዲበ ሕባኔ መልበሱ

ክብር የተሰጠው ሰው የክብሩን ታላቅነት ለጥፋቱ ይቅርታ ማግኛ ለማድረግ መሞከር የለበትም፡፡ እግዚአብሔር ለእርሱ ያደረገለትን ልዩ ቸርነትና ስጦታ የበለጠ ለመሥራትና የከበረውን እርሱን ለማክበር እንደ መነሻና ምክንያት ሊጠቀምበት እንጂ፡፡

ከሌሎች የተለየ ጸጋና ክብር ስላገኘ /ይህንን/ ኃጢአት ለመሥራት ምክንያትና ለመበደል እንደ ነጻነት ማግኚያ መንገድ አድርጎ የሚያስብ ሰው የእግዚአብሔር ቸርነት ለእርሱ መተላለፍ ምክንያት እንደሆነ ለማሳየትና ለማስረዳት የሚጥር ሰው ድርጊት ነው፡፡ እኛ ግን በአስተሳሰብም፣ በንግግርም፣ በሁሉም ስላደረገልን ሁሉ የበለጠ ልናከብረው ይገባናል፡፡

ከመንግሥት ሥልጣን ወደ ክህነት ስናመራ ዔሊ የሊቀ ካህናትነቱን ሥልጣን ፈልጎ አላገኘም፡፡ ነገር ግን በበደለ ጊዜ ይህ ምን ጠቀመው? አልፈልግም ማለት እንኳ አይችልም ነበር፡፡ ምክንያቱም የመቀበል ሕጋዊ ግዴታ ነበረበትና፡፡ ከሌዊ ነገድ በመሆኑ ከቀደሙት አባቶቹ የወረደውን ክህነት መቀበል ነበረበት፡፡ እንዲህ ሆኖም ግን ስለ ልጆቹ በደል ቀላል ቅጣትን አልተቀበለም፡፡

እርሱን በተመለከተ እግዚአብሔር ለሙሴ ብዙ ነገር የተናገረለት የመጀመሪያው የአይሁድ ሊቀ ካህናት (አሮን) በወንድሙ ምልጃ የእግዚአብሔር ቁጣ ባይመለስለት ኖሮ የሕዝቡን እብደት ብቻውን መቋቋም ባልቻለ ጊዜ ሊጠፋ ትንሽ ቀርቶት አልነበረምን? /ዘጸ.፴፪፥፲-፲፩/፡፡

ሙሴስ ራሱ እስራኤላውያንን የመምራትን ነገር አለመፈለግ ብቻ ሳይሆን «ጌታ ሆይ በምትልከው ሰው እጅ ትልክ ዘንድ እለምንሃለሁ» እስከማለት ደርሶ ነበር፡፡ /ዘጸ.፬፥፲፫/ እግዚአብሔር ራሱ ይህን ሓላፊነት እንዲሸከም ሲጠራው ይቅርብኝ እስከማለት የደረሰው እርሱ፥ በመሪባ ውኃ በበደለ ጊዜ በተደጋጋሚ ተወኝ እያለ መናገሩ ምክንያት ሆኖ ሊያድነው ቻለን? በእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታ አስገኘለትን? /ዘጸ.፳፥፲፪/፡፡ የተስፋይቱን ምድር ሳያይ ለምን ቀረ? ስለዚህ ምክንያት አይደለምን? እርሱ የመራቸው ሰዎች የገቡባትን ምድር ስለዚህ ምክንያት እርሱ ሳይገባባት ቀረ፡፡ ከብዙ ድካምና መከራ፣ የበረሃ መንከራተት፣ የመንገድ ላይ ጦርነቶችና ድሎች በኋላ ያን ሁሉ መከራና ድካም ወደ እርሷ ለመግባት ብሎ ከተቀበለላት ከነዓን ሳይደርስ በመንገድ ቀረ፡፡

በሓላፊነታቸው ባሚፈጽሙት ኃጢአት የሚጠየቁት ክህነትን ራሳቸው ፈልገውና ሽተው ገንዘብ የሚያደርጉት ብቻ ሳይሆኑ በሌሎች ጽኑ ፍላጎትና ግፊት የሚመጡትም መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ በራሱ በእግዚአብሔር ለዚህ ታላቅ ሥራ የተመረጡት እንኳ እንዲህ ከባድ ቅጣት ከተቀበሉ /ከከፈሉ/፤ አሮንን ዔሊንና፥ ታላቁን ሊቀ ነቢያት ሙሴን ከዚህ ቅጣት የታደጋቸው ምንም ነገር ከሌለ እኛን ታዲያ ሌላ ምን ሊያድነን ይችላል?

እግዚአብሔር ይሁዳን መረጠው፤ ከቅዱሳን ሐዋርያቱ ጋር ቆጠረው፤ እንደሌሎቹ ሁሉ የሐዋርያነትን ክብርና ሥልጣን ሰጠው፤ ከሌሎቹም አለፍ ያለ ሰጠው፡፡ /ገንዘብ ጠባቂ ነበርና ዮሐ.፲፪፥፮/ ኋላስ? ይህንን የተሰጠውን ነገር ያለአግባብ በተጠቀመ ጊዜ፦ ሊሰብክለት የጠራውን በመካድ እና በአግባቡ ሊጠቀምበት የሚገባውን ገንዘብ አለአግባብ በማባላሸት በበደለ ጊዜ ከጥፋት አመለጠን? እንዲያውም ስለዚህ ምክንያት በራሱ ላይ ከባድና ተገቢ የሆነ ቅጣትን አመጣ፡፡ በእግዚአብሔር የተሰጠንን ታላቅ ክብር እርሱን ለማሳዘን ልንጠቀምበት አይገባምና፥ እርሱን በተሻለ ሁኔታ ለማስደሰት እንጂ፡፡ መልካም ተደርጎለትም ጥሩ የማይሆን ሰው የከፋ ቅጣት ይገባዋልና፡፡ የማይችል ሰው ሌሎች ሰዎች ቢለምኑትና ቢማልዱትም ቦታ ሊሰጣቸው አይገባም፡፡ ከሁሉም አስቀድሞ የራሱን ኅሊና ሊመረምርና ነገሩን ሁሉ በጥሞና ሊመዝን ይገባዋል፡፡

መሐንዲስ ያልሆነ ሰው የቤትን ግንባታ ሥራ ለመሥራት ሓላፊነት አይወስድም፡፡ ችሎታ ያለው ሐኪም ካልሆነም በስተቀር የታመመን ሰው ለማከም አይሞክርም፡፡ ምንም ያህል ብዙዎች ቢለምኑትና ቢገፋፋትም እንኳ አለማወቁንና አለመቻሉን ለመግለጽና አይሆንልኝም ለማለት አያፍርም፡፡ ታዲያ ይህ እንዲህ ከሆነ የብዙዎች ነፍሳት አደራ በእርሱ ላይ የሚሆነው እርሱ ከሁሉ አስቀድሞ ራሱን ይመረምር ዘንድ አይገባውምን? ምንም ልምድና ችሎታ የሌለው ቢሆንም እንኳ እገሌ ስላዘዘው ወይም ሌላው ስላስገደደው ወይንም ሌላውን ሰው ላለማስቀየም ሲል የክህነትን አገልግሎት ይቀበላልን? እንዲህ ከሆነስ ከእነርሱ ጋር አብሮ ተያይዞ ግልጽ ወደ ሆነ ጥፋት ከመውደቅ እንዴት ሊያመልጥ ይችላል? በፊት እንደነበረው ቀጥሎ ቢሆን ኖሮ ሊድን ይችል ነበር፤ አሁን ግን በራሱ ጥፋት ውስጥ ሌሎችንም አብሮ ይዞ ይጠፋል፡፡ ያን ጊዜ ለእርሱ ማን ይቆምለታል? እንዴት ከቅጣት ያመልጣል? ወደ ክህነት የሚገፋፉንና የሚያስገድዱን ናቸው? በዚያን ጊዜ እነርሱን ራሳቸውንስ ማን ያድናቸዋል? እነርሱ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከእሳት ያመልጡ ዘንድ ስለ እነርሱ ስለ ራሳቸው የሚቆምላቸው ያስፈልጋቸዋልና።

ሐዋርያው ለደቀ መዝሙሩ የሚለውን እናዳምጥ፤ «በማንም ላይ ፈጥነህ እጆችህን አትጫን፥ በሌሎችም ኃጢአት አትተባበር» /፩ ጢሞ. ፭፥፳፪/። ሳያጣራ፤ የሚቻለውን ያህል ማወቅና መመርመር ያለበትን ሳያደርግ እንዲሁ በዘፈቀደ ክህነት የሚሰጥ በሌሎች ኃጢአት ተባባሪ ነው። ለሚቀበሉትም «እኔ ፈልጌ አልተቀበልሁም፤ ተውኝ ብላቸው እምቢ ብለው በግድ ሾሙኝ።» ማለት ነጻ ሊያደርጋቸው እንደማይችል ሁሉ ለሚሾሟቸውም የሾሙት እርሱ ማን መሆኑን አላወቅነውም ማለት በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም። የሾሙት ማን መሆኑን አለማወቃቸው ጥፋታቸውንና በደላቸውን የበለጠ ከባድ ያደርግባቸዋል። ማምለጫ ይሆነናል የሚሉት የራስ ሐሳብም የበለጠ ጥፋታቸውን ያከብድባቸዋል።

ዕቃ የሚገዙ ሰዎች ብዙ ተጨንቀው፥ አጣርተው፥ አውጥተው አውርደው እንጂ እንዲሁ ምንነቱን የማያውቁትን ዕቃ አይገዙም። እንዲህ ብዙ ነገር አጣርተውም የተወሰነ የሙከራ ጊዜ እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ። ለዚህ ታላቅ ሓላፊነትና ሥራ ሰዎችን የሚመርጡና የሚሾሙ ግን ምስክርነታቸውንና ፈቃዳቸውን እንዲሁ በግዴ ለሽነትና እንደ ቀላል ነገር በማየት ብዙም ሳይጨነቁና ጥብቅ ማጣራት ሳያደርጉ እንዲሁ አንዱ ስለ ፈለገ ብቻ ወይም እርሱን ለማስደሰትና ወዳጅ ለማድረግ ወይም የሆነን ሰው ላለማስቀየም ሲሉ ብቻ ያደርጉታል።

ታዲያ ስለእኛ ሊያማልዱ የሚገባቸው ራሳቸው በዕዳ ተይዘው ተከሰው የሚቆሙ ከሆነ ስለእኛ ማን ይጸልይልናል? ስለዚህ ክህነትን የሚሰጥ (የሚሾም) ሰው ጥብቅና ጥንቁቅ ሐተታና ምርመራ ሊያደርግ ይገባዋል፤ የሚቀበለው ደግሞ እጅግ የበለጠውን ሊያደርግ ይገባዋል።

የሚሾሙት /ተቀባዮቹ/ በእርሱ ቅጣት ቢሳተፉም /ቢተላለፉ ለሚፈጽመው በደል/ እርሱ ግን ከእነርሱ የበለጠ ዋና ውን ቅጣት የሚቀ በለው እርሱ ነው። እንደማይበቃ እያወቀት በተለየ ሰበብና ሽፋን ቢሾሙት የእነርሱ ቅጣት ከእርሱ ጋር እኩል ነው። እንዲያውም የበለጠም ሳይሆን አይቀርም። ቤተክርስቲያንን ለማ ጥፋት ኅሊናው ላዘነበለ ሰው ሥልጣን የሚሰጥ ሰው ያ ሰው ለሚፈጽመው ጥፋት ሁሉ ተጠያቂ ነው። ነገር ግን ባለማወቅ በሰዎቹ አስተያየት ተታልሎ የሾመው ከሆነ ግን ሙሉ በሙሉ ከተጠያቂነት /ከቅጣት/ ባያመልጥም ቅጣቱ ከተሿሚው ቀለል ያለ ይሆናል።

የሚሾመው /የሚመርጡት/ በተሳሳተ መረጃ ተሳስተው ሊሆን ይችላል። የሚሾመውና የሚመረጠው ግን «እኔ ራሴን አላውቅም» ሊል አይችልም። ስለዚህ ሌሎች ባለማወቅ ተሳስተው ሲያስገድዱትና ሊገፋፉት ቢነሡም እርሱ ግን ራሱን በሚገባ በመመርመርና በማወቅ ነገሩን በሚገባ ሊያስረዳቸውና የበለጠ እንዳይሳሳቱ ሊያደረጋቸው ይገባል።

በዚህ ዓለም የሥራ መስክ ገበሬ መርከብ ለመንዳት አውሮፕላን ለማብረር አይነሣም። ሙያው መርከብ ነጂ የሆነ ሰው ጦር እንዲመራ ቢጎተጎትም /ቢገደድም/ እሺ አይልም። እያንዳንዱ ያለ ችሎታው ቢሰማራ የሚከተለውን አደጋ አስቀድሞ ያያልና። ጥፋቱ ቁሳ ቁስና ንብረት በሚሆንበት ሁኔታ አስቀድ መን ብዙ የምናስብና ግፊትና ግዴታን የማንቀበል ሲሆን ክህነትን እንዴት እንደሚይዙትና እንደሚያገለግሉበት ለማያወቁ ቅጣቱ ዘለዓለማዊ በሆነበት ሁኔታ ግን ያለብዙ ማሰብና ማሰላሰል እንዲሁ በዘፈቀደ ወደዚህ ዓይነት ታላቅ አደጋ ውስጥ ዘለን እንገባለን? ለምሳሌ አንድ ሰው የቤት ሥራ ሙያ ሳይኖረው ብትሠራልን ስንለው እሺ ብሎ ቢመጣና እንጨቱንና ድንጋዩን ቢያበላሽና የሠራው ነገር ወዲያውኑ ተበታትኖ ቢወድቅ በራሱ ፈልጎ አለመምጣቱና በሌሎች ግፊት ሥራውን መጀመሩ በቂ ምክንያት ይሆነዋል? በጭራሽ።

የሌሎችን ግፊትና ጥሪ አልቀበልም ማለት ነበረበትና በርግጥም ተጠያቂ ነው። እንዲህ እንጨትና ድንጋይ ለሚያበላሽ ሰው በጥፋቱ ከመጠየቅና ከመቀጣት ምንም ምክንያት የለውም። ነፍሳትን የሚያጠፋ፤ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በግዴለሽነት የሚያንጽ፤ የሌሎች ግፊትና ማስገደድ በቂ ምክንያት ይሆነኛል ብሎ ሊያስብ ይገባዋልን? ይህ ሞኝነት አይደለምን?

*በዚህ ዓለም የሥራ መስክ ገበሬ መርከብ ለመንዳት አውሮፕላን ለማብረር አይነሣም። ሙያው መርከብ ነጂ የሆነ ሰው ጦር እንዲመራ ቢጎተጎትም /ቢገደድም/ እሺ አይልም። እያንዳንዱ ያለ ችሎታው ቢሰማራ የሚከተለውን አደጋ አስቀድሞ ያያልና። ጥፋቱ ቁሳቁስና ንብረት በሚሆንበት ሁኔታ አስቀድመን ብዙ የምናስብና ግፊትና ግዴታን የማንቀበል ሲሆን ክህነትን እንዴት እንደሚይዙትና እንደሚያገለግሉበት ለማያወቁ ቅጣቱ ዘለዓለማዊ በሆነበት ሁኔታ ግን ያለብዙ ማሰብና ማሰላሰል እንዲሁ በዘፈቀደ ወደዚህ ዓይነት ታላቅ አደጋ ውስጥ ዘለን እንገባለን?*

ፈቃደኛ ያልሆነን ሰው በርግጥም ማንም ሊያስገድደው አይችልም። የማትችል መሆንህን ካወቅህ ጥሩ፤ ታዲያ ማንም ሰው ባልማ ለደህና ባላስገደደህ ጊዜ የማትችልና ደካማ ነበርክ። ታዲያ ለዚህ ክብር ሲጋብዙህ በድንገት በተአምራት ብቁ ሆነህ ተገኘህ? ስለዚህ ምክንያት ጌታችን ግንብ ሊሠራ የሚፈልግውን ሰው ለመሥራት አቅም እንዳለው ሳያረጋግጥ መሠረቱን እንዳይጀምር መከረ፤ መሳቂያና መሳለቂያ እንዳይሆን። በዚህስ ቅጣቱ መሳቂያ መሆን ነው፤ በዚያ ግን የማይሞት ትልና የማይጠፋ እሳት ነው። /ኢሳ ፷፮፥፳፬/። ዕድል ፈንታው ጥርስ ማፋጨትና በውጭ ያለው ጨለማ፣ ከሁለት መሰንጠቅና ከግብዞችና ከከፋዎች ጋር መሆን ነው።❖

ይቆየን።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

## መስቀል አብርሃ

ከጌታችን ዘጠኙ ዐበይት በዓላት አንዱ የመስቀል በዓል ነው:: በዓሉ የሚከበረው መስከረም ፲፯ ቀን ነው:: ጌታችን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ፣ ሞቶም ከተነሣ በኋላ ሕሙማን መስቀሉን እየዳሰሱ፣ በመ ስቀሉ እየታሹ ከደዌያቸው ይፈወሱ ነበር:: በእነዚህም ተአምራት እየ ተሳቡ ብዙዎች ክርስቲያኖች ሆኑ:: ይህንን ያዩ አይሁድ መስቀሉን በአንድ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታ ጣሉት:: በየቀኑ የአካባቢው ነዋሪ ሁሉ ቆሻሻ ስለሚጥልበት ቦታው እንደ ጉብታ ሆነ:: በኋላም በጥጦስ ወረራ ክርስቲያኖቹ ኢየሩሳሌምን ለቀው ስለወጡ፤ የከተማዋም መልክ ስለተለወጠ መስቀሉ የተዳፈነበት ቦታ ወዴት እንደሆነ ለማወቅ አል ተቻለም:: በዚህም ምክንያት ከሦስት መቶ ዓመት በላይ ተዳፍኖ ቆይቷል::

በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን /፫፻፳፯ ዓ.ም/ የንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እናት ንግሥት እሌኒ ይህን ታሪክ ትሰማ ስለነበር አስቆፍራ ለማስ ወጣት ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘች:: እዚያም ደርሳ ጉብታ የሆነውን ሁሉ ብታስቆፍር መስቀሉ ያለበትን ቦታ አላገኘችም:: ሰውም ብትጠይቅ የሚያውቅ አላገኘችም:: በመጨረሻ ግን የመስቀሉ መውጣት የእግዚአ ብሔር ፈቃዱ ነበርና፤ ኪራኮስ የሚባል አንድ አረጋዊ የእሌኒን ድካም አይቶ «በከንቱ አትድከሚ፤ እንጨት አሰብስበሽ፤ ከምረሽ፤ ዕጣን አፍሺ በት:: በእሳትም አያይዢው የዕጣኑ ጢስ ወደላይ ወጥቶ ወደታች ሲመ ለስ አቅጣጫውን አይተሽ አስቆፍሪው» አላት:: እሷም ያላትን ሁሉ አደረገች:: የዕጣኑ ጢስ ወደ ላይ ወጥቶ ወደታች ሲመለስ መስቀሉ ያለበትን ቦታ በጣት ጠቅሶ እንደማሳየት ያህል አሳያት:: ምልክቱን ይዛ አስቆፍራ መስቀሉን መጋቢት ፲ ቀን አውጥታዋለች:: ነገር ግን መጋቢት ፲ ቀን በዐቢይ ጾም የሚውል በመሆኑ መስከረም ፲፮ ቀን ቁፋሮ የተጀመረበት ከተገኘም በኋላ ቅዳሴ ቤት የተከበረበት መስከረም ፲፯ ቀን በዓል እንዲሆን ተወሰነ:: በዓሉንም በመላው ዓለም የሚገኙ ክር ስቲያኖች በድምቀት ያከብሩታል::

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም በቀኖናዋ ሰፍራ፣ ቆጥራ እንዳስተማረ ችው መስከረም ፲፮ ሕዝበ ክርስቲያኑ በየአጥቢያው በየቤቱ ችቦውን እንጨቱን እያመጣ ይደምራል:: ካህናቱም በደመራው ፊት ለፊት ጸሎት አድርሰው «መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሰርገወ ሰማየ እም ኵሉሰ ፀሐየ አርአየ» እያሉ ደመራውን ይዞራሉ:: ቀጥሎም ሕዝቡ «ኢዮሃ አበባዬ መስከረም ጠባዬ» እያሉ በደ መራው ዙሪያ ይጨፍራሉ:: ደመራው በመባረኩም በዕለቱ ማታውንና ቀሪዎቹ ደግሞ ሌሊቱን በማቀጣጠል ያስቡታል:: በነጋው በ፲፯ም የመስቀል በዓል ይከበራል:: ማኅሌቱ፣ ቅዳሴው፣ ጸሎቱና ውዳሴውም አይታጐልም:: ሕዝቡም ሁሉ በዓሉን በደስታ፣ በፍስሐ ያከብራሉ::

*/አባ ጎርጎርዮስ፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በኢትዮጵያ፤ ገጽ.፻፲፭/*

### ብሂለ አበው

- «ቅዱሳት መጻሕፍትን አለማወቅ በአዘቅትና በጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ መኖር ነው» */አባ ኤጲፋንዮስ/*
- «ታዛዥነትና ተዐቅቦ በአንድነት ሲገኙ ሰውን በአራዊት ላይ ሥልጣን ይሰጡታል::» */አባ እንጦንስ/*
- «ጸሎት የትካዜና የውስጣዊ ሐዘን ማስታገሻ ነው» */አባ ኔላስ/*
- «ጠላት በበዛበት ቦታ የምንኖር ከሆነ ብርቱ ወታደር እሆናለሁ» */አባ ጴሜን/*

### ቀና በል ቀን አለ

የነበረው ሞቶ አዲስ ይወለዳል፣
ችግርም መከራም ስቃይ ሁሉ ያልፋል፣
ምን የማያልፍ አለ ሁሉም ነገር ያልፋል::
ሽንፈትህ ቢነገር ውድቀትህ ቢወራ፤
ስተትህ ቢተረክ ገዝፎ እንደ ተራራ፤
ተዋርዶም ተንቆም ሰው መሆን ስላለ፣
አንገትህን አትድፋ ቀና በል ቀን አለ::

*ታሪኩ ሺፈራው*

## ለኔ ነው እንባ የሚያሻው
## /ቁጥር ፩/

አባት አያቶቼ በክብር
ከጉዲት፣ ከግራኝ ተናንቀው፣
የሱስኒዮስን የግፍ ስለት
ርሃብና ጥሙን ታግሰው፤
የበረሃው ቆንጥር ከገላቸው
ሱፋጭ 'የተሰካ በእግራቸው፣
ደማቸው ተዘርቶ በየፈፋው
ተቦጭቆ እየቀረ ሥጋቸው፤
ያቆዩትን ርስት መንፈሳዊ
በወጉ መጠበቅ አቅቶኝ፣
እንቁዬን ለእሪያ አቅርቤ
መርገም በእጄ ለጨበጥኩኝ፣
የፍፃሜውን ደወል ድምፅ
የመለከቱን ጥሪ ሳልሰማሁኝ፤
በቅዱሳን ጸሎት እሳት
የታጠረች አገር ይገፔ፣
ውስጧ 'ሲፈርስ' ባለማየት
ለተቀመጠኩኝ ደንዝገፔ፤
ለኔ ነው እንባ የሚያሻው
ከልቦና የሚያስታርቅ፣
ዶሮ ሲጮህ ሦስት ጊዜ!!!
ጊዜው ደርሶ የትንቢት ቃል
መፈጸሙን የሚያሳውቅ::
ፊደል ቆርሰው፣ ፊደል ገድፈው
ሊያሳንሱኝ ሲጣጣሩ፣
መስቀል፣ ፅና፣ ብራናውን
እየሸጡ አልባሳቱን ሲያሳጥሩ፤
የአያቶቼን ርስት ደፍረው
ገዳማቱን ሲያቃጥሉ፣
ታሪኬ ላይ ታሪክ ጥፈው
ብርዝ ታሪክ ይብቀል ሲሉ፤
መንታ ምላስ መርዝ ታጥቀው
ያጐረሰ እጅ ነክሰው፣
እንደ ራበው ክፉ አንበሳ
ሲያጋሱብኝ ዙሪያ ከበው፤
ለኔ እንጅ እንባ 'ሚያሻው !!!
አረም ሲውጠው ማሳዬን
ዛሬም ጎልያዶች ሲነሡ፣
«አሐዱ ...» ሳልል እኔ
«እትው ...» ሲሉ እነሱ::
በለስ ስትረዝም አቆጥቁጣ
የቁም እንቅልፍ ለተኛሁኝ፣
ታሪክ ሲበርዝ!
ደብር ሲነድ!!
ለምን ብዬ ሳልጠየኩኝ::

*አንዱዓለም አባተ*
*አዲስ አበባ*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «ጡቶችሽም የወይን ዘለላ ይመስላሉ»

መኃ.፯÷፰

## አዲሱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ጠቀሜታው ምንድን ነው?

*ዲ/ን ብርሃኑ አድማስ*

መፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞን ከተለዩት ሁሉ የተለየ /መኃልየ መኃልይ/ በተባለ የመዝሙሩ ክፍል እግዚአብሔርንና እርሱ የመረጣቸውን በልዩ ምሳሌዎች እየመሰለ «የተለየ» የተባለ ምስጋናውን አቅርቧል። ነቢዩ በዚህ ምስጋናው ከፍተኛ ሥፍራ ሰጥቶ የሚያወሳው «የአምላክን ሰው መሆን» በመሆኑ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፈጽሞ አመስግኗል። የመኃልየ መኃልይን ምስጋና ከዚህ ታላቅ ጉዳይ አውጥቶ መረዳትም በእጅጉ አስቸጋሪ ነው። ከዚህም ጋር መድኃኔዓለም ክርስቶስ ሰው ሆኖ ስለሚገለጥባት ስለቅድስት ድንግል ማርያም፣ ስለቤተ እስራኤል /አቅሌስያ/ እና ስለሐዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን በሰፊው ተናግሯል።

«ጡቶችሽም የወይን ዘለላ ይመስላሉ» የሚላትም ምሳሌዋን ቤተ እስራኤልንና አማናዊቷን የሐዲስ ኪዳኗን ቤተ ክርስቲያን ነው። «ጡቶችሽ» የሚላቸውም ለቤተ እስራኤል ሁለቱን ጽላቶች ሲሆን ለቤተ ክርስቲያን ደግሞ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳንን ነው። ሌላውን ትንታኔ ለጊዜው አቆይተን ወደ እኛ ዋና ጉዳይ ስንመለስ በሁለት ጡቶች የተመሰሉት ሁለቱ ኪዳናት እንደገና «የወይን ዘለላ ይመስላሉ» ተብለው የምሳሌ ምሳሌም ተሰጥቷቸዋል።

ከጡት የሚገኘው ወተት ነው። እግዚአብሔር ለነሙሴ ለነ ኢያሱ «ማርና ወተት» የምታፈስው ምድር ሲል የጠራትም የኦሪት እና የወንጌል መገኛ መሆኗን ለመናገር ነበር። ማር የኦሪት፣ ወተት ደግሞ የወንጌል ምሳሌዎች ነበሩና። ኦሪትን ሲታጠቡት በሚለቀው በማር የመሰላት በወንጌል የምትተካ መሆኗን ለመግለጽ ሲሆን ወተትና የወተት ውጤት የሆነው ቅቤ የነካው ልብስ ቢያጥቡት እንደማይለቀው ወንጌልም የማትለቅ ወይም የማትተካ መሆኗን ነግሮናል። እንዲህ እያለ የገለጻትን ቤተ ክርስቲያን አሁን ደግሞ ሁለቱ ኪዳናትሽ እንደ ወይን ዘለላ የሚወደድ፣ የማይጠገብ፣ ለምግበ ሥጋ ለምግበ ነፍስ የሚሆን የምስጢር ምግብ ናቸው፤ ይላታል።

የወይን ዘለላ ገና ሲያዩት ያስደስታል፤ ያስጐመጃልም። ይህ የሚሆነው ደግሞ በውስጡ አምቆ ስለያዘው «ወለላ» ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትም እንዲሁ ናቸው። ንባባቸውን ሲሰሙት ገና ያጠግባሉ፤ ደስ ያሰኛሉ። ትርጓሜያቸው፣ ምስጢራቸውና ርቃቂያቸው ደግሞ ልክ የወይን ዘለላ ውስጥ እንደታመቀ ወለላ ነው። ወለላው ሽፋኑ ሲነሣ እንደሚገኘው የቅዱሳት መጻሕፍትን «ወለላም» ከንባቡ አልፎ ወደ ትርጓሜው ካልገቡ አያገኙትም። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያንን ጡቶችሽ /ሁለቱ ኪዳናትሽ/ በመጻሕፍቶችሽ እንደ ወይን ዘለላ የነፍስ ምግብ ብቻ ሳይሆን ለሥጋዊ ሕይወታችንም መመሪያና ሕይወት የሆነውን የምስጢር ወለላ የሚመግቡን ናቸው እያልን ከሰሎሞን ጋር እናመሰግናታለን።

ወለላዋን የምንመገብበት ዋናው መንገድ ደግሞ የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ነው። መጻሕፍት በተለያዩ ቋንቋዎች ካልተተረጐሙና በየሕዝቡና በየነገዱ ቋንቋ ሁሉ እግዚአብሔር ካልተመሰገነ ያ የወይን ዘለላ ወዴት አለ? በዚህ ጽሑፍም ይህን ቃል መነሻ ያደረግነው ለዚሁ ነው። ትክክለኛ ትርጓሜ የወይን ዘለላውን ሰጥቶ መመገብ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያናችንም ለሕዝቡ ሁሉ በሚደርስ መንገድ አዘጋጅታ በማቅረቧ እናታችን ሆይ ጡትሽን አጥብተሽናል፤ የወይን ዘለላውንም መግበሽናል ለማለት ነው። ይሁን እንጂ ይህን ጉዳይ በድፍኑ ብቻ ልንተወው ስለማንችል ወደ ዝርዝር ቅኝቱ /ሥነ ጽሑፋዊ/ ገብተናል።

በዚሁ መሠረት ባለፈው እትማችን ስለ ትርጉም ምንነትና ስለሞያው አስፈላጊነት አውስተን ትርጉም በኢትዮጵያ ስላለው ታሪክም ቅንጫቢ ነገር አቅርበን ነበር። በዚህ እትማችን በግንባር ቀደምነት የምናየው ባለፈው ከጠይቅናቸው ጥያቄዎች አንዱን ብቻ ቢሆንም በሀገራችን ቅዱሳት መጻሕፍትን በቋንቋችን ስላገኘንበት ጊዜ ትንሽ ተጨማሪ መረጃ መስጠትን እናስቀድማለን።

ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ግእዝ መተርጐም የጀመሩበት ጊዜ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ እንደ ነበርና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትም ቢሆኑ ከሦስተኛውና ከዐራተኛው ክፍለ ዘመን ሳይዘገዩ እንደገቡ ባለፈው ዕትም ጠቁመን ነበር። አንዳንድ ዘመናዊ ምሁራን ግን ይህን ጊዜ ለማወቅ በሚያደርጉት ፍለጋ ውስጥ ተጨባጭ ማስረጃ ባለማግኘታቸው ምክንያት የሐዲስ ኪዳኑን ቀርቶ የብሉይ ኪዳኑን ትርጓሜም «ከክርስቶስ ልደት በኋላ ነው» እያሉ ሲከራከሩ ይደመጣሉ።

ለእኛ ቤተ ክርስቲያን ሥራዎች በጉልህ አለመታወቅ ሁለት ፈተናዎችን ማቅረብ ይቻል ይሆናል። የመጀመሪያው በዮዲት ጉዲት ዘመን እስከዚያ ዘመን /እስከ ዘጠነኛው ክ/ዘመን/ የነበረን መረጃ ሁሉ በዚያ የ፵ ዓመት ጦርነት፣ የአብያተ ክርስቲያናትና የገዳማት መቃጠል የክርስትናችንንና ከዚሁ ጋር የሚነሡ መረጃዎችን ማጣታችን ነው። ከዚህ የተረፉትም በኋላ በግራኝ መሐመድ መጥፋታቸው ለአሁኑ ጊዜ ምርምር መረጃ እንዳይገኝ አድርጐታል ማለት ይቻላል። ሁለተኛው ደግሞ አሁን ያለው ትውልድ በሚቀበለው መንገድ ሀገራችን የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ለመሥራት የጀመረችበት ጊዜ አሁንም እኛ ያለንበት ክፍለ ዘመን መሆኑ ነው። ከዚህ ጋር ድህነታችንና ዓለም አሁን ለእኛ ባለው አመለካከትና አቀባበል የድሮውንም ጭምር እያጣመምን መረዳታችን ሌላው ትልቁ ዕንቅፋታችን ሆኖአል። ይህ ጉዳይማ እንዲያውም አለፍ ብሎ «ምሁር ለመሆን የራስን ማናናቅ መገለጫው ነው» የተባለ እስኪመስል ድረስ ለዘመናዊ ሰዎቻችን ፈተና ሆኖባቸዋል።

የመቀሌ ዩኒቨርስቲ የአንትሮፖሎጂ መምህርና ተመራማሪ ቀለመወርቅ ተፈሪ ሉላዊነትና የባህል ለውጥ /Globalization and Cultural Change/ በሚለው ጥናታዊ ሥራቸው «የዘመናችን ዐቢይ ክስተት በሆነው ሉላዊነት አፍሪካ በቀል የሆኑ አስተሳሰቦች፣ ባህሎች፣ መለኪያ ሥርዓቶች ... እየተናዱ ነው» እንዳሉት የእኛ የሀገር በቀል ሊቃውንት ዕውቀትም እየተጣለ ያለ ይመስላል። እንደ ምሁሩ ጥናት በርግጥም የአፍሪካ ሕዝብ ቀስ በቀስ የራሱን ተጨባጭ እውነታም በምዕራባውያን አመለካከት እንዲያይ እየተማረ ነው፤ (Indeed, the African people are gradually learning to see their own objective realities through western glasses / The Ethiopian Herald, vol. Lvlll, No. 138, yekatit 10, 1994, Art and culture) እንደተባለው ብዙዎቹ የእኛ ዘመናዊ ምሁራን የሀገራቸው ዕውቀትን ለመጠቀም ሲያዘንብሉ አይታዩም። ሀገር በቀል ዕውቀትን በዘመናዊ የጥናት መስፈርት ለመደገፍና ለዓለም ለማስተዋወቅ ከመጣርም ሌሎች ስለእኛ ቀነጫጭበው ያሉትን ሲያቀርቡ ደስ ይላቸዋል። ይህ ደግሞ በዘመናት ለተሰናዱት የእኛ ዕውቀቶች የሞት ያህል አስደንጋጭ ነው። ለማንኛውም ዋና ጉዳዩ ይህ ስላልሆነ ከዚህ ወጥቼ ወደ ዋናው ጉዳይ ልመለስ፤ ነገር ግን ጉዳዩን ያነሣሁት የውጭ ሀገር ምንጭ ለሚያስደስታቸው ሰዎች አንድ መረጃ ጨምሮ ለማለፍ ስለነበረ እርሱን ላስቀድም።

ስለቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ታሪክ ከተናገሩት ውስጥ ሦስት ሊቃውንት ተደጋግመው ይነሣሉ። ከሦስተኛው እስከ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩት ሊቃውንት





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ውስጥ ሐሳባቸውንና ዕውቀታቸውን በጽሑፍ በማስፈረም ትተው ካለፉት ውስጥ ቅዱስ አውግስጢኖስ /፫፻፶፬-፬፻፴/፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ /፫፻፵፯-፬፻፯/ እና ታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ /፪፻፷፫-፫፻፴፱/ ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ናቸው:: በዚሁ መሠረት ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ቅዱስ አውግስጢኖስ «Christ» በተባለ መጽሐፉ አምስተኛ ምዕራፍ ላይ ቅዱሳት መጻሕፍት በዘመኑ ወደ ሰው ሁሉ ቋንቋዎች መተርጐማቸውን መስክሯል:: አውሳብዮስም እንደ እርሱው ሁሉ በድፍኑ «ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ሁሉም ቋንቋዎች ተተርጉመዋል፤ በግሪኮች፣ በበርበሮች እና በዓለሙ ሁሉ» ሲል ተናግሯል:: /De prae parat, Evangel, xii.1/ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ግን ለይቶ የተናገረላቸው አሉ:: «ሶርያዎች፣ ግብጾች፣ ሕንዶች፣ ፋርሶች፣ ኢትዮጵያውያኖች እና ሌሎች ብዙ ሀገሮች ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ ራሳቸው ቋንቋዎች ተርጉመዋል» ሲል ምስክርነቱን ሰጥቷል:: /Hom.i, in Joan/ ቅዱስ አውግስጢኖስ ይህን ሲያጠናክርም «መለኮታውያን መጻሕፍት ወደ ሰው ሁሉ እጅ ደርሰዋል» ብሏል:: /Letter ccxxxii. vol. ii, p.446, clark's ed./ እነዚህን መረጃዎች መሠረት አድርገን ወደ እኛ ሀገር ሊቃውንት ጽሑፎች /ባለፈው ዕትም ላይ የተገለጹት/ ስንመጣ በእኛ ሀገር ቅዱሳት መጻሕፍት የተተረጐሙት ከዘጠኙ ቅዱሳን መምጣት በፊት መሆኑን በርግጠኝነት መናገር ይቻላል:: ምክንያቱም ከላይ የተጠቀሱት አበው በሙሉ የነበሩት ከጉባኤ ኬልቄዶን በፊት ነውና:: በጣም የሚያስገርመው ደግሞ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በመንበሩ በቁስ ጥንጥንያ ሆኖ ስለ ኢትዮጵያ የነበረው ዕውቀት ነው:: በርግጥ በዚያ ዘመን ኢትዮጵያ ከቀይ ባሕር ማዶ ግዛት ያላትና ጊዜውም ኢትዮጵያን ከመካከለኛው ምሥራቅ ለያይቷት የቀረው እስልምና ከመፈጠሩ በፊት ስለነበረ ላያስደንቅ ቢችልም ያን ጊዜ የነበረንበትን ደረጃ ግን በጥሩ ሁኔታ ይጠቁማል:: የእኛ ችግር ያንን ጊዜ በአሁኑ ግንኙነት ላይ ተመሥርተን መተንተናችን ሳይሆን አይቀርም:: ይህም ሆኖ ግን የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ዘመንና ከእርሱ በፊት መሆኑ በዚያ ዘመን እንኳ የታወቀ ነበር ማለት ነው:: ስለ ትርጉም ታሪካችን ይህን ያህል ከጠቆምን ወደዚህ ዕትም ሥራችን እንመለስ::

*ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ግን ለይቶ የተናገረላቸው አሉ:: «ሶርያዎች፣ ግብጾች፣ ሕንዶች፣ ፋርሶች፣ ኢትዮጵያውያኖች እና ሌሎች ብዙ ሀገሮች ቅዱሳት መጻሕ ፍትን ወደ ራሳቸው ቋንቋዎች ተርጉመዋል» ሲል ምስክርነቱን ሰጥቷል:: ... በእኛ ሀገር ቅዱሳት መጻሕፍት የተተረጐሙት ከዘጠኙ ቅዱሳን መምጣት በፊት መሆኑን በርግጠኝነት መናገር ይቻላል::*

### የአዲሱ ትርጉም አስፈላጊነት

የአዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ አስፈላጊነትን በተመለከተ በራሱ በዚሁ በታተመው መጽሐፍ ቅዱስ መግቢያ ላይ የሚከተሉት ሁለት ምክንያቶች ተቀምጠዋል::

፩. የመጀመሪያው ትርጉም በግእዙ መሠረትነት የተተረጐመ ባለመሆኑ ከግእዙ ዘርዕና ከሰባ ሊቃናቱ ዘርዕ ጋር ብዙ ልዩነት ስለሚያሳይ

፪. የአተረጓጐሙ ስልትም ከቤተ ክርስቲያናችን የአተረጓጐም ስልት የራቀ ስለሆነ አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው ብለው በሙሉ ለመቀበል ሲቸገሩ ኑረዋል:: ቤተ ክርስቲያናችን በእነዚህ ትርጉሞች ስትገለገል የምትታይ ቢሆንም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ቅዱሳት መጻሕፍትን በግእዙ መሠረትነት ከዕብራይስጡና ከሰብዓ ሊቃናቱ ጋር በማስተያየት ለመተርጐም ምቹ ጊዜ ትጠብቅ ነበር::

በመጀመሪያ እነዚህን ምክንያቶች አጠር አድርገን እንመልከት:: ምክንያቱም ሰፊ ማሳያ ለማቅረብ የመጽሔቱ አምድ በቂ ካለመሆኑም በላይ ጉዳዮቹ በራሳቸው ሰፋ ጥናት የሚጠይቁ በመሆናቸው ነው::

በመግቢያው ላይ በተገለጸው የመጀመሪያው ምክንያት እስካሁን ያሉት ትርጉሞች ግእዙን መሠረት አለማድረጋቸው ተገልጾልናል:: ቀደም ብዬ እንዳልኩት በዚህ ጽሑፍ «እነዛ ሥራዎች ግእዙን መሠረት አድርገዋል ወይስ አላደረጉም? ለምን?» የሚለውን አንመረምርም:: ይሁን እንጂ ለአሁኑ ትርጉም ግእዙን መሠረት ማድረግ ለምን አስፈለገ? የሚለው ሊነሣ የሚገባው ነው:: ግእዙን መሠረት ማድረጉስ ለምን ይጠቅመናል? የሚለውም እንዲሁ ሊዳሰስ የሚገባው ጉዳይ ነው::

ቀደም ብለን በመግቢያችን ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ግእዝ የተተረጐሙት መቼ ነው? የሚለውን ለመዳሰስ የሞከርነውም ለዚህ ነበር:: በዚህ ዕትምም ሆነ ከዚህ በፊት በነበረው እንደተመለከትነው ኢትዮጵያ ሀገራችን ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደራሳቸው ቋንቋ ከተረጐሙት ጥቂት ሀገራት መካከል ተቀዳሚ ናት:: በተለይም እንደ እኛ ሀገር ሊቃውንት እምነት ብሉይ ኪዳንን ከዓለም ቀድማ የተረጐመች፣ የተጠቀመችበትም እርሷ ናት:: /ትርጓሜ ሲራክ ወሰሎሞን መቅድም ተመልከት/ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በዘመኑ እንደገለጸው በዚያ ዘመን /ከ፬ኛው ክፍለ ዘመን/ ኢትዮጵያ ሐዲሳቱም እንደ ነበሯት ተመስክሯል:: ስለዚህ እውነተኛውን ምንጭ ከያዙት ውስጥ ተቀዳሚዋ ናት:: ለዚህ እንደ ምሳሌ መጽሐፈ ሔኖክን መመልከት ይቻላል:: መጽሐፈ ሔኖክ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ከፍተኛ ዕውቅናን እያገኘ መጥቷል:: ይህ መጽሐፍ ለዚህ የበቃው ከጥንት ቅጂዎች መካከል በቁፋሮ የሚገኙት ብጥስጣሾቹ ሲጠኑ ከኢትዮጵያው መጽሐፈ ሔኖክ ጋር በመግጠማቸው ነው:: ይህም መጽሐፉ አለን ከሚሉት ይልቅ ኢትዮጵያ በተለየ ሁኔታ መጽሐፉን መጠበቋንና ለዓለማችንም ማስረከቧን ያሳያል:: ነገር ግን መጽሐፉን የማቆየቷን ያህል በጥናቱም መስክ ተጠቃሚ ለመሆን አልቻለችም:: በዚያም አለ በዚህ ግን ጥንታዊና ያልተበረዘ ምንጭ ለመያዟ ይህ መጽሐፍ ምስክር ሆኖታል:: በሌሎች ሀገራት የነበረው የመጽሐፈ ሔኖክ ቅጂ በቁፋሮ ከተገኘው ጋር ሳይገጥም የኢትዮጵያው ገጠመ ማለት ትርጉሙን ሳታዛባ እስካሁን ለመጠበቋ ትክክለኛ አስረጂ መሆኑ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው:: ይህ ከሆነ ዘንድ ሌሎቹንም መጻሕፍት ወደ አማርኛና ሌሎች ቋንቋዎች ስትተረጉም ግእዙን መሠረት ማድረጓ ዓለም ሁሉ ሊወደው የሚገባ ዐቢይ ተግባር ነው:: ስለዚህ «ግእዙን መሠረት ማድረግ» የሚያመጣው ይህ መሠረታዊ አስፈላጊ ጉዳይ እንጂ ቋንቋው የእኛ የመሆኑ ጉዳይ አይደለም::

በሌላ መልኩ ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ «ግእዙን የተጠቀምኩት እስካሁን ያለው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ንባቡ ወይም ዘርዑ ያልተሟላ በመሆኑ ነው» ካለች ወደ ይዘቱ ስንገባ ይህን ልዩነት ማሳየት ይኖርባታል ማለት ነው:: ስለ ዚህ በመግቢያው የተገለጸው የመጀመሪያው ምክንያት የሚነግረን የዘር ለውጦች መኖራቸውን ነው:: ይህ ሁኔታ በይዘቱ ከተገኘ ደግሞ በርግጥም የትርጉሙ ሥራ አስፈላጊ ነበር ለማለት ይቻላል:: ይሁን እንጂ አሁን እነዚያን ማሳያዎች አናቀርብም:: ይልቁንም ሁለተኛውን ምክንያት እንመልከት::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ «የአተረጓጐሙ ስልትም ከቤተ ክርስቲያናችን የአተረጓጐም ስልት የራቀ ስለሆነ» የሚል ነው:: በዚህ ጽሑፍ የመጀመሪያ ዕትም ላይ ስለ ትርጉም ምንነት በቅድሚያ ያየነው በዚሁ መሠረታዊ ምክንያት ነበር:: በርግጥ ቤተ ክርስቲያኒቱ የዚያን የአተረጓጐም ስልት ችግሩም ምን እንደሆነ ከዚያም ደግሞ የእኛን ቤተ ክርስቲያን አተረጓጐም ምንነትና የዚያኛውን ችግር የመፍታት አቅሙን ብታሳይ የተጠቀሰው ምክንያት የበለጠ ግልጽ ይሆን ነበር:: ይሁን እንጂ ይህ አለመሆኑ የተመራማሪ ፍላጐትን ባያረካም እውነታውን ስለማያስቀረው ወደ ጉዳዩ እንለፍ::

በቅድሚያ ስለ ትርጉም ያለንን ትውፊታዊ አመለካከት መጠቆም የሚያሻ ይመስላል:: ምክንያቱም ይህ ጉዳይ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንትን ሲያከራክር የኖረና አሁንም የሚያከራክር በመሆኑ ነው:: ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ነው:: ሲተረጐሙስ? ያለመንፈስ ቅዱስ ልዩ ዕርዳታ መተርጐም ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ነው:: ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ይህን ጥያቄ ለመመለስ የሚያመሩት ወደ ሰባ ሊቃናት /Septuagint/ ትርጓሜ ነው:: ወደ ዚያ ካመሩ በኋላ የሰባ ሊቃናት ትርጉም የተተረጐመው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ነው ወይስ በሊቃናቱ የቋንቋ ችሎታ ብቻ? የሚለውን ይመረምራሉ:: ይህም ቢሆን ግን አንድ መልስ አላስገኘላቸውም:: ከፊሎቹ ሊቃውንት ሰብዐ ሊቃናት ተከፋፍለው የተረጐሟቸውን መጻሕፍት በመመርመር የአንዱን የቋንቋና የሰዋስው ችሎታ ከሌላኛው ጋር በማነጻጸርና በማበላለጥ ዕውቀታቸው

> «አብነት» የሚሉት ብዙ ጊዜ ሳይነካካ ከቀድሞ መምህራን ጀምሮ የነበረውን ንባብና «ምስክር» የሆኑት መምህራን በጥንቃቄ እየጠበቁ ለትውልድ የሚያሸጋግሩት ንባብ ነው:: ታዲያ በዚያ ንባብ ውስጥ የከበደውን ቋንቋ የአንድ ዘመን ሊቅ ለዘመኑ በሚመጥን ቢተረጉመው አብነቱን (ያን የጥንቱን) አያጠፋውም::

ተጽእኖ አሳርፏል፣ ስለዚህ በቂ ዕውቀት እስካለ ድረስ ለመተርጐም ሌላ ተጨማሪ ኃይል አያስፈልግም ሲሉ ከፊሎቹ ደግሞ የስምዖንን ታሪክ በማቅረብ ያለመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ መተርጐም አይገባም ብለው ይከራከራሉ::

የስምዖን ከፊል ታሪክ በሉቃስ ወንጌል ላይ ሰፍሯል:: «በኢየሩሳሌምም ስሙ ስምዖን የሚባል አንድ ሰው ነበር፣ እርሱም ጻድቅና ደግ ሰው ነበር፣ እርሱም የእስራኤልን ደስታቸውን ያይ ዘንድ ተስፋ ያደርግ ነበር፣ መንፈስ ቅዱስም ያደረበት ነበር፣ የእግዚአብሔርንም መሲሕ ሳያይ እንደማይሞት መንፈስ ቅዱስ ገልጦለት ነበር፣ ...» እያለ ቅዱስ ሉቃስ ተናግሮለታል:: /ሉቃ.፪÷፳፭-፴፭/

በዚህ ንባብ ውስጥ «የእግዚአብሔርን መሲሕ ሳያይ እንዳይሞት መንፈስ ቅዱስ ገልጦለት ነበር» የሚለው ወሳኙ ነገር ነው:: በዚህ መሠረት ስምዖን ማን ነው? መንፈስ ቅዱስ ይህን ያለው ለምንድን ነው? መቼ? ... የሚሉት ጥያቄዎች መነሣታቸውም አይቀሬ ነው::

ስምዖን ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ጽርዕ /ግሪክኛ/ ፪፻፹፬ ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ከተረጐሙት ሰብዓ ሊቃናት አንዱ ነው:: በእኛ ትርጓሜ ላይ እንደተቀመጠው ይህ ሰው ሊተረጉመው የተሰጠው /ድርሻው/ ትንቢተ ኢሳይያስ ነበር:: እርሱን ሲተረጉም «ድንግል ትጸንሳለች፣ ወንድ ልጅም ትወልዳለች» የሚለው ላይ ሲደርስ «ድንግል ከሆነች እንዴት ትጸንሳለች? ከጸነሰችስ እንዴት ድንግል ትሆናለች?» የሚል ጥያቄ በሕሊናው ይመጣበታል:: ከዚህ በኋላ የራሱን ዕውቀት ተጠቅሞ «ድንግል» የሚለውን «ሴት» በሚል ለወጠና «ሴት ትጸንሳለች ...» ብሎ ተረጐመው:: ወዲያው ድካም ይሰማውና ይተኛል:: ከእንቅልፉ ሲነቃ እርሱ «ሴት» ብሎ የጻፈው ተለውጦ «ድንግል» ሆኖ ያገኘዋል:: ብዙም ሳያሰብበት እርሱ ተሳስቶ የጻፈው መስሎት አሁንም «ድንግል» የሚለውን ለውጦ ሴት ብሎ ይጽፈዋል:: አሁንም ዕንቅልፍ ይጥለውና እንደገና ድንግል ተብሎ ያገኘዋል:: እርሱም እንደገና «ሴት» ይለዋል:: በዚህ ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ ከላይ የተጠቀሰውን መልስ ያገኛል:: ቃሉን «ድንግል» እንዲልና ይህን ማመን ስለከበደውም ይህን ሳያይ እንደ ማይሞት ይነገረዋል:: ስለዚህ ስምዖን ከ፫፻ ዓመታት በላይ ኖሮ በድንግልና ተጽንሶ በድንግልና የተወለደውን ጌታ ታቀፈና እርሱም ታደሰ::

ይህን ታሪክ ማስታወስ ያስፈለገው በሁለት ምክንያት ነው:: አንደኛው ከላይ ባየነው ክርክር ውስጥ ሁለተኛዎቹ ወገኖች «ለትርጉም የመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ ያስፈልጋል» የሚሉት መነሻቸው ይህ ዐቢይ ታሪክ ስለሆነ ነው:: ሁለተኛው ግን ይህ ትውፊት በእኛ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዘንድ በሰፊው መታወቁ ስለእኛ ቤተ ክርስቲያን የትርጉም አመለካከት ያለውን አስተዋጽኦ ለመጠቆም ነው::

ክርክሩ እስካሁን ቢኖርም የሰብዐ ሊቃናት ትርጉም በመንፈስ ቅዱስ ተራዳኢነት ተተርጉሟል የሚለው ግን በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ነው:: ምክንያቱም ከላይ የጠቀስነው የአንድ መጽሐፍ ከሌላው ጋር ያለው የቋንቋና የሰዋስው ልዩነት መጠነኛ ልዩነት ከመሆኑም በላይ መንፈስ ቅዱስም በአካል ሳይሆን በሰው አድሮ መሥራቱን የሚያሳይ በመሆኑ ነው:: ይህም ማለት መንፈስ ቅዱስ ምስጢር እንዳይዛነፍ፣ እንዳይጐድል እንዳይተርፍ ይረዳቸዋል፣ ሌላም ምስጢር ይገልጽላቸዋል ማለት ሰውነታቸውን አጥፎቶና ገርኝቶ ያሠራቸዋል ማለት አይደለም:: ስለዚህም የሰውነታቸው አሻራ በቋንቋና ሰዋስው የአቅም ልዩነት መገለጡ ሥራውን ሰዎችም እንደሠሩት የሚያሳይ ማስረጃ ነውና::

ከሰብዐ ሊቃናት የትርጉም ታሪክ ይህን ያህል ብልጭታ ካየን የእኛ ሊቃውንት የትርጉም አመለካከት ምንድን ነው? የሚለውን ለመጠቆም ይቻላል:: በዚህ መሠረት ሊቃውንቱ ተሰባስበውና ተከራክረው ወይም ተስማምተው በወጥነት ይህ ነው ብለው ያስቀመጡት ሰነድ ባይኖርም ትውፊቶቹ ግን አሉ:: የመጀመሪያው ትውፊት ከላይ የጠቀስነው የስምዖን ታሪክ ነው:: ከዚህ ታሪክ ሦስት ነገሮችን ማስተዋል ይቻላል:: የመጀመሪያው በሥጋዊ ዕውቀትና ፍልስፍና ብቻ ተወስኖ ከቅዱሳት መጻሕፍት አንዲት ቃልንም መለወጥ ክልክል መሆኑን ነው:: ስለዚህ ዕውቀት አስፈላጊና የሥራውም ዋና አካል ቢሆንም የቅዱሳት መጻሕፍት ምስጢርና መልእክት ከዚህ ዕውቀት በላይ በሚሆንበት ጊዜ በምናውቀው ዕውቀት ብቻ ተመሥርቶ መሔድ አይገባም ማለት ነው:: ጊዜውን ጠብቆ እንደ ስምዖን ማወቅ፣ ማየትና ማረጋገጥ እንጂ ሆኖ ካላየሁት እኔ በዚህ አላምንም ማለት አይቻልም ማለት ነው:: ሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍት ያለ መንፈስ ቅዱስ ርዳታ ሊተረጐሙ አይቻልም፣ የሚለው ነው:: እዚህ ላይ መስተዋል ያለበት ነገር አለ:: የመንፈስ ቅዱስ ርዳታና ለቅዱሳት መጻሕፍትም የሚሰጠውን ጥበቃ በስምዖን ተገልጦ ያየነው እርሱ በተነሣበት የኅሊና ጥያቄና በፈጠረው ስሕተት ምክንያት ነው:: ይህ ማለት በተሳሳተ ጊዜ ባይነግረውና ባያስተካክለው ኑሮ መኖሩን ላናውቅ እንችል ነበር:: መንፈስ ቅዱስ ግን ነበረ:: ስምዖን ከመጀመሪያው «ድንግል» የሚለውን ቃል ሳይለውጥ ጽፎ ቢሆን ኖሮ ይህን ሁሉ ታሪክና ክስተት አናገኘውም ነበር:: ይህ ማለት ግን መንፈስ ቅዱስ አልነበረም ማለት አይደለም:: ስምዖንን ሲረዳውና ሲጠብቀው ባይቆይ ኖሮ በተሳሳተ ጊዜ ለምን ይናገረው ነበር? ስለ


ወደ ገጽ ፴፰ ዞሯል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# በጆሮአችን የሰማነውን በዐይናችን አየነው

ጌታቸው በቀለና መ/ር ሳሙኤል ተስፋዬ



«ወከዐው ደሞሙ በእንተ መንግሥተ እግዚአብሔር፣ ወተዐገሡ ሞተ መሪረ»
/ሰማዕትነት በተቀበሉበት ቤተ ክርስቲያን/ የሚገኘው የሰማዕታተ በሻሻ ሐውልት

*ባለፈው የሐምሌ/ ነሐሴ ፳፻ እትም ከጅማ ሀገረ ስብከት እንቅስቃሴ ጀምሮ እስከ ጨጐ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ድረስ የተመለከትናቸውን አብያተ ክርስቲያናት ያሉበትን ሁኔታ፣ የምእመኑን መንፈሳዊ ሕይወት በተመለከተ ሰፊ ዘገባ ማቅረባችን ይታወሳል:: ቀሪውን ከበሻሻ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ እስከ ናትሪ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የተመለከትነውን እነሆ:: መልካም ንባብ::*

## በሻሻ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን

ባለፈው እትም በጅማ ሀገረ ስብከት የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን አስቃኝተናችሁ ጨጎ ቅዱስ ገብርኤል ስደርስ በይደር ማቆማችን ይታወሳል:: ዛሬ ደግሞ በዘገባችን ማጠቃለያ በሻሻ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እና ናትሪ ደብረ ሰላም ቅዱስ ገብርኤልን እናስተዋውቃችሁ::

በሻሻ ከተማ ከጅማ ፸ ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች:: በሻሻ እንደደረስን መኪናችንን ከመንገዱ በስተቀኝ ጠርዝ አቁመን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አመራን:: ሊቀ መዘምራን ብርሃኑ ጌጡ እየመሩን፣ እኛ እየተከተልናቸው ከመንገዱ በስተቀኝ የምትገኘዋን አፋፍ ወጣን:: ወደ ቦታው እንዳደረስን ገርበብ ወዳለው የቆርቆሮ በር አመራን:: ወደ ውስጥ ስንዘልቅ የግቢውን ጥበቃ፣ አንዷት ዕድሚያቸው በ፷ዎቹ አካባቢ የሚገኙ የቤተ ክርስቲያኑ አቃቢትና አንድ ወጣት አገኘን:: ሦስቱም ከተከዙበት ቀና ብለው በአግራሞት ይመለከቱናል:: ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሰው ዝር በማይልበት ወቅት እንዴት መጡ? እነማን ናቸው? የሚሉ ይመስላሉ:: በቅድሚያ ከሊቀ መዘምራን ጋር ሰላምታ ተለዋወጡ፤ ከእኛም ጋር እንደዚያው::

እንደሚታወቀው ጥቅምት ፬ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም አክራሪ እስላሞች ክርስቲያኖችን በገጀራ ጨፍጭፈው በመግደላቸውና ቤተ ክርስቲያኑን በማቃጠላቸው በቦታው የደረሰው መከራ የሐዘን ድባብ እስካሁን አለ:: በቤተክርስቲያኑም ያገኘናቸው ሦስቱ ሰዎች ተክዘው የሚተያዩት ከዚህ የተነሣ ሳይሆን እንደማይቀር ገምተናል:: የቦታውን መጎሳቆል፣ የሰውን ፍራቻ ስናይ ወደ ኋላ ሔደን ፲፫ኛው መ/ክ/ዘ የግራኝ አሕመድ ወረራን እንድናስታውስ አስገደደን::

በቅድሚያ የቤተ ክርስቲያኑን ዙሪያ እየተዟዟርን በቃጠሎ የወደመውን ተመለከትን:: ቤተክርስቲያኑን ሙሉ በሙሉ አቃጥለውታል:: በቦታው የፈራረሰ ግድግዳ እንኳ አይታይም:: ባዶ ሆኗል:: በተቃጠለው ቤተ ክርስቲያን ላይ ሰማዕትነት ለተቀበሉት ክርስቲያኖች ማዘከሪያ የሚሆን ሐውልት ተሠርቷል:: በዙሪያውም ከቃጠሎ የተረፉ ጫማዎች፣ ልብሶች... ተበታትነው ይታያሉ:: ከአጠገቡም ጣሪያው የተነቃቀለ፤ ግድግዳው በገጀራ የተቸፈቸፈ፣ በሩና መስኮቱ የወላለቀ የሰንበቴ ቤት ይታያል::

ዝቅ ብሎ ወደ ዋናው መንገድ አቅራቢያ በቆርቆሮ የተሠራች ትንሽ መቃኞ ትገኛለች:: መንገድ አቅራቢያ የተሠራበት ምክንያት የሚያልፍ የሚያገድመው ክርስቲያን ተሳልሞ፤ ጸሎቱን አድርሶ ሊያልፍ እንዲችልና ለዳግም ጥቃት እንዳይጋለጥም ታስቦ መሆኑን ሊቀ መዘምራን ብርሃኑ ጌጡ ገልጸውልናል::

የበሻሻ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተው በ፲፱፻፹ዎቹ ነው:: ቤተ ክርስቲያኑ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ከአጽራረ ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ፈተናዎች በየጊዜው ይደርስበት ነበር:: በወቅቱም ሕዝበ ክርስቲያኑ በሚያሰሙት ሮሮ ሊቀ ጳጳሱ፣ የሀገረ ስብከቱ ሠራተኞች እየተመላለሱ ያጽናኗቸው ነበር:: ቤተ ክርስቲያኑ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ፈተና ተለይቶትም አያውቅም::

አክራሪ ሙስሊሞቹ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑን ሲያቃጥሉ ንዋየተ ቅድሳቱን፣ ቅዱሳት መጻሕፍቱን ሁሉ አውድመውታል:: የታሪክ ሰነዶች የእሳት ራት ሆነዋል:: ካህናቱና ምእመናን አብረው ተቃጥለዋል:: ከእሳት የተረፉት ምእመናንና ሕፃናት በገጀራ ተሰይፈዋል:: ያለውድ በግዴታ ሃይማኖታቸውን እንዲለውጡ የተደረጉም አሉ:: በዚህ ጭፍጨፋ ከ፶ ያላነሱ ሰዎች ቀላልና ከባድ የሰውነት መቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል:: ከዚህ በላይ እጅግ የሚያስቅቅ ዘግናኝ የሆነ ጾታዊ ጥቃትም በሴት እኅቶቻችን ላይ መፈጸሙ የሚረሳ አይደለም::

የአእምሮ እና የአካል ጉዳት ከደረሰባቸው ውስጥ የቤተክርስቲያኒቷ አቃቢት ወለተ ሥላሴ /ወሰኔ ገብሬ/ አንዷ ናቸው:: አቃቢቷ በገጀራ ተጨፍጭፈው፣ ጫካ ተጥለው በሁለተኛው ቀን የተገኙ ናቸው:: ሆስፒታል ተወስደው ቢታከሙም ዛሬም ጠባሳው ይታያል፤ ኅሊናቸውም አልተረጋጋም:: በገጀራ የተቸፈቸፈውን ሰውነታቸውን አሳዩን:: በዚያን ወቅት በቤተ ክርስቲያኑ ላይ የደረሰውን ጥቃት ሲያስቡት ማመን ያቅታቸዋል፤ አእምሮአቸውም አሁንም ይረበሻል:: ስናነጋግራቸው ዕንባቸው ቀደመ፤ ድምፃቸው እየተቆራረጠ «እስላሞቹ ያንን የመሰለ ቤተክርስቲያን ከነ ጽላቱ ማቃጠላቸው ያሳዝነኛል:: የእግዚአብሔርን ፍርድ እጠባበቃለሁ:: የደረሰብን መከራ መቼም አይረሳም:: በአሁኑ ወቅትም የተለያዩ ስጋቶች አሉብን» አሁንም እንባቸው ይፈሳል::

በአጥቢያው ከ፴-፶ የሚደርሱ ክርስቲያን አባወራዎች የሚገኙ ቢሆንም ተበታትነው የሠፈሩ ናቸው:: የኑሮ ደረጃቸው ዝቅተኛ በመሆኑ የዕለት ጉርስ፣ የዓመት ልብስ በበቂ ሁኔታ የማያገኙ ናቸው:: ካለባቸው ተጽዕኖና ፍርሃት የተነሣ እምብዛም ወደ ቤተ ክርስቲያን አይመጡም:: ከቃጠሎው በኋላ ከፊሎቹ ካህናትም ተሰደዋል:: የቀሩት ሁለት ናቸው:: በዚህም የተነሣ ስብከተ ወንጌል ተዳክሟል:: ምእመኑንም የሚያጽናና ካህን የጠፋበት ሁኔታ ይታያል::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የጎማ ወረዳ ቤተ ክህነት ሊቀ ካህን ቀሲስ ታጋይ ታደሰ እንደገለጹት የጅማ ሀገረ ስብከት ሁኔታ የተለየ ነው፤ በተለይ የገጠሩ ክፍል:: ምእመናን የሚያጽናናቸው፣ የሚመክራቸውና ለችግራቸው የሚደርስላቸው ይፈልጋሉ:: ስለዚህ ሁኔታ ቀሲስ ታጋይ የሚከተለውን ነግረውናል:: ሲገልጽልን «እነዚህን ለማስተማርና ለማጽናናት ከአዲስ አበባ መምህራን ለማስመጣት ስንፈልግም፤ በቅድሚያ ስንት ብር ትከፍለኛለህ? ነው የምትባለው:: ይሄ በጣም አሳዛኝ ነው:: የሙስሊሞቹን ግን ስናይ የሚገርም ነው:: ከሀገር ውስጥና ከኢትዮጵያ ውጭም ከፓኪስታን፣ ከዐረብ ምድር እየመጡ ገጠር ድረስ ገብተው ያስተምሯቸዋል:: ክርስቲያኑን የሚያጠቁበት ታክቲክ ምን እንደሆነ ያስረዷቸዋል:: የእኛ መምህራን ግን እንዲህ አይደሉም፤ ከከተማ መውጣት አይፈልጉም» ብሎን ነበር::

ከቤተ ክርስቲያኑ ቃጠሎና ከክርስቲያኑ ጭፍጨፋ በኋላ ሀገረ ስብከቱ እያደረገ ያለውን ሊቀ መዘምራን ብርሃኑ ጌጡ ሲገልጹ «ሀገረ ስብከቱ ቤተሰቦቻቸው የሞቱባቸውን ወገኖቻችንን አቅም በፈቀደ መጠን በገንዘብ፣ በምክርና በአካልም በየቤታቸው ድረስ በመሄድ አጽናንተናል:: ምእመኑ አገልገሎት እንዲያገኝም በቆርቆሮ መቃኞ ተሠርቷል:: ጥር ፳፮ እና ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም በርካታ ምእመናን በተገኙበት ጽላቱ ገብቷል:: በዚህም ምእመኑ በመጠኑም ቢሆን አገልግሎት እንዲያገኝ ተደርጓል» ብለዋል::

አዲስ የተሠራው መቃኞ ቤተ ክርስቲያን ውስጡን እንደተመለከትነው የተሟላ ንዋያተ ቅድሳት፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ... የሉትም:: ሌላው በውስጡ የተመለከትነውና ትኩረታችንን የሳበው ሰማዕትነት የተቀበሉትን የስድስቱን ሰዎች ፎቶና ታሪካቸውን የያዘ አንድ ትልቅ የእምነ በረድ ጽሑፍ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ተቀምጧል:: «የሰማዕታቱን ታሪክ የያዘውን የእምነ በረድ ጽሑፍ ሐውልቱ ላይ ያላደረግነው ለጥበቃ አመቺ ስላልሆነ ነው» ይላሉ ሥራ አስኪያጁ:: ሰማዕታቱ የተቀበሩት አጋሮ ከተማ በምትገኘው የአጋሮ ፈለገ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ነው:: የሰማዕታቱም ቤተሰቦች ቢሆኑ ለከፍተኛ ችግር ተጋልጠዋል:: አንቱ የተባሉበትን ቀዬአቸውን ለቀው የተሰደዱ፣ አድራሻቸውም እስከ አሁን የማይታወቅ ሰዎች እንዳሉ ከሊቀ መዘምራን ገለጻ ተረድተናል::


የበሻሻ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያን የጥበቃ ሠራተኛው አቶ መሠረት ታዬ በአካባቢው ካለው የሙስሊምና የመናፍቃን ወረራ የተነሣ መደረግ ያለበትን ሲገልጹ ደግሞ «በአሁኑ ወቅት ያለው ሁኔታ የተረጋጋ አይደለም:: ቢሆንም ግን ነቅተን እየጠበቅን እንገኛለን:: ሀገረ ስብከቱ እንዲያሟላልን የሚያስፈልገው ነገር አለ:: አንድ ችግር ቢደርስብን እንኳ ወደ ወረዳ ወይም ሀገረ ስብከት ስልክ ለመደወል ገመድ አልባ ስልክ እንዲያስገባልን ነው» ይላል::

በጅማ ሀገረ ስብከት በክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመውን ግፍ በጥሞና ሲከታተል የነበረው ፍቅረ ማርያም የተባለ አንድ የሕግ ባለሙያ የሃይማኖት አባቶች ማድረግ አለባቸው ያለውን አስተያየት ሰጥቶናል:: «በአሁኑ ወቅት ያለውን ሁኔታ ከባለፈው በተነፃፀረ ሁኔታ ስንመለከተው ውጥረቱ ረገብ ያለ ይመስላል:: የሻከረውን ግንኙነት ለማለስለስ አንድ ኮንፍረንስ ማዘጋጀት ግን ያስፈልጋል:: የሃይማኖት አባቶች ክርስቲያኑንና ሙስሊሙን በአንድነት በመሰብሰብ ይቅር የሚባባሉበትንና የወንድማማች መንፈስ የሚፈጠርበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባቸዋል:: አለበለዚያ ግን ውሎ አድሮ ነገሮቹ ሊቀየሩ ይችላሉ::»

በበሻሻና በጨጎ የተፈጸመው ጭፍጨፋ መላው ዓለምን አሳዝኗል:: አብያተ ክርስቲያናቱን ለማጥፋት፣ ክርስቲያኑን ለማስለም የታቀደው ሤራ ከሙስሊሙ አንደበት በተደጋጋሚ የሚደመጥ ነው:: ድርጊቱ በተፈጸመበት ቦታ ተገኝተን አንዳንድ ያነጋገርናቸው ምእምናን ይህን ሁኔታ ደጋግመው አስረድተውናል::

ክርስቲያንን በመጨፍጨፍ ቤተ ክርስቲያንን በማቃጠል ግን ክርስትናን ማጥፋት አይቻልም:: ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተመሠረተች፣ ክርስቲያኖችም የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ናቸውና:: ይኸንንም የቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ «ሰውን ብትታገልና ብትዋጋ ታሸንፈዋለህ:: ቤተ ክርስቲያንን ግን ለማሸነፍ አይቻልም:: ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ ትወጋለች /ትጠቃለች/ ተሸንፋ ግን አታውቅም:: ዲያብሎስ ዝናሩን አራገፈ፣ ቀስቱንም ጨረሰ፤ ቤተ ክርስቲያንን ግን አልጎዳትም» እንዳለ ዛሬም አጽራረ ቤተ ክርስቲያን ይህን ሁሉ መከራ በቤተ ክርስቲያን ላይ ቢፈጽሙባትም ቤተ ክርስቲያን ግን አሁንም አለች፤ ወደፊትም ትኖራለች::

በሻሻ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ካየን በኋላ ወደ አጋሮ ከተማ ተመለስን፤ የአጋሮን ጓዳ ጎድጓዳውን አየን:: «አጋሮ ቼንቶ በጓሮ»:: የቡና አገር ሁሉም ሠርቶ የሚያድርባት የተለያዩ የብሔረሰቦች ስብጥር የሚታይባት ናት:: የመልክአ ምድር አቀማመጧ ወጣ ገባ የሆነ ከባሕር ወለል በላይ ፩ሺሕ፭፻ ሜትር ከፍታ ያላት ሲሆን የአየር ንብረቷም ወይና ደጋ ነው:: ተዘዋውረን እንደተመለከትነው በአጋሮ ከተማ ከሚገኙት አራቱ አብያተ ክርስቲያናት አንዱ በከተማዋ ቀደምት የሆነው በ፲፱፻፲፱ ዓ.ም በራስ ደስታ ዳምጠው የተመሠረተው የደብረ ፀሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ነው:: ከዕድሜ ብዛት አርጅቶ በመፈራረስ ላይ ይገኛል:: ከዚያም የፈለገ ሰላም ቅድስት ማርያምንና የቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተመልክተን ወደ ጅማ ተመለስን:: ከዚያም ወደ ናትሪን::



*በ1999 ዓ.ም በአክራሪ እስላሞች ክርስቲያኖች ታርደው ቤተ ክርስቲያኑ ከተቃጠለ በኋላ የተሠራው መቃኞ /በሻሻ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ/*

## ናትሪ ደብረ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል

ጉዞአችን ያጠናቀቅነው የናትሪ ደብረ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንን በመጎብኘት ነበር:: ናትሪ ቅዱስ ገብርኤል ከአዲስ አበባ ፪፻፳ ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል::

የናትሪ አካባቢ ምእመናን በአቅራቢያቸው ቤተ ክርስቲያን ስለሌለ ለጥምቀት፣ ለፍትሐት፣ ለቁርባንና ሌሎችንም መንፈሳዊ አገልግሎቶች የሚያገኙት ከአካባቢያቸው ፲፪ ኪ.ሜ በላይ በእግር ተጉዘው ቁምቢ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ነበር:: የናትሪ ምእመናን ዙሪያቸውን የከበቧቸው የእስልምና እምነት ተከታዮች በየጊዜው መከራ ያደርሱባቸው ነበር:: ይህም ሆኖ ግን ተስፋ ሳይቆርጡ ከፈጣሪያቸው ጋር



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

የሚነጋገሩበት ቤተ ክርስቲያን በአቅራቢያቸው እንዲኖር ወደ ፈጣሪያቸው ያሳስቡ ነበር፡፡

እግዚአብሔር በወጀብና በአውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለውና በጥቂት ፍቅረ እግዚአብሔር ባደረባቸው ምእመናን አድሮ የናትሪ ሕዝበ ክርስቲያንን ታሪካቸውን ለወጠላቸው፡፡ ዶ/ር ገብረ መስቀል፣ አቶ ወርቅነህ፣ ወ/ሮ እልፍነሽ ሁንዴና በወቅቱ የነበሩ ክርስቲያኖች ቤቱን ለማነጽ ተነሣሡ፤ ጀመሩም፡፡ ይህንን ቅዱስ ሐሳባቸውን በወቅቱ ለጅማ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ለነበሩት ለብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ በማሳወቅ በትዕግስትና በጸሎት ውጤቱን ይጠባበቁ ጀመር፡፡ ሀገረ ስብከቱ በሐሳባቸው ቢስማ ማም ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑን ግን ለማስጀመር አልተቻለም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የሕዝበ ክርስቲያኑ አለመተባበር ሳይሆን ጽላት አግኝቶ ከቦታው ላይ ማምጣት ባለመቻሉ ነበር፡፡

ጉዳዩ በዚህ እንዳለ የኩሎ ኮንታ ወረዳ አስተዳዳሪ የነበሩ ወደ ጅማ ሲመጡ በመ ንገዳቸው ላይ አንድ የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ተቃጥሎ ጽላቱ ምንም ሳይሆን አገኙ፡፡ ወዲያው ጽላቱን ይዘው ወደ ጅማ መጡ፡፡ እኒህ አስተዳደሪ የነበራቸው ዕቅድ ይዘውት የመጡትን ጽላት በጅማ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ለማስቀመጥ ነበር፡፡ እግ ዚአብሔር ያልፈቀደው አይሆንምና ሐሳባቸው ሳይሳካ ቀረ፡፡ በኋላም በጅማ ከተማ በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ያገለግሉ የነበሩትን ካህን አስጠርተው፤ ጉዳዩን አስ ረድተው ጽላቱን በአደራ አስረከቧቸው፡፡

ካህኑም ጽላቱን በወቅቱ ከሚያገለግሉበት ቤተ ክርስቲያን አስቀመጡት፡፡ ይሁን እንጂ እኚሁ የወረዳ አስተዳዳሪ ጡረታ ስለወጡ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ነበር፡፡ አደራ ውን የተረከቡት ካህንም ከጊዜ በኋላ ጽላቱን ለማስረከብ ሲሉ አደራ የሰጧቸውን ሰው ሲያፈላልጉ ወደ አዲስ አበባ መምጣታቸውን ይሰማሉ፡፡ በመጨረሻም አድራሻቸውን በማግኘታቸው ወደ አዲስ አበባ ተጓዙ፡፡ አዲስ አበባም አደራ የሰጧቸውን ሰው ቤት ቢያገኙም ሰውዬው በጠና ታመው ሆስፒታል መግባታቸው ስለተነገራቸው ጽላቱን ይዘው ወደ ሆስፒታል ያቀናሉ፡፡ የፈለጓቸውን ሰው ግን ከጠበቁት በላይ የአልጋ ቁራኛ ሆነው አገኟቸው፡፡ ሰውየውም ሊረከቧቸው በማይችሉበት ሁኔታ ላይ ስለነበሩ ካህኑ ጽላቱን ይዘው ወደ ጅማ ለመመለስ ተገደዱ፡፡

በአደራ የተረከቡትን ጽላትም በጅማ ጅሬን ቅ/ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አስቀመጡ፡፡ ከልብ የፈለጉት ነገር ሳይገኝ አይቀርምና የዚህን ዜና እነ ዶ/ር ገብረ መስቀል ሰሙ፡፡ ከካህኑም ጋር ተገናኝተው ተወያዩ፡፡ እነርሱም ወደ ሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሄደው ጉዳዩን አስረዱ፡፡ በአሠሩት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ጽላት በብፁዕ ነታቸው ፈቃድ ጥር ፲፱ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ፡፡ በዕለቱም የቤተ ክርስ ቲያኒቱን መከፈትና አገልግሎት መስጠት ይጠባበቁ የነበሩ በጅማና አካባቢዋ የሚገኙ በርካታ ምእመናን በተገኙበት በደመቀ ሥነ ሥርዓት በዝማሬ በቅዳሴ በድምቀት ተከብሯል፡፡ እግዚአብሔር ለዶ/ር ገብረ መስቀል የልባቸውን መሻት አሳካላቸው፡፡

ለዘመናት በጸሎትና በጾም፣ በፍጹም መንፈሳዊ ትጋት ይጠባበቁ የነበሩ የናትሪ ምእመናንም በሊቀ መላእክት በቅዱስ ገብርኤል ስም በተጠራው ቤተ ክርስቲያን አማ ካኝነት ፈጣሪ እንባቸውን አበሰላቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያኑም በዚህ ሁኔታ እየተገለገለ ቆየ፡፡ ዶ/ር ገ/መስቀልም ቤተ ክርስቲያኑን አሠርተው የጽላቱን መግባት ካዩ በኋላ፣




ሊቀ መዘምራን ብርሃኑ ጌጡ
የጅማ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ

ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ አስቀድ መውም የመቃብር ቤት አሠርተው ስለ ነበረ በዚያ ተቀበሩ፡፡ ከዚያም ቤተ ክር ስቲያኑ አገልግሎት ሲሰጥበት ቢቆይም ተንከባካቢ፣ ተመልካች በማጣቱ ለረጅም ጊዜ ያለ ጠባቂ ተቀምጧል፡፡ በአገልጋይ እጦት የተነሣ አገልግሎትም አይሰጥበ ትም ነበር፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም በሀገረ ስብከቱ ከተዘጉት አብያተ ክርስ ቲያናት እንደ አንዱ ሆኖ ይቆጠር ነበር፡፡ ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር እንዲል ቤተ ክርስቲያን የሚሠራበት፣ የተዘጋው የሚ ከፈትበት ዘመን ስለደረሰ እግዚአብሔር የናትሪ ደብረ ሰላም ቅዱስ ገብርኤለ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ሥራና ልማት ማኅበርን አስነሣ፡፡

ስለ ናትሪን ማኅበር አመሠራረት የሕ ንጻ አሠሪው ሥራና ልማት ማኅበር ሰብ ሳቢ አቶ ሙሉጌታ ቱሉን አነጋግረናቸው ነበር፡፡

አቶ ሙሉጌታ የዛሬ አምስት ዓመት ከባለቤታቸው ከወ/ሮ እመቤት ተፈራ ጋር በአቡነ ሐራ ማኅበር አማካኝነት ወደ ጅማ ሀገረ ስብከት ይጓዛሉ፡፡ በዚያም በጅማ መስመር በተዘጉት ፻፳፩ አብያተ ክርስ ቲያናት መካከል ቁምቢ ሚካኤል፣ ደቢ መድኃኔዓለም፣ ሳጃ ዮሐንስንና የናትሪ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንን ይጎበ ኛሉ፡፡ አቶ ሙሉጌታንና ባለቤታቸውን ከሁሉም በላይ ልባቸውን የነካቸው ዶ/ር ገ/መስቀል በተቀበሩበት በመቃብር ቤት ያለው የናትሪን ቅዱስ ገብርኤል ጽላት ነው፡፡ እኛ ቪላ ቤት እየኖርን የቅዱስ ገብርኤል ጽላት በመቃብር ቤት እንዴት ይቀመጣል? በማለት አዝነው፤ አልቅሰው ቃል ኪዳን ገብተው ይመለሳሉ፡፡

ከሁለት ዓመት ተኩል በኋላ ሐምሌ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ፈቃደኛ የሆኑ ፳፩ ምእመ ናን ከአዲስ አበባ ወደ ናትሪ ቅዱስ ገብርኤል ይዘው ሄዱ፡፡ በዚያም «የናትሪ ደብረ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ማኅበር» ሊመሠረት ቻለ፡፡ የተዘጉት ተከፍተው አገልግሎት እንዲሰጥባቸው እናደርጋለን ብለው ቃል ገቡ፡፡ በዚያም ማኅበሩ ወደ ፊት መሥራት ያለበትን ዕቅድ አወጡ፡፡ የመጀመሪያ ዕቅዳቸው የናትሪ ቅዱስ



የናትሪ ደብረ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ገብርኤልን ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ማሠራት ነበር:: እንደ አቀዱትም የአዲስ አበባ ምእመናን አስተባብረው ሕንጻውን 869,000 ብር ወጪ አድርገው አሠርተዋል:: በ፩ ዓመት ተኩል ውስጥ ሕንጻውን ሠርተው አጠናቀው ሐምሌ ፲፱ ቀን ፳፻ ዓ.ም የህገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስና በርካታ ምእመናን በተገኙበት አስመርቀዋል::

በአካባቢው ፲፭ አባወራ ክርስቲያኖች የሚኖሩ ሲሆኑ ክርስቲያኖቹን የሚያንቋሽሽ፣ የሕፃናትን ጭንቅላት የሚመርዝ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይሄዱ ለማድረግ የሚገፋፋ ስድብ ሙስሊሞች የሚሰድቧቸው መሆኑን አቶ ሙሉጌታ ይገልጻሉ:: «ሕፃናቱን ስለሚሰድቧቸው ወደ ቤተክርስቲያን አንመጣም ሙስሊሞቹ እንዲህ ይሉናል እያሉ የሚሰድቧቸውን ጭንቅላት የሚነካ ስድብ የሚናገሩበትና የሚፈሩበት ሁኔታ ነበር:: አሁን በተቻለ መጠን ያለባቸውን ሥነ ልቡናዊ ጫና ተቋቁመው ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ ሰንበት ት/ቤት እንዲቋቋም እያደረግን ነው፣ ፶፯ የሚሆኑ ልጆችንም አግኝተናል» ይላሉ::

ማኅበሩም የህገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በሚሰጧቸው መመሪያ የተለያዩ አመርቂ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል:: ማኅበሩ የተቋቋመበትን ምክንያት ሰብሳቢው ሲገልጹ «የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናትን ለማስከፈት የተቋቋመ የአገልግሎት ማኅበር ነው:: ማኅበሩ ቁምቢ ሚካኤል፣ ዶቢ መድኃኔዓለም፣ ሳጃ ዮሐንስን አስከፍቶ፣ ለእያንዳንዳቸው ሦስት ካህናት ቀጥሮ፣ ደመወዛቸውን በመክፈል አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል::

የገጠር አብያተ ክርስቲያናትን ችግር ዕለት በዕለት እየተከታተሉ በጉልበታቸው፣ በገንዘባቸውና በዕውቀታቸው አስተዋጽኦ በማበርከት ችግሩን ለመቅረፍ ምእመናን የሚሰባሰቡበት ነው:: እነዚህም ገንዘብ መስጠት ብቻ ሳይሆን በቦታው ተገኝተው ያለውን ችግር በቅርበት ተረድተው መፍትሔ የሚሰጡ ናቸው:: የአዋጡትን ገንዘብ በሰበካ ጉባኤ አማካኝነት በየወሩ ለካህናቱ ደመወዝ እንዲከፈልና አገልግሎት እንዲካሄድ ያደርጋሉ::

የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናትን አስከፍተው የስብከተ ወንጌል አገልግሎትን ለማስፋፋት በባትሪ ድንጋይ የሚሠራ ቴፕ፣ የተለያዩ የመዝሙርና የስብከት ካሴቶች ገዝተው በማቅረብ ምእመኑ ስብከተ ወንጌል እንዲያገኙ እያደረጉ ነው:: ማኅበሩ «ፕሮጀክት ሎዛ» በሚል አንድ ፕሮጀክትም እያከናወነ ነው:: በዚሁ ፕሮጀክት የተዘጉና የተዳከሙት ሙሉ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉና ዘላቂ መፍትሔ ለማምጣት «አንድ ብር ለአንዲት ገጠር ቤተ ክርስቲያን በወር ልግስና» በሚል መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ጀምሯል:: በዚህ ፕሮጀክት የመጀመሪያ ተጠቃሚ የሚሆኑት አጽራረ ቤተ ክርስቲያን ከፈጸሙት ግፍ ጋር ተያይዞ በጅማ ሀገረ ስብከት የተዘጉ ፮፴፮ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው:: የፕሮጀክቱ ተከታይ ዓላማ ሌሎችም የሀገሪቱን ክፍሎች የሚዳስስ ቢሆንም በእነኚህ ላይ መሠረታዊ የራስ ማስቻል ለውጥን ለመፍጠር ይጥራል::

ከአዲስ አበባ ወደ ናትሪ በ፳፭ መኪናዎች ተጉዘው ከጅማና ከአጥቢያውም በርካታ ምእመናን ተገኝተው የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ምርቃትና ዓመታዊውን የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በዓልን ሐምሌ ፲፱ ቀን ፳፻ዓ.ም በድምቀት አከብረዋል:: በገጠር ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት መፍትሔ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ማስገንባት ብቻ ሳይሆን ስብከተ ወንጌል ማስፋፋትና አብያተ ክርስቲያናቱ የራሳቸው ገቢ እንዲኖራቸው መንገድ መቀየስ ነው:: በዚህ ቦታ ላይ ማኅበሩ ሊሠራ ያቀደውን ሰብሳቢው አቶ ሙሉጌታ ሲያስረዱ:-

- በናትሪና በአካባቢው ከአምስት እስከ ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ሊያገለግሉ የሚችሉ ሁለት ሰባክያነ ወንጌል መቅጠር፣
- መምህራኑም ከናትሪ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ተነሥተው በየገጠሩ እየተዘዋወሩ እንዲያስተምሩ የሚያስችላቸው አንድ ፈረስና አንድ ሞተር ሳይክል መግዛት፣
- አብያተ ክርስቲያናቱን ከተመጽዋችነት ለማውጣት አነስተኛ ልማቶችን ማቋቋም፣
- የዶሮ ርባታ፣ የንብ ማነብ፣ ከዚሁ ጋር በተጓዳኝ አብያተ ክርስቲያናቱ በጋራ የሚጠቀሙበት መጭመቂያና ማሸጊያ ማሽኖችን በጋራ ማቆም እና
- የመስኖ ልማት መዘርጋት ሲሆን ለዚህም የውኃ ቴክኖሎጂ ኤክስፐርቶችን አስመጥተው አስጠንተዋል ...::

ናትሪ በርካታ ተአምራት በየጊዜው የሚፈጸሙበትም ቦታ ነው:: በአጥቢያ የነበሩ አንዳንድ ሙስሊሞች በቤተክርስቲያኑ ላይ የተለያየ የድፍረት ኃጢአቶችን ይፈጽሙ ነበር:: ታዲያ ቤተ ክርስቲያኑ ተዘግቶ በነበረበት ወቅት በአፀዱ ዙሪያ ሙስሊሞቹ ከብቶቻቸውን የሚያሰማሩበት፣ ቆሻሻ መጣያና መጸዳጃ አድርገውት ነበር:: የአጥቢያው ክርስቲያኖች ቢነግሯቸውም አልሰሟቸውም:: በተለይ አንዱ ሙስሊም በተደጋጋሚ ይህንኑ ተግባር ይፈጽም ነበር:: አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ውስጥ የራሱ በሬ ሰውዬውን ጥሎት እላዩ ላይ ቆመበት:: ሰውዬው ሲጮህ ሰው ተሰብስቦ በሬውን ቢደበድቡት፣ ቢጎትቱት ከሰውዬው ላይ ሊወርድ አልቻለም:: በኋላም ይሄ ከእግዚአብሔር የታዘዘ ነው ብለው ካህን ጠሩ:: በካህኑ ጸሎትም በሬው ለቀቀ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰውዬው ሽባ ሆኖ ቀረ:: እስከ ዛሬም ሽባ እንደሆነ በቤቱ ይገኛል:: «ቦታውን አርክሼው ነው:: ተጠምቄ ክርስቲያን መሆን አለብኝ» ሲል የአካባቢው ሙስሊሞች ክርስቲያን ከሆንክ አንተንም ቤተሰብህንም እናጠፋለን፣ ሀብትህንም እናወድማለን ስላሉት ፈርቶ እግዚአብሔር አንድ ቀን ያሳካልኛል ብሎ በተስፋ እየጠበቀ ይገኛል::

በናትሪ አካባቢ በስፋት የሚታየው ችግር በርካታ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የናትሪ ደብረ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በገጠር ቀበሌ የሚገኝ ነው:: ዙሪያውም በሙስሊሞች የታጠረ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ በአጥቢያው ያሉ ምእመናን በሚደርስባቸው ተጽዕኖ ቁጥራቸው እያነሰ በመሄድ ላይ ይገኛል:: የበጎ አድራጊዎች አለመኖርና የቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮችም ከአካባቢው የሚደርስባቸው ኢሰብአዊ በደል ለመቋቋም ከአቅማቸው በላይ በመሆኑ በየጊዜው ይሰዳዳሉ:: ይህም ቤተ ክርስቲያኑ የተሟላ የወንጌል አገልግሎት ለመስጠት እንዲሳነው ከማድረጉም በላይ በቀሩት ምእመናን ላይ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት እንዲያንዣብብ አድርጓል:: የማኅበሩ ሰብሳቢ አቶ ሙሉጌታ ለዚህ መፍትሔ ያሉት «ክርስቲያኖቹ በአካባቢው የመኖር ዕድል እንዲኖራቸው ክርስቲያን ባለጠሀብቶች ወደ እነዚህ አካባቢዎች የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ኢንቨስት ቢያደርጉ፣ የክርስቲያኖቹ ልጆች ቀዬአቸውን ለቀው አይሰደዱም:: ቤተ ክርስቲያናቸውንም በቅርበት ሆነው ማገልገል ይችላሉ» ብለዋል::

ሙስሊሞች የቤተ ክርስቲያኑን መሬት በማን አለብኝነት በመውሰድ ብቸኛ መጋቢያ በሩን /ደጀ ሰላሙን/ እና የበዓል ማክበሪያ ዐውደ ምሕረታቸውን ለከብት ገበያ ሥፍራነት ወስደውባቸዋል::

### ማጠቃለያ

በጅማ ሀገረ ስብከት የሚታዩ ችግሮች ፈርጀ ብዙ ናቸው:: ከመናፍቃንና ከእስልምና እምነት ተከታዮች በየጊዜው በሕዝበ ክርስቲያኑና በየአብያተ ክርስቲያናቱ ላይ እየደረሰ ያለው ጥቃት ሀገረ ስብከቱ ብቻውን የሚቋቋመው አይደለም:: ቅዱስ ሲኖዶስ፣ ምእመናንና በጎ አድራጊዎች ትኩረት በመስጠት የዜግነት ድርሻቸውን፣ ሃይማኖታዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ እየጠቆምን፣ በመከራ እየተሰደዱ ላሉ ምእመናንና የቤተ ክርስቲያን አካላት እንድረስላቸው እንላለን::✤



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# እናንተስ 'ሀብትንና ክብርን' ሹ፤ ሌላው ሁሉ አይታወቅም!

ዲ/ን ማለደ ዋስይሁን

እም መጽሐፈ አራዳ

በአንድ ወቅት አንድ ወንድሜ በክርስትና ሕይወቱ ዙሪያ እየተወያየን ሳለ በመኻል አንድ በእጅጉ ያስገረመኝን ገጠመኙን ነገረኝ:: ሁለት ወንድሞች አሉት:: ሁለቱም ፕሮቴስታንቶች እና ሀብታሞች ናቸው:: እርሱ ክርስቲያን ሆኖ ጸንቶ በመገኘቱ ይበሳጫሉ:: ታዲያ ሁል ጊዜ እርሱን ወደ እነርሱ ዓለም ለመሳብ የሚያነሡት መከራከሪያ ነጥብ ሃይማኖታቸውንና ሀብታቸውን ነው:: በእነርሱ ሐሳብ ያላቸውን ሀብት ያገኙት ፕሮቴስታንት በመሆናቸው ነው:: «ይህም የሃይማኖታችን ፍሬ ነው:: ጌታም ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ እንዳለ ይሄን ሀብት ያፈራነው በጌታ ኢየሱስ ስላመንን ነው» ይሉታል:: ይህ ወንድሜ ይኼን እንደ ነገረኝ ብዙ አሰብኩ:: በዓይነ ኅሊናዬ የታዩኝ በዚህ ሐስተኞች እንኳን በልተው ለማደር ሌትና ቀን በሚዞሩበት ዓለም ውስጥ በጽናት የቆሙ፣ የክርስቶስን ሕግና ትእዛዛት እየጠበቁ ለእነርሱና ለልጆቻቸው የምድር ሕይወት የሚያስፈልገውን ለማሟላት እየጣሩ ግን ፈተና የሆነባቸው ወንድሞቼና እኅቶቼ ናቸው:: የዘመናችን ፈታኝ የአውሬው ድምፅ ይሄ ነው:- «ለእኔ ብትሰግድ የምታየውን ሁሉ እሰጥሃለሁ»:: በርግጥ ጥቅሶችን ይጠቅሱልናል፤ መልእክቱ ምንድን ነው?

## የተዛባ ትርጉም

የእግዚአብሔር ልጅ የዳዊት ልጅ የተባለ /የሆነ/ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድረ እስራኤል የሚመጣበትን የተስፋ ቃል አይሁድ ይጠብቁበት የነበረው አንድምታ ምድራዊና ነጻነቱም የሥጋ እንደሆነ እያሰቡ ነበር:: ከእግዚአብሔር በቀር ሀብት ካልነበራት ድንግል ማሕፀን አድሮ በተዋረደ በረት ውስጥ መወለዱና በእረኞች ምስጋና በእንስሳት እስትንፋስ የታጀበው የጌታ ቀዳሚ ምጽአት በአይሁድ ተቀባይነት ያላገኘው ሀብተ ሥጋን ለመስጠት፣ ምድራዊ ንግሥናን ገንዘብ ለማድረግ ያነጣጠረ ባለመሆኑ ነው:: ለእነሱ በእጅጉ አስጨናቂው በሮማውያን የመጣባቸው ተዋርዶ እንጂ በእግረ አጋንንት መጠቅጠቃቸው አልነበረም:: ለእነርሱ ትልቁ ድህነት ለሮማ ቄሣሮች በሚያቀርቡት ግብር የመጣው ሥጋዊው ኪሣራ እንጂ ነፍሳቸው ለዲያብሎስ በምታቀርበው የኃጢአት ግብር የደረሰባት መራቆት አይደለም::

በዚህ ጉዳይ ጌታችን የመጣበትን ዓላማ ያልተረዱትና ለመረዳትም ዝግጁ ያልሆኑ የእስራኤል ወገኖች የክብርን ጌታ ሰቀሉት:: በምድር ካሉ ገዢዎች ነጻ የሚያወጣ ምድራዊ ብልጽግናንም የሚሰጥ መስሏቸዋልና «መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም» ቢላቸውም አላመኑም:: /ዮሐ.፲፰፥፴፮/ በዚህ ማስተዋል በጎደለው የተሳሳተ እምነት በይሁዳ ንጉሥ የነበረው ሄሮድስም ሰብአ ሰገል ሊገብሩለት የተጉለት ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ዙፋን የሚቀመጥ እንደሆነ አስቧል:: ለነበረው ምድራዊ ዙፋን በመስጋቱ የካህናት አለቆችና የሕዝቡን ጻፎች ሁሉ ሰብስቦ «ክርስቶስ ወዴት እንዲወለድ ጠየቃቸው::» /ማቴ.፪፥፬/ ይህ ምድራዊ ሐሳብ ለቤተ ልሔም ሕፃናት ዕልቂት ምክንያት ሆኗል:: እንዲህ ባለ በራስ መረዳት የተወሰነ ትርጉም ውጤቱ ይኸው ነው::

## ትምህርተ አበዊነ

ጌታችን ያስተማረው ትምህርት፣ የአባቶቻችንም ትርጓሜ ግን እንዲህ አይደለም:: በምድር ላይ የምድር ባዕለጸጎች ሳይሆን የምድር ድሆችን መስሎ «ባዕለጸጎችን ያሳፍር ዘንድ የዓለምን ከንቱ ነገር መረጠ» እንደተባለ በትሑት ሰብእና ተመላልሷል::

አንድ ጊዜ የተሰጠች የመላእክትና የሰዎች ሃይማኖት÷ መንፈስ የሆነች፤ ስለ መንፈሳዊውም ጸጋና ሀብት የምትናገር የመንፈሳውያን መንገድ እንጂ ስለሚያልፍ ስለሚጠፋ ምድራዊ ኑሮ የምትታመን አይደለችም:: ዋናው ትምህርቷም ምድራዊውን ነገር መናቅ በእርሱም አለመመካት ነው:: የጌታ መወለድ አይሁድ የፈለጉትን ምድራዊ ክብርና ብልጽግናና ደስታ ለመስጠት የተሰጠ ተስፋ ባለመሆኑ እነርሱን ቢያስከፋም መድኃኒታችን ግን መንፈሳዊ ለሆነው ጸጋና ሀብት ብቻ ሰዎችን በመጥራት ፴፫ ዓመት በምድር ላይ ተመላልሷል::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ ለአርአያነት ለአርባ ቀናት በምድረ በዳ በቆየበትም ጊዜ ድል ከነሳቸው አርእስተ ኃጣውእ መካከል መብልና ሥጋዊ ክብርን መሻት ዋናዎቹ ነበሩ:: «እነዚህን ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው»፣ «የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው» የሚሉት ቃላት የዲያብሎስን ሥራና ሐሳብ በቀጥታ የሚያመለክቱ የፈተና ቃላት ናቸው:: ሰይጣን የእግዚአብሔር በሆነው እውነተኛ ሃይማኖት ፋንታ በራሱ ሐሳብ ሰዎችን ለ0 ምራት የዓለምን መብል፣ ሀብትና ንብረት ማማለያ አድርጎ እንደሚያቀርብ ከዚህ በቀላሉ መረዳት ይቻላል:: /ማቴ.፬፥፩-፱/

የጌታን መምጣት ለሥጋቸው ብልጽግና እንደሆነ ያስቡ የነበሩት አይሁድ ብቻ ሳይሆኑ ከመካከላቸው አክብሮ የጠራቸውና የመረጣቸው ደቀመዛሙርትም ነበሩ:: የቅዱስ ዮሐንስና የያዕቆብ እናት ማርያም ስለ ልጆቿ ያቀረበችው የግራ አዝማችነትና የቀኛዝማችነት የሥልጣን ጥያቄ ምንጭ ይኸው የገነነ ምድራዊ ሐሳብ ነበር:: «እኛ ግን እስራኤልን እንዲቤዠ ያለው እርሱ እንደሆነ ተስፋ አድርገን ነበር. . . .» የሚለው የቀቢፀ ተስፋ ድምፅ እና «ጌታ ሆይ በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን?» በማለት ሐዋርያትና አርድእት ያቀረቡት ጥያቄ የዚሁ ጥማት መገለጫዎች ነበሩ:: /ሉቃ.፳፬፥፳፩ ፤ የሐዋ.፩፥፮/

ጌታ በምድር ላይ ያስተምር በነበረበት ዘመን እርሱን ሲከተል ከነበረው ሕዝብ መካከልም ቢሆን ብዙዎች ጌታ እንጀራን ባርኮ ባበላበት የጥብርያዶስ አካባቢ ተግተው ይፈልጉት ስለነበር ስለዚህ ሥጋዊ ፍላጎታቸው «የምትፈልጉኝ እንጀራን ስለበላችሁ ስለጠገባችሁ ነው» በማለት እውነተኛ መሻታቸውን ገልጦ ተናግሯል:: /ዮሐ.፮፥፳፮/ መድኃኒታችን ከሰይጣን፣ በመንፈስ ካልጠነከሩ ሐዋርያቱና ከተከተለው ደካማ ሕዝብ ጋር ከላይ በተጠቀሰው መልክ ሲታገል የነበረው ከዓለም ፍቅርና መመካት ሰዎችን ዋጅቶ የነፍስ አርነትን ለመስጠት ስለመጣ ነው::

ከዚሁም ጋር አያይዞ ለሕዝቡ እና ለሐዋርያቱ ምድራዊ ሐሳባቸውን ትተው ቅድሚያ ለሚሰጠው ዘለዓለማዊ እንጀራና ሀብት እንዲጨነቁ እንዲህ በማለት ገሥጾአቸዋል:: «ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ::» /ዮሐ.፮፥፳፯/ በኋላ ግን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ሂዱና አስተምሩ» ያላቸው ሐዋርያት በመንፈስ ሲጠነክሩ የሃይማኖታቸው ጸጋ እና ሀብት በብር የሚገኝ ስለገንዘብም የሚሰጥ እንደሆነ የሚያስብን ወገን ሁሉ «አንተ ከብርህ ጋር ጥፋ...» በማለት ይገሥጹ ነበር:: /የሐዋ.፰፥፳፩/ የዓለምን ሕዝብም «ብርና ወርቅ የለንም ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ ተነሣና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተመላለስ . . .» በማለት በጽናት አቁመዋል::/የሐዋ.፫፥፮/

ምእመናን ሐዋርያት የሰበሰቧትን ቤተ ክርስቲያን ይቀላቀሉ የነበሩት በእጆቻቸው ስለነበረው ብርና ወርቅ ሳይሆን የሚያመልኩት አምላክ ስለሚያድለው ሰማያዊ/መንፈሳዊ/ ሀብት ነበር:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ድሆች ስንሆን... » ብሎ እንደተናገረ ሀብት ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ስም በቀር ያከማቹት



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

የዚህ ዓለም ገንዘብ አልነበራቸውም:: /፩ቆሮ.፮÷፲/ጌታም «ብርና ወርቅ አት ያዙ...»/ማቴ.፲÷፱/ በማለት እንዳዘዛቸው ለብዙዎች የምድርን በረከት ከመስጠት ጋር ቤተ ክርስቲያንን አንፀዋል::

አይሁድም የክርስቶስ መምጣት የሥጋችንን መሻት ካልሞላ አንቀበልም በማለታቸው በወንጌል የመጣውን ዘለዓለማዊ ሕይወት እንዳላገኙ ሁሉ ዛሬም ተረፈ አይሁድ መናፍቃን በዚሁ በፍትወት ሐሳብ ሰክረው ሳለ በሥጋዊ ብልጽግና ምእመናን እየቀኑ የጥፋታቸው ታዳሚ እንዲሆኑ ስልት አድርገው እየተንቀሳቀሱ ነው:: ሰይጣን በተንኮሉ ያሳደረውን በምድር ሀብት የመበልጸግ ጽኑ የምኞት ዘር ከመናፍቃን ልብ ጋር አስማምቶ በመዝራት በምእመናን ልብ ውስጥ የአይሁድን ጥፋት እያበቀለ ነው:: «ክብራቸው በነውራቸው፣ ሆዳቸው አምላካቸው፣ ሐሳባቸው ምድራዊ ነው:: ...» /ፊል.፫÷፲፱/ በማለት ሐዋርያት በገሠጹት መንፈስ ውስጥ የሚመላለሱት መናፍቃን ዛሬም ስልታቸውን በመለዋወጥ በምድራዊ ሀብትና ንብረት፣ በመብልና በመጠጥ ምእመናንን በመደለል ወደ አጋንንት ዓለም እያስኮበለሉ ነው:: በመጽሔትና ጋዜጦቻቸው የለመለመ መስክ፣ የሚያስጎመጅ መብልና መጠጥ፣ ሕንፃና፣ ማራኪ የምድር ገጽታዎችን በማቅረብ የሚታወቁት የጅሆቫ የጥፋት መልእክተኞች በሃይማኖት ስም ይህን ማባበል እየተጠቀሙበት ነው:: በዓለማችን የካፒታሊዝም የፖለቲካ ሥርዓት መንፈስ ነው የሚባለው ፕሮቴስታንቲዝም ይህን መደለያ ስልት በማድረግ ድልድይ እንደሰበረ ጎርፍ ሊያስፈራራን ይሻል:: የዚሁ የፕሮቴስታንት የእምነት ድርጅት ክፍል የሆነው የብልጽግና ወንጌል አራማጆችም ጌታ ለብዙ ገንዘቡ ገንዘብ ያኘ፣ ለቤቱ የሚታይ ውበትና ዘመናዊነት፣ ለልብሱ ፋሽን እንደነበረው ሊሰብኩን መሞከራቸው ለጊዜው በምድር ላይ እንጀራ ያልጠገቡ ወንድሞችና እኅቶችን ምራቅ በማስዋጥ /በማስጎምጀት/ ልቡናቸውን ለማጨለም መሆኑ አያጠራጥርም::

ክርስቲያኖች ግን ከምንም በላይ አበክረው መረዳት ያለባቸው በክርስቶስ ክርስቲያን የተባልንበት ሃይማኖት ስለ ምድራዊ ሀብትና ንብረት የተቸረ፣ ያንንም ለማግኘት የተሰጠ አለመሆኑን ነው:: የምድር ባዕለጸጎች የሀብታቸውን ብዛት ያገኙት በውስጣቸው ስላለው ቀና ሃይማኖት ነው ብሎ ማሰብ ማሳሰብም በእጅጉ ወደ ጥፋት የሚወስድ የሥጋውያን የአኗኗር ስልት ነው:: በሚያስገርም ሁኔታም ስለመብል ስለ ሀብት ንብረት እያስላሰሉ መራመድ ወደ ቀደመው የባርነት ሕይወት መመለስ፣ የተሰጠንንም መንፈሳዊ ጸጋ በመናቅ እርሱንም ባለመሻት መኖር ነውና::

*ክርስቲያኖች ግን ከምንም በላይ አበክረው መረዳት ያለባቸው በክርስቶስ ክርስቲያን የተባልንበት ሃይማኖት ስለ ምድራዊ ሀብትና ንብረት የተቸረ፣ ያንንም ለማግኘት የተሰጠ አለመሆኑን ነው:: የምድር ባዕለጸጎች የሀብታቸውን ብዛት ያገኙት በውስጣቸው ስላለው ቀና ሃይማኖት ነው ብሎ ማሰብ ማሳሰብም በእጅጉ ወደ ጥፋት የሚወስድ የሥጋውያን የአኗኗር ስልት ነው::*

ከእውነተኛ የእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ መኖር ነው:: ክርስቲያኖች መንፈሳውያን ናቸው:: የሚኖሩትም በመንፈስና ለመንፈሳዊው ነገር ነው:: ክርስቶስ የምድርን ሀብትና ንብረት ሊሰጠን አልመጣምና:: የምድር ሀብትና ንብረትም የአማንያን የሃይማኖት ብቃት መለኪያ አይደለም:: እንደውም ስለ ዓለም ማሰብ ስለ ሥጋ ማሰብ ነው:: መጽሐፍ ደግሞ እንዲህ ይላል «ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው:: ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና» /ሮሜ.፰÷፮/:: የሥጋ የሆነው ሀብት ንብረት የመልካም ነታችን ፍሬ ሳይሆን እንደውም መልካም እንዳንሠራ ማነቆ/ወጥመድ/ በመሆን ከመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ያስወጣናል:: ጌታም «ለባለጠጋ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት ጭንቅ ነው» /ማቴ.፲፱÷፳፫/ «የዚህ ዓለም ሐሳብና የባለጠግነት መታለል ቃሉን ያንቃል...» /ማቴ.፲፫÷፳፪/ በማለት ይነግረናል::

ስለዚህ ክርስትና የዘለዓለምን ሕይወት የሚሰጥ እንጂ ተሰናክለን የምንወድቅበትን የዚህን ዓለም ሀብትና ንብረት ለምእመናን ለመስጠት የሚተጋ አይደለም::

ሀብት ንብረት የሰው ልጆች በተለያየ መንገድ ሊያገኙት ይችላሉ:: ሀብትን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ደክመው ሠርተው በላባቸው ሊያገኙ ይችላሉ:: በአንፃሩ ደግሞ በስርቆት ማለትም በማታለል፣ በንጥቂያ ወይም በስውር ከሌላው ወስደው ሊያከማቹ ይችላሉ:: ወይም በጥንቆላ፣ በዝሙት ... በመሳሰሉት የኃጢአት ሥራዎች ላይ ተመሥርተው የዚህን ዓለም ሀብት ሊያከማቹ ይችላሉ:: በዚህም ምክንያት በምድራችን ላይ ሀብት ንብረትን የተጠመቁም ያልተጠመቁም፣ ክርስቶስን የሚያውቁም የማያውቁም ተቀራምተውት ይገኛሉ:: ሕዝብም አሕዛብም በምድር ላይ የሚኖሩትና ሥጋውያን በመሆናቸው በጽድቅ ወይም በኃጢአት መንገድ የምድርን መብልና መጠጥ /ሀብት ንብረት/ ይሰበስባሉ:: በየትኛውም መንገድ መጥቶልን ለእኛ ብቻ እስከተጠቀምንበት ድረስ የሚጠቅመው ሥጋን ነው:: ሀብት ንብረትን ሰዎች ሠርተው እንዲያገኙ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆንም የሚያልፍ በመሆኑ በዚያ መመካት ግን አይመከርም:: የዓለም ሀብት ስላላቸው ብቻ በነፍስ የሚሞቱ ይኖራሉ አይባልም፤ በኃጢአት የሚመላለሱ ድሆች በዓለም ነበሩና:: የዓለም ሀብት ስለሌላቸውም በነፍስ ነዳያን ይሆናሉ አይባልም፤ ከትሑት ሰብእና ጋር ብልጽግናና ክብርን ይዘው በሕይወት መንገድ የተመላለሱ ባዕለጸጎች ነበሩና የዓለም ሀብት ለኃጢአትም ለጽድቅም ምክንያት የሚሆን፤ ነገር ግን ኃላፊ ጠፊ የሆነ፤ ከምድር የተገኘና በምድርም የሚቀር ነው /፩ቆሮ.፯÷፴፩/::

ስለዚህ የዚህ ዓለም ሀብት ንብረት ከቅድስና የተነሣ የተሰጠ የሃይማኖት ፍሬ አድርጎ እየተመኩ መናገር የሚያዋጣ አይደለም:: ይልቁንም ወንጌል ፍጹምነትን ለማግኘት ለሚወድ ሰው የምትመክረው «ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ...» በማለት ነው /ማቴ.፲፱÷፳፩/:: ነገር ግን ሀብት ባለበት በዚያ እግዚአብሔር አለ ብሎ መስበክና ማስተማር ያስተዛዝባል፤ ያስጠፈርዳልም:: ይህ ዓይነቱ አካሄድ ሰዎች ስለነፍሳቸው እንዳይጨነቁ በማድረግ በፍትወተ ሥጋ እንዲደነዝዙ እንዳያስተውሉም ተጽዕኖ የሚያሳድር የአጋንንት ሴራ ነው:: ወንጌል አሁንም «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል፤ ሰውስ ስለነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?» /ማር.፰÷፴፮/ እያለች ከሥጋ ይልቅ ለነፍሳችን መዳን እንድንቆም ታስጠነቅቃለች:: «ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በሚሠረቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ:: ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት፣ ሌቦችም ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና» /ማቴ.፮÷፳/:: በማለት ሀብትን በመሰብሰብ እንዳንመካ፤ እንዳንሰናከል በት፤ ይልቁንም ለነፍሳችን የሚበጅ መልካም ሥራን እንድናበዛበት ትመክረናለች::



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ሐዋርያውም ሀብት ንብረት፣ መብል መጠጥ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ወይም ከእግዚአብሔር መንግሥት ለመውጣት መፈራረጃ እንደ ማይሆን ሲያስረዳ «የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅ፣ ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችም» ይላል፡፡ /ሮሜ.፲፬÷፲፯/

ክርስቲያኖች ስለሚበሉት ስለሚጠጡት ለልጆቻቸው ስለሚያወርሱት ሀብት በመጨነቅ ከአምላካቸው መንገድ መውጣት እንደሌለባቸው ጌታ አስተምሯል፡፡ በጎደለን እንዲሞላ፣ በጠፋብን እንዲተካ ጌታን በእምነት መለመን መልሱንም በትዕግሥት መጠባበቅ ይገባናል፡፡ «ስለነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት ወይም ስለ ሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ፤ ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ አይበልጥምን... ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል» /ማቴ.፮÷፳፭-፴፫/ በማለቱ መድኃኒታችን ስለዘለዓለማዊ ሕይወታቸው በቅድሚያ ተግተው የሚሹትን የጎደላቸውን የምድር በረከት ሊሞላ የታመነ ነው፡፡

ለዚህም ምስክር የሚሆነን ጌታ ለሐዋርያቱ ስለሕዝቡ እንዲህ ሲል የተናገረውን ከወንጌል እናነባለን፡፡ «ሕዝቡ ከእኔ ጋር እስካሁን ሦስት ቀን ውለዋልና የሚበሉት ስለሌላቸው አዝንላቸዋለሁ፡፡ በመንገድም እንዳይዝሉ ጦማቸውን ላሰናብታቸው አልወድም አላቸው»/ማቴ. ፲፭÷፴፪/፡፡

ይህም ብቻ ሳይሆን በምድር ላይ በማንም ላይ እንዳንከብድ፣ ተግተን በመሥራት በላባችን ባገኘነው ውጤት እንድንጠቀም የእግዚአብሔርም ፈቃድ ነው፡፡ ሐዋርያው «ከእናንተ ዘንድ በአንድስ እንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን በድካም፣ በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም ... ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና. . .» በማለቱ ይታወቃል /፪ኛ ተሰ.፫÷፮-፲፫/፡፡ ከሀብት ንብረት ወጥመድ አምልጠው ለክብር ስለሚበቁ፤ በእውነት ሠርተው፤ ከሀብት ንብረታቸውም ዐሥራት በኩራት አውጥተው፤ የተቸገረን ረድተው፤ ወልደው ከብደው፤ ለልጆቻቸው አውርሰው፤ የሃይማኖትና የሥራ አርአያነታቸውን ትተው በሰማይ መዝገብ ስለሚሰበስቡ እና የሁለት ዓለም ዕድለኞች ስለሆኑ ክርስቲያን ባዕለጸጎች ጌታ እንዲህ ይላል «የዚህ ዓለም ልጆች ለትውልዳቸው ከብርሃን ልጆች ይልቅ ልባሞች ናቸው፤ እኔም እላችኋለሁ የዓመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘላለም ቤቶች እንዲቀበሏችሁ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አኑሩ፡፡» /ሉቃ. ፲፮÷፰-፱/

**ሀብት ባለበት በዚያ እግዚአብሔር አለ ብሎ መሰበክና ማስተማር ያስተዛዝባል፤ ያስፈርዳልም፡፡ ይህ ዓይነቱ አካሄድ ሰዎች ስለነፍሳቸው እንዳይጨነቁ በማድረግ በፍትወተ ሥጋ እንዲያነዝዙ እንዳያስተውሉም ተጽዕኖ የሚያሳድር የአጋንንት ሴራ ነው፡፡**

### ተዐቀቡኬ...

ይህን ሁሉ ከማድረግ አልፈን ግን የእግዚአብሔርን መንገድ በሚያናንቁ የምድር ባዕለጸጎች በመቅናት መናወጥ የለብንም፡፡ የጎደለብንን ሀብትና ንብረት፣ መብል መጠጥ ለማሟላት ሃይማኖትን መለወጥ፣ በጥንቆላ፣ በሌሎችም የርኩሰት ሥራዎች ውስጥ መኖር፤ የሚያመልኩትንም አምላክ ማማረር የሰማይን አምላክ ተስፋ ከሚያደርጉ ክርስቲያኖች አይጠበቅም፡፡ ይህም ጌታ በወንጌል «እናንተ እምነት የጎደላችሁ እንጀራ ስለሌላችሁ ስለምን እርስ በእርሳችሁ ትነጋገራላችሁ? ገና አታስተውሉምን?» እንዳለ በፊቱ እምነት ማጣት፣ ማንጎራጎርና አለማስተዋል ይሆናል /ማቴ.፲፮÷፱/፡፡ ሌላው ቀርቶ በምድር ላይ ባለ የሽሚያ ሕይወት ባይቀናን፣ በሥጋዊ ጉስቁልና ብንመላለስ እንኳ ሠለስቱ ደቂቅ «የምናመልከው አምላካችን ከሚነደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፡፡ ከእጅህም ያድነናል፡፡ ባያድነን አማልክትህን እንዳናመልክ፤ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት ዕወቅ» በማለት የያዙትን የእምነት አቋም በልብ ማኖር ያስፈልጋል /ዳን.፫÷፲፯/፡፡

ነገር ግን በሥጋዊ ድህነት ምክንያት መናፍቃን ላቆሙት ጣዖት ሰጋጅ፣ አጋንንት ላዘጋጁት ወጥመድ ሰለባ ከሆንን የጻድቁ ኢዮብና የምስኪኑ አልዓዛር አምላክ ያፍርብናል። /ኢዮ.፩÷፳፤ ሉቃ.፲፮÷፲፱/፡፡ ክርስቲያኖች ራሳችንን ማስተያየት ያለብን በዘመናችን ካሉ በኃጢአት ከበለፀጉ ምድራውያን ሳይሆን «ሁሉን ትተን ተከተልንህ» ካሉ ሐዋርያት ኑሮ ጋር ነውና /ማቴ.፲፱÷፳፯/፡፡ ክርስትና ሃይማኖትን ለሀብት ማግኛነት የተቀበለው ሲሞን መሠርይ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ለድኅነት ሳይሆን ለሀብት ሃይማኖታቸውን የሚለውጡት ሁሉ የሚመላለሱበት መንገድ የሃይማኖት አለመሆኑን መገንዘብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለእኛ «አስቀድማችሁ ጽድቁንና መንግሥቱን ሹ፤ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል» የሚለው ትምህርት ሕይወት አለው፡፡ ለእነርሱ ግን ሁሉ ነገር «አስቀድማችሁ ሀብትንና ክብርን ሹ፤ ...» የተባለ ይመስላል፡፡ ስለዚህ ወዳጆች ሆይ በ«አራዶች መጻሕፍት» ጥቅስ ልቡናችን አናድክመው፤ ይልቁንም ይህን ከመሰለው ፍትወት እንጠበቅ፡፡ /ተዐቀቡ!/፡፡ ❖

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*


ከሰሜን አሜሪካ ምን ይደመጣል?
መካነ ድር /website/
http://www.mahiberekidusan.org
www.tewahedomedia.org

ሬደዮ
ለኢትዮጵያና አካባቢዋ
17.690 MHz አጭር ሞገድ
ዘወትር ሰኞ
ከምሽቱ 4:00-5:00
(10pm-11pm)

አትላንታ
860 AM
WAEC
Sundays
7:30 pm - 8:00 pm EST

ዲሲ
1390 AM
Abyssinia Radio
Saturdays
7pm - 7:30pm EST

ዴንቨር
670 AM
KLT Radio
Sundays
8:00 pm - 9:00pm EST




©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

## «ለችግሩ መፈጠር...»

ልጆች የሚያውቁት የአሁኑን ነው:: ሲያድጉም ይህንኑ ተቀብለውት ይጓዛሉ:: በኋላም የበለጠ እያሳደጉት ይሄዳሉ እንጂ የእኛ የምንለውን ለመማርም፣ ለመስማትም ጊዜ አይኖራቸውም፤ ጆሮአቸውንም አይሰጡም:: የእኔ ፍርሃት ከዚህ ይጀምራል:: በአሁኑ ወቅት ወደዚህኛው ተመለሱ ትክክለኛው ይሄ ነው የሚል ጠቋሚ የለም::

የሌሎቹን የእምነት ድርጅቶች ስናይ እንደፈለጉ ቢሆኑም ይሄኛው እኮ ከዚህ ጋር ይጣረስባቸዋል የሚል ነገር የለውም:: የእኔ ፍርሃት ዛሬ ዝም ተብሎ የተለመደ ልማድ ነገ ሕግ ይሆናል በኋላም ወደ ጽሑፍነት ይቀየራል:: ከዛም ቤተክርስቲያን በዚህ ነው መመራት ያለባት የሚል ትውልድ ይፈጠራል:: ነገ ዲያቆን፣ ካህን... የሚሆነው ይህንን ሂደት እየተከተለ፣ እያራገበ፣ እያጨበጨበ፣ እልል እያለ የሚሄድ ሰው ይሆናል:: የቀጠድሞዎቹ አባቶች ባለፉበት ወንበር የሚተካው ይህንኑ አጽንቶት ነው የሚሄደው:: ስለዚህ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን ከአሁኑ መሆኑን ማስገንዘብ አለብን:: ልማድ ሕግ እንዳይሆን ነው ፍርሃቴ::

*ሐመር፡-* ትክክለኛው ክፍተት የተፈጠረው ምኑ ላይ ነው?

*መ/ር ዘመድኩን፡-* ለምሳሌ እኔን ብትወስዱ ወንጌል ከመማር በዘለለ የዜማ ትምህርት የለኝም:: ግን ዛሬ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ካህናቱ ሳይቀሩ እየመረጡ የሚዘምሯቸውን ደርሼ ለዘማርያን የሰጠኋቸው መዝሙሮች አሉኝ:: ዜማ ደርሻለሁ:: እነዛ ዜማዎች ደግሞ ተመራጮች ናቸው፤ ይዘመራሉ:: ይህ ሁኔታ አዲስ ስለሆነ ነው ችግሩ የሚፈጠረው:: በተለይ ቀደም የነበሩት ዘማርያን ዜማዎቹን የወሰዱት ከዜማ መጻሕፍት አውጣጥተው የታወቁ የግእዝ ዜማዎችን ነው:: በኋላም በአማርኛ አዘጋጅተው ዘመሯቸው:: መሪጌታ ፀሐይ እና ኪነ ጥበብ ወልደ ቂርቆስን መጥቀስ ይቻላል::

ከ፲፱፻፹ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ያሉት ሰዎች የሠሯቸው መዝሙራት መነሻ የሆነ ነገር ይኖራቸዋል እንጂ አዲስ ግኝት ነው:: በዚህ አዲስ ግኝት ውስጥ ደግሞ የቀድሞዎቹን የዜማ ሥርዓት የመጠበቅ ነገር የለም:: ከልቡ የሚፈልቀውን፣ በአእምሮው የሚመስለውን ነገር አውጥቶ ያዘጋጃል::

*ሐመር፡-* አንዳንድ አሳታሚዎች ከገበያ አንፃር ከንስሐ መዝሙራት ይልቅ ሞቅ ያሉ የቸብቸቦ መዝሙራት የሚመርጡበት ሁኔታ ይታያል:: እርስዎ ይህን እንዴት ይመለከቱታል?

*መ/ር ዘመድኩን፡-* የእኔ መዝሙራት ከመጀመሪያዎቹ ጋር ይመሳሰላሉ:: እኔ መዝሙር መድረስና ማሳተምን በመጀመሪያዎቹ

ከገጽ ፲፬ የዞረ

ዓመታት እንደ ሥራ ዘርፍ ነበር የቆጠርኩት:: ክብሮ ይግባበት፣ ዕል ልታ ጭብጨባ ይኑረው እንጂ እኔ ምንም አይመስለኝም ነበር:: በኋላ ግን መጠንቀቅ ጀመርኩ:: መፍራት የጀመርኩት ገቢዬን ይዘጋል ከሚል አንፃር ሳይሆን የስሕተት ሐውልት እንዳላቆም በሚል ነው:: ያ ፍርሃት ወደ መጠንቀቅ ወሰደኝ:: መጠንቀቁም መዝሙር ለማሳተም ዓመታትን እየወሰዱብኝ መጡ:: ከበሮ፣ ጭብጭባ የሌለው መዝሙር አይሸጥም ይባላል:: እኔ ግን በፍቅር ስለምሠራ በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ሳሳትም አጃቢ፣ እልልታ ጭብጨባ የለውም:: ስለዚህ ልጁን /ዘማሪውን/ ብቻውን አንዳንድ ከበሮ በሚገባበት ቦታ በማድረግ ከበሮ አደረግሁ:: አቀራረቡ በጥሩ ሁኔታ ስለነበር ተሸጠ:: ከሕዝቡ ያገኘሁት ምላሽም «ሰላም አገኘን:: ሁከት ጠፋልን» የሚል ነበር::

*መዝሙሩም*

*የቤተክርስቲያኒቷ ፈርጀ ብዙ ችግር ነጸብራቅ ነው:: የመዝሙር ችግር ኢምንት ነው፤ ትልቁ ችግር ያለው ሌላ ቦታ ነው:: ችግሩን ለመፍታት በጠረጴዛ ዙሪያ ተሰባስበን መወያየት አለብን:: ለችግሩ መፈጠር ሁላችንም ተጠያቂ መሆናችንን መረዳት አለብን:: የችግሩ ተጠያቂ አንዱ እኔ ነኝ:: ነገር ግን የሚጠይቀኝ አካል የለም:: ስለዚህ የሰው ጠያቂ ቢጠፋ ደግሞ መድኃኔዓለም ይጠይቃል፤ መጠየቁም አይቀርም::*

እንዲህ ደግሞ ፀጥ ያለ ነገር ሲመጣ ግጥሙ መልእክቱ ጐልቶ ይሰማል:: ለምሳሌ እኔ እስከ አሁን 'ቋንቋዬ ነሽ' የሚለውን መዝሙር እንደ አዲስ መዝሙር እሸጠዋለሁ፤ ሦስት ዓመቱ ነው:: ከዚህ አንፃር የትኛውንም ሥራ ስሠራ ከገበያ አንፃር አላየውም፤ ለምእመኑ ከሚያስተላልፈው መልእክት እንጂ:: ቋንቋዬ ነሽን ለመሥራት ፩ ዓመት ከ፮ ወር የጥናት ጊዜ ፈጅቶብኛል:: መዝሙሩን ካዘጋጀሁ በኋላ ዘማርያን፣ የመዝሙር ቤት አሳታሚዎችን አምጥቼ እንዲመለከቱት አደርጋለሁ:: ካሴት አዟሪዎችን ለዚህ የተለየ ዕውቀት ባይኖራቸውም እንዲሰሙት አደርጋለሁ:: ከመዝሙር ጋር ግንኙነት የሌላቸውን ሰዎችም አሰማቸዋለሁ:: አስተያየታቸውን ይሰጡኛል:: እኔ ያላየሁበትን አንፃር ይነግሩኛል:: ስለዚህ እኔ ለእነዚህ ሰዎች አሳይቼ፣ ጨምቄ፣ ከባለስቱዲዮም ጋር ተነጋግሬ፣ ደክሜ ነው የማዘጋጀው:: ስለዚህ እኔ መዝሙር ሳዘጋጅ ጊዜ ወስጄ፣ በጥሩ ሁኔታ ስለሚዘጋጅ የንስሐ፣ የቸብቸቦ የሚለው እኔን አያስጨንቀኝም::

*ሐመር፡-* መፍትሔው ምንድን ነው?

*መ/ር ዘመድኩን፡-* መፍትሔ የሌለው ነገረ የለም:: ችግሩን መፍታት የምትችለው ቤተክርስቲያን ራሷ ናት:: ቤተክርስቲያን አንድ ማዕከል ብታቋቁም ጥሩ ነው:: ቤተ ክርስቲያን የዘማርያኑን የግጥምና ዜማ ደራስያን ብሶት የሚሰማ አንድ ቡድን ማቋቋም ይጠበቅባታል:: ይህ ከተቋቋመ ግን በዚህ አሠራር ውስጥ አልገባም፤ ለሥርዓተ ቤተክርስቲያን አልገዛም የሚለው አካል ማን እንደሆነ ይታወቃል:: ነገር ግን ለዚያ ደረጃ የሚመጥንስ፣ በዚያ መስመር ያለፈውስ ሰው ማነው?

ስለዚህ የዘመናዊ አስተዳደር ሁኔታ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ እስከሌለ ድረስ ተጠያቂነት አይኖርም:: ለመሆኑ ማነው ተጠያቂነትን የለመደው? ሥርዓቱስ አለ ወይ? ስለዚህ ዘመናዊ አስተዳደርና ተጠያቂነት በሁሉም ዘርፍ እስከሌለ ድረስ፤ «እከሌ የሚያጠፋው እንዲህ... ስለሆነ ነው፤ የቤታችን ገመና ነው፤» እየተባለ የሚቀጥል ከሆነ በመዝሙሩም ላይ ለምን ጫና ይበዛበታል? ስለዚህ በመዝሙር ላይ ብቻ ሳይሆን ቤተክርስቲያኒቷ በሁሉም ዘርፍ ራሷን ማሳደግ አለባት:: መዝሙሩም የቤተክርስቲያኒቷ ፈርጀ ብዙ ችግር ነጸብራቅ ነው:: የመዝሙር ችግር ኢምንት ነው፤ ትልቁ ችግር ያለው ሌላ ቦታ ነው:: ችግሩን ለመፍታት በጠረጴዛ ዙሪያ ተሰባስበን መወያየት አለብን:: ለችግሩ መፈጠር ሁላችንም ተጠያቂ መሆናችንን መረዳት አለብን:: የችግሩ ተጠያቂ አንዱ እኔ ነኝ:: ነገር ግን የሚጠይቀኝ

ወደ ገጽ ፴፫ ዞሯል



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

## «መንበረ ፓትርያርኩ ...» ከገጽ ፲፫ የዞረ

ማንም አምልጦንም አይደለም። በአጭሩ ለሚመለከተው አካል ትጽፋለህ፤ የሚመለከተው አካል ያስቆመዋል፤ በአንድ ቀን። በዚህ ጉዳይ ግን አልሔድንም። እንዳንሔድ ያደረገን ጉዳይ ምንድን ነው? ሰዎች ቅልጥ ወዳለ ዘፈን ከሚሔዱ ይልቅ ወደ መለስተኛ ዘፈን እንኳ ቀርበው ትንሽ ወደ መንፈሳዊነት እየቀረቡ እንዲሔዱ ብለን አስበን እንጂ እነርሱን ለማቆም አቅቶን አይደለም። ስለዚህ ለገንዘብ ነው የሚሉን ካሉ ገንዘቡም ዕውቀቱም፣ ሕጉም ያለው እዚህ ስለሆነ አምጡ ለማለትም እንችላለን። ዐሥራትና በኵራት መስጠት ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዝ ነው።

*ሐመር፦ ዘማርያንና አሳታሚዎች እንደሚናገሩት ማዕከላዊ አሠራርን ለማምጣት ተሰብስበን ብንመጣም መምሪያው ትኩረት አልሰጠንም፤ በመሆኑም ሁሉም በየፊናው ለማዘጋጀት ተገዷል ይላሉ፤ በዚህ ላይ ያለዎት አስተያየት?*

መ/ር ዕንቈ ባሕርይ፦ በርግጥ ተሰባስበው ነበር። ለዚህም ሁላችንም ትኩረት አድረገናል። ከዚያም በሕግና በሥርዓት ሒዱ ተባሉ። እነርሱ ግን አልሔዱም። በራሳቸው አፈንግጠው የራሳቸውን ፕሮግራም አውጥተው ሔዱ። ያ እንዲቆም አድርገናል። ምክንያቱም መስማማት በሌለበት ሁኔታ እየተጓዙ ስለሆነ ነው። አሁንም እንኳ ሕጋዊነቱ እስካለ ድረስ በአግባቡና በሥርዓቱ መምጣት ይችላሉ።

በሌላ በኩል ስናየው የእነርሱ ደራስያን እነማን ናቸው? መዝሙር የሚደርስላቸው የትኛው የዶግማ ምሁር፣ የትኛው በቤተክርስቲያን ዜማ ልክ የሚሔድ ነው? ማነው? ዝም ብለው ከየትም ገዝተው እያመጡ ነው። ስለዚህ ያንንስ እኛ ሥርዓቱን የጠበቀ ነው ብለን መቀበል እንዴት እንገደዳለን? ሊቃውንት ያዩት፣ ያሹት፣ ያበሰሉት ቢሆን ኖሮ ትክክለኛ መዝሙር ነው ብለን እንቀበላለን። ስለዚህ መዝሙር ነው እያሉ የተገኘውን ማግበስበስ በቤተ ክርስቲያኗና በቅዱስ ያሬድ ስም ማፌዝ ይመስላል። ዝም ብለው እንደ አቅማችን እናገልግል ካላሉ በስተቀር 'ያሬዳውያን ነን' ወይም ደግሞ 'እኛ ያቀረብነው መዝሙር የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ነው' ብለው ራሳቸውን የሚክቡ ካሉ ሐዋርያው እንዳለው የቆሙ ቢመስላቸው እንዳይ ወድቁ ይጠንቀቁ እንላለን።

*ሐመር፦ የአንዳንዶች ሥጋት ደግሞ ማደራጃ መምሪያው ሥርዓት ባስከብር ብሎ ቢነሣ እንኳን ከገዳማትና ከአድባራት አስተዳደር አካላት ጋር በመወዳጀት የተፈለገውን ነገር ማድረግ ስለሚቻል መምሪያው አቅም አይኖረውም። ማስከበርም አይችልም ይላሉ፤ እውነት ነው?*

መ/ር ዕንቈ ባሕርይ፦ "የተፈለገው መግባባት ይኑር፤ አቅሙና ዕውቀቱ ከዚያም በላይ ደግሞ ውክልናው ያለው ግን ማደራጃ መምሪያው ነው። ማደራጃ መምሪያው ከአቅሙም በላይ ሲሆን እኮ ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው የሚያቀርበው።

ከላይ እንደጠቀስኩት ማቆሙ ስከንድ አይፈጅም። ማቆም ግን በራሱ ውጤት አይደለም፤ እኛ የምንፈልገው ሰዎችን ወደ ተሻለ ሕይወት ማቅረብ ነው። ለቤተክርስቲያን ወደ ተሻለ ሕይወት እንዲመጡ፤ በነፍሳቸውም በሥጋቸውም እንዲጠቀሙ እንፈልጋለን። ለዚህም የምንመኘው ተደራጅተው ወደ እኛ እንዲመጡ ነው።

ምእመናን ሁላችን ቅዱስ ያሬድን፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ነው» የምንል ከሆነ በሥርዓትና በሕግ መሔድ አለብን። እኛ የዘገየን ብንሆን እንኳን እንድን ፈጥን ከእኛ ጎን መቆም አለባቸው እንጂ በዚያኛው ጎራ ሆነው ቀረርቶውን ሁሉ መዝሙር እያሉ እየተቀበሉ ከሔዱ ትክክል አይደለም።

*ሐመር፦ ማዕከላዊ አሠራሩን የሚደግፉ እንዳሉ ሁሉ፤ የሚፈሩም አሉ። መምሪያው በጊዜ ግጥሙንም፣ ዜማውንም ገምግሞ ለማድረስ አይችልም። በአገልግሎቱ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል የሚሉ አሉ። ሌሎች ደግሞ ማዕከላዊው አሠራር የሚሰፍን ከሆነ ለሙስናም በር ይከፍታል ይላሉ። ሥርዓት ያልጠበቁ መዝሙሮችም የሚወጡበት ዕድል ይኖራል ብለው የሚሰጉም አሉ።*

መ/ር ዕንቈ ባሕርይ፦ ማዕከላዊነቱን ማስጠበቅ የሚለው ጉዳይ ለእኛ እንግዳ አይደለም። ማዕከላዊ አሠራርን ማምጣትም ይቻላል። አቅሙም ኢኮኖሚውም አለ። እሱ ብቻ አይደለም እጅግ ዘመናዊ የሆነ ስቱዲዮ በማዕከል እንዲዘጋጅም እናስባለን። እርሱም በሒደት ላይ ነው።

> *መዝሙሮቹ ተራ ጩኸት ሳይሆኑ የቅድስና መዝሙሮች መሆን አለባቸው። ለምሳሌ በቤተክርስቲያናችን አንድ ንዋየ ቅድሳት ሲገዛ ለዚያ የሚገባ ጸሎት ካልተጸለየበት በስተቀር ወደ ቤተክርስቲያን አይገባም። እንደዚሁ ሁሉ በአሁኑ ወቅት ያሉ መዝሙሮች ዝም ብሎ ገጣሚ ስለገጠመው ብቻ መዝሙር ልንላቸው አንችልም። ሌላ ስም ካልተሰጣቸው በቀር።*

ወደ አፈጻጸም ደረጃም ተደርሷል። የኦዲዮ ዕቃዎች በሙሉ ከቴክኖሎጂ አንጻር አሁን መሔድ ስላልቻሉ በአዲስ /በዲጂታል/ መተካት አለባቸው የሚል ሐሳብ ቀርቦ ጥናት እየተካሄደበት ስላለ ነው። ይህ ደግሞ ቅዱስነታቸው ይዘውት ነው ያለው።

ማዕከላዊነት ከመጣ ሙስና ይሰፋል ስለሚሉት ነገር ምናልባት እነርሱ በሚያውቁት ቋንቋ ቢመልሱት ይሻላል። በቤተክርስቲያን ሙስና የሚባል አናውቅም፤ የለምም። ቤተክርስቲያን የምታስተምረው ኃጢአት አትሥራ ብላ ነው። ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ ብላ ታስተምራለች እንጂ ገንዘብ አምጣ አትልም።

*ሐመር፦ ለእነዚህ ሁሉ ችግሮች መፈጠር ክፍተቱ በእርግጥ የትጋ ነው? ተጠያቂውስ ማነው? መምሪያው ነው?*

መ/ር ዕንቈ ባሕርይ፦ ለክፍተቱ ተጠያቂ ክፍተቱን የፈጠረው አካል ነው። ቤቱ መሥራት ያለበትን እየሠራ ነው። ምናልባት ገበያ አውጥተህ ካልሸጥክ ካልተባለ በስተቀር ይህንን ችግር ለመቅረፍ በዋናነት የሚያግዙ የአብነት ትምህርት ቤቶችን እያደራጀ ነው።

ቤተክርስቲያንም አቅሟ በፈቀደ መጠን እያስተማረች ነው። ምእመናንን እያስተባበረች በየአቅጣጫው ዝማሬ መዋስዕቱ፣ አቋቋሙ፣ ድጓው፣ ጾመ ድጓው፣ ምዕራፉ፣ የቃል ትምህርቱ፣ ላይ ቤቱ፣ ታች ቤቱ፣ ሳንኳው፣ ... በሙሉ ሥርዓቱን ጠብቆ እየሔደ ነው። እነዚህ አገልግሎቶች በየአብያተ ክርስቲያናቱ እየተካሔዱ ነው።

ዛሬ ግእዝ ፫ኛው ሺሕ ድረስ እየተሸጋገረ ነው ያለው፤ ይህ የሆነው ትናንት በተነሡ «መዝሙረኞች» አይደለም። ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሆኑ ብራናዎች በሙሉ ጽፉ ያቆየች ቤተክርስቲያን መሥራት ያለባትን እየሠራች ነው።

*ሐመር፦ በመምሪያው የተዘጋጁ መዝሙሮች እስከ አሁን ሳይታተሙ የቀሩት ለምንድ ነው?*

መ/ር ዕንቈ ባሕርይ፦ ምክንያቶቹ ሁለት ነገሮች ናቸው። አንደኛ ማደራጃ መምሪያው ካለው አቅም አንፃር በጀት ጠይቆ ማስፈቀድ አለበት። በራሱ የሚያደርገው ነገር የለም። ሁለተኛው የእኛ ዕቅድ በስፖንሰርነት እንኳ ቢሆን በዓመት ቢያንስ ስድስት ካሴት ለማውጣት ነበር። ይሔ በራሱ በቂ አይደለም፤ ከዚሁ በተጓዳኝ በዜማም ተዘጋጅቶ መውጣት አለበት። ቤቱ /መንበረ ፓትርያርኩ/ አምኖበት እንዲታተም ፈቅዷል፤ በቅርብ ቀናት ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል።

*ሐመር፦ መምሪያው ለሰንበት ት/ቤት ወጣቶች የአሠልጣኞች ሥልጠና ሰጥቶ ያለገንዘብ እንዲደርሳቸው ለምን አያደርግም?*

መ/ር ዕንቈ ባሕርይ፦ እሱን ደግሞ የፈራነው ነገር አለ። እንደርሱ ብናደርግ ሰዎች ወስደው ሊያሳትሙት ይችላሉ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የሚል ስጋት አለን:: በዚህም የተነሣ ፍርድ ቤት ለፍርድ ቤት ስንካሰስ መዋል አንፈልግም::

*ሐመር፦ የመጨረሻ አስተያየትና መልእክት ካለዎት?*

*መ/ር ዕንቈ ባሕርይ፦* ማደራጃ መምሪያው የሚለው መዝሙረ ማኅሌት መጽሐፍ በቅርብ ቀን ይወጣል:: መጽሐፉን እንድንገለገልበትና ለማስተማሪያም እንድንጠቀምበት ስለሆነ ልናስብበት ይገባል:: ሌላው ደግሞ አሁንም ማዕከላውያን መዘምራን በየአቅጣጫው እያስተማሩ ነው ያሉት:: ለወደፊቱ ዕቅዳችን እስከ ክፍለ ሀገር ድረስ እንዲደርስ ነው::

በሌላ በኩል ከሕግ ውጪ ሆነው በዘፈቀደ የሚንቀሳቀሱ ሰዎችንም የቤተ ክርስቲያን ልጆች ናቸውና፤ እንደ ቤተ ክርስቲያን ልጅነታቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን ቀርበው የጎደላቸው ነገር ካለ ተስተካክሎ በሥርዓትና በአግባቡ ማገልገል እንዲችሉ መልእክት አስተላለፋለሁ::

ሌላው ምእመናን ቅዱስ ያሬድን ማወቅ አለባቸው:: ቅዱስ ያሬድን አወቅ ነው ማለት ደግሞ ዜማውን እንጠብቃለን፤ እናከብራለን ማለት ነው:: ስለ ዚህ የሚያውቁትን ያህል ሊያከብሩትና ሊሳሱለት ይገባል:: በዓለም ለ፲፮፻ ዓመት የዘለቀ ዜማ ከኢትዮጵያ በስተቀር ያለው የለም::

ያሬድ መባሉ ብቻ በቂ አይደለም:: እውነት እንነጋገር ከተባለ ቅዱስ ያሬድ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሦስት አብያተ ክርስቲያናትና ስድስት ኪሎ ከሚገኘው ከያሬድ ትምህርት ቤት ሌላ በስሙ የተሰየመለት ምን አለ? ምእመናንም ትምህርት ቤት፣ ቤተክርስቲያን በመሥራት፣ በዓሉን በማክበር አስተዋጽኦ ማበርከት አለባቸው::

ቅዱስ ያሬድ በሚገባው መጠን ያልታወቀው ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ይመስለኛል:: ሌሎቹ ከውጭ የመጡ ቅዱሳን ስንት መታሰቢያ ቤተክርስተያን ነው የተሠራላቸው? ለቅዱስ ያሬድ ግን በአዲስ አበባ አንድ ብቻ ነው ያለው:: ወደ ሰሜንም በቅርቡ አክሱም ላይ የተሠራውና ገዳሙ ካልሆነ በስተቀር ሌላ የለውም:: ኋላ በ፲፪ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጡት ቅዱሳን በሺሕ የሚቆጠር የስማቸው መታሰቢያ ቤተክርስቲያን አላቸው:: ስለዚህ ቅዱስ ያሬድ አልተጨቆነም? አክበርነው ብለን እናስባለን? አባታችን መሆኑን የምንገልጸው በምንድን ነው?

ይህችን ቤተክርስቲያን ከቅዱስ ያሬድ ውጪ ማሰብም ከባድ ነው:: ግእዝ እንኳ ሕይወት ኖሮት እስከ ፫ኛው ሺሕ እንዲሸጋገር ያደረገው የቅዱስ ያሬድ ዜማ ነው:: ስለዚህ ምእመናን አውቀው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት አለባቸው:: ✦

## «ለችግሩ መፈጠር...»

ከገጽ ፴፯ የዞረ

አካል የለም:: ስለዚህ የሰው ጠያቂ ቢጠፋ ደግሞ መድኃኔዓለም ይጠይቃል፤ መጠየቁም አይቀርም:: ማዕከላዊነት ቢኖር ኖሮ ግን የበለጠ ሥራ መሥራት ይቻላል:: በአጠቃላይ ግን በአንድነት ተሰብስበን ያለፉትን ስሕተቶች ላለመድገም ምን እናድርግ? ብለን መወያየት እንድንችል ቤተክርስቲያን ሁኔታውን ማመቻቸት አለባት::

*ሐመር፦* በመጨረሻም የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ?

*መ/ር ዘመድኩን፦* እኔ ማገልገል እፈልጋለሁ:: የችግሩ አንዱ አካል ምሰሶም እኔ ስለሆንኩ፤ ሌሎችም እንደ እኔ የችግሩ አካላት ነን የሚሉ ተሰባስበው ምን እናድርግ በማለት መፍትሔ ማምጣት አለባቸው:: የምንሠራው ሥራ እንደሌላው የንግድ እንቅስቃሴ፣ የሸቀጥ ግብይት ብቻ አይደለም:: ጥሩ ከሠራን ትውልድን የሚቀርጽ አለበለዚያም የሚጎዳ ነገር ነው::

ሥራው ጥሩ ነው:: በሥጋም በነፍስም የምንቀደስበት ነው፤ የሚመጣውም ገንዘብ በረከት ያለው ነው:: ታዲያ ይህን ሥራ ለመሥራት ግን መሠረቱን እያፈረስን መሄድ የለብንም::

አሁን መዝሙራችን ዓለም አቀፋዊ አገልግሎትም እየሰጠ ነው:: ዘማርያኑ ከቤተ ክርስቲያኒቷ ቁጥጥር ውጭ ወደ ዐረቡ ዓለም፣ ደቡብ አፍሪካ፣ አሜሪካና አውሮፓ... ይሄዳሉ:: ቦታውንም እየተቆጣጠሩት ነው:: እዚህ አልመች ካላቸው አሁን እንዲያውም የተመቻቸ ነገር ተፈጥሯል፤ የፈለጉበት ቦታ ይሄዳሉ:: ማዕከላዊነት ቢኖር ኖሮ ግን እከሌና እከሌ እዚህ ሄዳችሁ አገልግሉ ይባል ነበር:: ማነው የላካቸው? ስንል መልስ የለውጠም:: ብቻ ሄደዋል፤ አሁን ተቆጣጠርንም አልተቆጣጠርንም፣ ዕውቅና ሰጠንም ዘማርያኑ እንደሆነ ዕውቅና እያገኙ መጥተዋል:: እነዚህ ክፍተቶችን ለመ ድፈን ቤተክርስቲያን ልጆቼ ብላ ጠርታ ልትሰበስበን ይገባል:: ካጠፋን እንቆን ጠጥ፤ እንመከር፤ ያለፈውን የባለፉትን ትተን ወደፊት አንድ ሆነን እናገልግል፤ ለሁሉም ግን ወሳኙ የቤተክርስቲያኒቱ አስተዳደር ትጋት ነው::

ስለዚህ በእኔ መዝሙር ቤት በወጡ ነገሮች ለመጠየቅ፣ ንስሐ ለመግባት፣ እስከ ዛሬ የሠራኹው ሥራ ሕዝቡን አሳስቷል በግልጽ ሕዝቡን ይቅርታ ጠይቅም ከተባልኩም ይቅርታ ለመጠየቅ ዝግጁ ነኝ::✦

## «ጡቶችሽም ...»

ከገጽ ፳፰ የዞረ

ዚህ ያለ መንፈስ ቅዱስ ርዳታ ሥራው የሚቻል አይደለም ማለት ነው:: ሦስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ እግዚአብሔር እንዲህ ያደረገበት ዓላማ ነው:: እግዚአብሔር ይህን ታሪክ እንዲገለጽና እንዲታወቅ ያደረገው ስለቅዱሳት መጻሕፍት ያለውን ሐሳብ እንድንረዳና በእርሱም ፈቃድ መሠረት እንድንፈጽም ስለሚወድ ነው:: ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ይህን የእግዚአብሔር ፈቃድ ዝም ብላው ልታለፍ አትችልም::

ከዚህም በላይ ሌሎቹን ትውፊቶቻችን መመልከት እንችላለን:: ለምሳሌ አሁን ያለው የታች ቤት የአንድም ትርጓሜ እንዲገኝ ምክንያት የሆኑት መምህር ኤስድሮስ መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው እጅግ ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍትን የመረመሩ እንደነበሩ ታሪካቸው ይመሰክራል::

ቅዱሳት መጻሕፍት ሲነበቡና ሲተረጐሙ ያለውን የጽጥታ ሁኔታ፣ ሒደቱም በጸሎት ካልተዘጋ በቀር መንቀሳቀስ አለመቻሉ ስለመንፈስ ቅዱስና ስለቅዱሳት መጻሕፍት ግንኙነት ያለንን እምነት የሚገልጽ ነው:: ወንጌልና አሥራው መጻሕፍት ሲነበቡ ብቻ ሳይሆን አዋልዱም ሲነበቡ ፍጹም ጸጥታ ይደረጋል:: ለአብነትም «የበረታ ቁሞ የደከመ ተቀምጦ ያድምጥ፤ ፍጹም ዝምታ ይሁን» የሚለው የተአምረ ማርያም መቅድምና ስለ ትንቢተ ኤርምያስ ንባብና ስለአንባቢው ዓይን ማልቀስ የሚናገረው የድርሳነ ሚካኤል መቅድም ሊጠቀሱ ይችላሉ:: አሁን አንባቢ ማስተዋል ያለበት በእነዚህ አዋልድ መቅድሞች ላይ ያሉት ታሪኮች መቼና በእነማን ተጻፉ የሚለውን እየመረመርን አለመሆኑን ነው::

ይልቁንም በቤተ ክርስቲያናችን ስለቅዱሳት መጻሕፍት ንባብና ትርጓሜ ያለውን ትውፊት ለመጠቆም ነው:: በመሆኑም እንደተገለጸው ሁሉ ትውፊታችን የሚያሳየው ቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀቱና ሃይማኖቱ ያላቸው እየጸለዩ የመንፈስ ቅዱስን ዕርዳታ በሚያገኙ ሰዎች መተርጐም አለባቸው የሚለውን ነው::

በዚሁ መሠረት የእኛ ቤተ ክርስቲያን የትርጉም ስልት አንደኛ ከዚህ ከተጠቀሰው እምነት የሚመነጭ ነው:: ወደ ሥራው ሲገባ ደግሞ ለሥራው የሚመጥን በቂ ዕውቀት፤ በተለይም የግእዙን ሰዋስውና ቃላቱ የሚሸከሙትን ትርጉም፤ ከዚያም ጋር በገቡበት ዓረፍተ ነገር ውስጥ ያላቸውን ዐውደ ይዘታዊ ፍቺ /Contextual meaning/ በደንብ ተረድቶ የመተርጐም ብቃት በቅድሚያ የሚጠበቅባቸው ነገር ነው::

ከዚህም አልፎ የእኛ የቀድሞ ሊቃውንት በተናጥል የተረጐሙትን በተለይ ደግሞ በአንድምታው ትርጓሜ ላይ ታሪኩን ከመተረካቸው፣ ትርጉሚውን

ወደ ገጽ ፴፱ ዞሯል



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

የሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል የግእዝ ቋንቋ ያለውን የማይተካ ዘርፈ ብዙ ሚና በማጤንና የአንባብያንን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ይህን «አቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት» የተሰኘ ዓምድ ከ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. ጀምሮ መክፈቱ ይታወሳል:: በዓምዱ የሚቀርበው ትምህርት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራንና ተማሪዎች በሚያዝያ ወር ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በተቋቋመው «የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ማኅበር» የሚዘጋጅ ነው:: ማኅበሩ ለግእዝ ቋንቋ ፍላጎት ያላቸውን ሁሉ በቋንቋው ማንበብ፣ መጻፍና መናገር የማስቻል፣ በቋንቋው የተጻፉትን ዕድሜ ጠገብ መጻሕፍት በመመርመር ያካበቱትን ልዩ ልዩ ሀብት ለትውልድ የማቆየት ዓላማና ግብ አንግቦ የተነሣ ነው::

*መ/ር ደሴ ቀለብ*

# በ ግ እ ዝ  እ ን ነ ጋ ገ ር

## «ትውልድ የኀልፍ ወትውልድ ይተርፍ»

### ለትውልደ ሣልሳይ ሺሕ ዐመት

ሰላም ለክሙ ትውልድ ቀደምት ዘዕሥራ ምእት ዕንቋ አብጽሐክሙ ለሣልሳይ ሺሕ ዘመን:: ዘመንሰ ንሕነ ውእቱ:: ወዘመንሰ ፈረስነ ውእቱ ዘንረውጽ ወዘነሐውር ቦቱ:: እፎ ኀለፈ ዘመነ አበዊነ? ወእፎ ይእቲ እምነቶሙ? ወእፎ ኀለፈ ዘመነ ሊቃውንት፣ ካህናት፣ ዲያቆናት... በቀዳማይ ወበካልዓይ ሺሕ ዓመት ወምንተ ገብሩ እለ ካሌብ ወላሊበላ ወአባ ጊዮርጊስ? ወእፎ ሐነፁ አብያተ ክርስቲያናት በበደወሉ? ወእፎ ሀለው በፍቅር ወበሰላም ምስለ ሕዝብ ወአሕዛብ? በአማን አበዊነሰ ትጉኃን ውእቶሙ ለሀገር ወለቤተክርስቲያን:: ወኮኑ እለ ያፈቅሩ ሀገሮሙ ወእለ ይደግሙ /ይጼልዩ/ መዝሙረ ዳዊት ወውዳሴ ማርያም:: ወንሕነኒ ትውልድ ዘሣልሳይ ሺሕ ዘመን...? እንዳኢ!:: አኀውየ ወአኀትየ ጸልዩ ላቲ ለሀገርነ ወለቤተክርስቲያንነ ቅድስት:: ኢንኩን መፍቀርያነ ዓለም ዘየኀልፍ:: ዘመንነ እግዚአብሔር ውእቱ:: በከመ ይቤ ጳውሎስ እመኒ ንመውት ለእግዚአብሔር ንመውት ወእመኒ ነሐዩ ለእግዚአብሐር ነሐዩ:: ለምንት ውእቱ ዘአልብነ ፍቅር? ለምንት ኢንትፋቀር በበይናቲነ? ለምንት ውእቱ ሃይማኖትነ? ለተርእዮኑ? ለስምኑ? አይቴ ውእቱ መካነ ዕረፍትነ? ወአይቴ ውእቱ አክሊልነ? አኮኑ በሰማይ በኀበ አምላክነ?

ዓለምሰ ትስሕብነ በሐብለ ሙስና ወታወርደነ ታሕተ:: በእንተዝ ንቁም በበሕላዌነ በነሢአ መስቀሉ ለመድኀኒነ:: አሜሃ ሀገርነ ትጸንዕ ከዊና መልዕልተ አህጉር ዘዓለም:: አ ደቂቀ እምየ ቤተክርስቲያን ነያ ሠናይት ኢትዮጵያ ከመ ጽጌ ገዳም:: ምንተ ንግበር ለእምነ ቤተ ክርስቲያን ወለርስትነ ኢትዮጵያ:: አምሳለ ወርቅ ንግበር ላቲ:: እስመ መንገለ አቡሃ መልከ ጼዴቅ ወመንገለ እማ ንግሥተ አዜብ አልቦ ዘይትኤረያ:: ወልሳና ግእዝ ብሔረ ዓለም ውእቱ:: ዝማሬሃ ዝማሬ መላእክት ውእቱ:: እንተ በምድር ሥረዊሃ ወበሰማይ አዕጹቂሃ ይእቲ ሐረገ ወይንነ ኢትዮጵያ:: ወእፌጽም ነገርየ እንዘ እብል «ንኩን እንከ ከመ ብእሲ የዋሕ ዘይጸውም ወይጼሊ ወያስተሠሪ በእንተ ኀጢአቱ፤ ንሑር በጽድቅ ንርከብ ሠናየ ወናክብር ሰንበተ ወንትመሀር ገቢረ ሠናይ:: ወእፎ ትበጽሕ ተዋሕዶ ሃይማኖትነ ለዓለም?

«ርኢነ ሰማየ ሐዲሰ ወምድረ /ዘመነ ሐዳሰ/»

*ሎቱ ስብሐት ወለወላዲቱ ድንግል*
*አነ ድኩም ኀጥእ እትኩሙ ፍሬ ጽድቅ*
*/አሐዱ ኀጥእ ዘእም ቤተሰብእ ዘግእዝ/*



## «ጡቶችሽም ...»

ከገጽ ፴፰ የዞረ

/አንድሙን/ ከማውረዳቸው፣ ከማመስጠራቸውና ከማራቀቃቸው በፊት ንባቡ ላይ የሠሯቸውን ሥራዎች በበቂው ግምት ውስጥ ማስገባት ይጠይቃል:: እነዚህ ጥቁምታዎች በዘመናዊ መንገድ ቢጠኑ ከፍተኛ መፍትሔ ሊሰጡ ይችላሉ:: ለምሳሌ ያህል ሁለቱን ነጥቦች ላንሣ:: አንደኛው «አብነት እንዲህ ይላል፣ በአብነቱ እንዲህ የሚል አለ፤ እንዲህ የሚል ንባብም አለ፣» የሚሉትን አገላለጾች የተመለከተ ነው:: «አብነት» የሚሉት ብዙ ጊዜ ሳይነካካ ከቀድሞ መምህራን ጀምሮ የነበረውን ንባብና «ምስክር» የሆኑት መምህራን በጥንቃቄ እየጠበቁ ለትውልድ የሚያሸጋግሩት ንባብ ነው:: ታዲያ በዚያ ንባብ ውስጥ የከበደውን ቋንቋ የአንድ ዘመን ሊቅ ለዘመኑ በሚመጥን ቢተረጉመው አብነቱን (ያን የጥንቱን) አያጠፋውም:: ስለዚህ የኋላ መምህራን ያንን የጥንቱን በማግኘታቸው ሁልጊዜ «እንዲህ ይላል አብነት» እያሉ ያመጡታል:: ይህም በዕውቀታቸው ሳይመኩ፣ በአዲስ መልክ ለዘመናቸው በሚረዳው ሲተረጉሙም የቀደመውን ሳያጠፉ የመጡበት መንገድ ነው::

«እንዲህ የሚል ንባብም አለ» የሚለው ደግሞ አሁንም ጥንት ከአንድ በላይ ትርጉም መኖሩን የሚያመለክት ነገር ነው:: ስለዚህ ተርጓምያኑ እነርሱ ከተቀበሉት ቅጅ ውጪ ሌላውንም የሚያገላብጡ መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን ሲጠቀሙበትም ከሌላ ማምጣቸውን ለመግለጽና ያንኑ ለማብራራት የሚጠቀሙበት መንገድ መሆኑን ነግረውናል ማለት ነው:: የዘመናቸው የመረጃ አሰጣጥ ትውፊት ይህ ነበርና:: /ኅትመት ስላልነበር ዓመተ ምሕረት፣ ተርጓሚ፣ ... የመሰለውን ልንጠብቅባቸውና በዚህም ሊወቀሱም አይገባም/::

ሁለተኛው ደግሞ «መጽሐፍ ምስጢር እንጂ ዘይቤ አይጠነቀቅም» የሚለው ብሒላቸው ነው:: ይህን ብሒል ከተናገሩ በኋላ ንባቡን ያቀኑታል ወይም «እንደዚህ ብለው ይገጥሟል» ይሉና መልእክቱን የሚያስረዳ ሐረግ ከሌላ የመጽሐፍ ክፍል አምጥተው ይገጥሙለታል:: እዚህ ላይ በጥንቃቄ መረዳት ያለብን አንደኛ ይኸው ጉዳይ የሚፈጸመው በአንድምታ ትርጓሜ ወቅት መሆኑን ነው:: ይህን ያነሣነው ግን ለሦስት ነገሮች ያለውን አስተዋጽኦ ለመጠቀም ነው:: በመጀመሪያ ደረጃ የእኛ ሊቃውንት ያገኙትን ንባብ

ወደ ገጽ ፵ ዞሯል



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# በግእዝ እንነጋገር

**ቆስጠንጢኖስ**

እፎ ኀደርኪ እምየ?
እንዴት አደርሽ እናቴ?
አይቴ ተሐውሪ በጽባሕ?
በጧት የት ትሔጃለሽ?
ኀበ ሜድትራንያንኑ?
ወደ ሜድትራኒያን ነውን?
ለምንት?
ለምን?
ምንተ ትገብሪ በኢየሩሳሌም?
በኢየሩሳሌም ምን ታደርጊያለሽ?
አይቴ ውእቱ መስቀል ትዕምርትነ?
ምልክታችን መስቀል የትነው?
መኑ ይነብበኪ በኀበ ሀሎ
ያለበትን ማን ይነግርሻል?
ዐቢይ ውእቱ ክብርኪ እምየ
እናቴ ክብርሽ ታላቅ ነው
ማእዜ ትትመየጢ ኀበ ሮም
ወደ ሮም መቼ ትመለሻለሽ?
ፍኖትኪሰ ዘያደክም ይመስለኒ
ወእምድኅረ ዝንቱስ አይቴ ውእቱ ፍኖትኪ
ከዚህ በኋላ መንገድሽ ወዴት ነው?
መንገድሽስ የሚያደክም ይመስለኛል
ወበዝንቱ ንመውእሙ ለኵሎሙ ፀርነ
በዚህም ጠላቶቻችን ሁሉ ድል እናደርጋቸዋለን

**እሌኒ**

ሎቱ ስብሐት ወልድየ
ምስጋና ለሱ /ጌታ/ ልጄ
ኀበ መርሶ ሐመር
ወደ መርከቡ ወደብ
እዎ
አዎ
አነ አሐውር ኀበ ኢየሩሳሌም
እኔ ወደ ኢየሩሳሌም እሔዳለሁ::
አነ አኀሥሥ መስቀለ ክርስቶስ አምላኪየ
የአምላኬን የክርስቶስን መስቀል እፈልጋለሁ
ውስተ አድባረ ኢየሩሳሌም ውእቱ
በኢየሩሳሌም ተራሮች ነው
እግዚአብሔር ዘፈነዎ
እግዚአብሔር የላከው
መስቀል ውእቱ ክብርየ ወኀይልየ
ክብሬም ኀይሌም መስቀል ነው::
እምድኅረ ተፈጸመ ሊተ ተምኔትየ
ምኞቴ ከተፈጸመልኝ በኋላ
መስቀል ብሂል መከራ ውእቱ
ኀበ ኢትዮጵያ ከመ ይብራህ ደመራሁ ለኵሉ ዓለም
ደመራው ለዓለም ሁሉ ይበራ ዘንድ ወደ ኢትዮጵያ እሔዳለሁ
መስቀል ማለት መከራ ማለት ነው::
በአማን
በእውነት



## «ጡቶችሽም ...»

ከገጽ ፴፱ የዞረ

ሳይሸራረፉ የማስተላለፍ ቃል ኪዳናቸውን ነው:: ሲተረጉሙ መልእክቱን እንድንረዳው ሰዋስውን አስተካክለው ሲያስቀምጡ የመጀመሪያውን ቅድሚያ ሰጥተው ያስቀምጡልናል:: በሁለተኛ ደረጃ «ዘይቤ አይጠነቅቅም» ሲሉ የቅዱሳት መጻሕፍት ትኩረት መልእክታቸውን መንገር ነው፤ ካሉን በኋላ እኛን /አንባቢን/ ለመረዳት ደግሞ ሰዋስው ያስተካክላሉ ማለት ነው:: ይህም ምስጢሩን ሳያዛቡ ንባቡን ተነባቢ ለማድረግ የሚያስችል ከፍተኛ ዕውቀት ያላቸው መሆኑን ያሳየናል:: ሦስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ የሰውንም የመንፈስ ቅዱስንም ድርሻ ጠቁመውናል:: በትርጉም ወቅት ሰውየው /ሊቁ/ የሚተረጉመውን ጽሑፍ ቋንቋ ሰዋስው አርሞ ወደ ተቀባይ ቋንቋ ማምጣት የሚችልበት አቅም ያለው መሆን አለበት ማለት ነው:: ይህም ማለት አንድ ሰው ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ሲተረጉም የእንግሊዝኛውን ሰዋስው በደንብ ማወቅና ጽሑፉ /እንግሊዝኛው/ የተሳሳተ ሰዋስው ቢኖርበት እንደተሳሳተ ከመተርጎም ይልቅ የእንግሊዝኛውን ሰዋስው አስተካክሎ ቢተረጉመው የተሻለ መሆኑን የሚያሳይ ነው:: የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ ወይም ርዳታ የሚያስፈልገው ደግሞ «መልእክቱ» ላይ ነው:: «ምስጢር ይጠነቅቃል» ማለትም መልእክቱን በፍጹምና በፍጹም ማዛባት አይገባም ማለት ነው:: ይህ ማለት ደግሞ ሊያዛባ በሚችል ቃል መለወጥ አይቻልም /አይገባም/ ማለት ነው:: «ድንግል» እና «ሴት» እንደሚለው ማለት ነው:: ይህን መጣስ ከመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ለመውጣት ወይም ደግሞ ርዳታው አያስፈልገኝም ማለት ነው::

ስለዚህ አዲሱ የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ የቀደመው ላይ «አተረጓጎሙ ስልት» ጥያቄ አነሣ ማለት በዚያኛው የምስጢር መዛባት የሚያመጡ ቃላት ስለነበሩ እነርሱን አስተካክያለሁ ለማለት ነው:: አሁንም ግን እነዚህን በምሳሌ አሳይተውን ቢሆን ኖሮ እንዴት ጥሩ ይሆን ነበር:: ለማንኛውም በዚህ ጽሑፍ ቀጣይ ክፍል ላይ በትንሹም ቢሆን እነዚህን ጉዳዮች መመርመራችን አይቀሬ ነው:: መጽሐፍ ቅዱሱ እንደጠቀሰው እነዚህን ችግሮች ለመፍታት እስከ ተዘጋጀ ድረስ በእጅጉ ያስፈልገናል፡: ይህን ጉዳይ ለማጠቃለል በዚህ ጽሑፍ የመጀመሪያ ዕትም /ሐመር ግንቦት/ሰኔ ፳፻/ ዓ.ም/ ካነሣናቸው የትርጉም ዓይነቶች ውስጥ የዚህ ትርጉም ሥራ ወደየትኛው ይቀርባል? በርግጥ የጨመረው ወይም የጐረደው ወይም የለወጠው ዘርዕ አለን? ለምሳሌ? የቁጥሩስ ጉዳይ?♦

*ይቀጥላል::*



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# የደመራ በዓል አከባበር በአዲስ አበባ

በ፲፱፻፳ ዓ.ም የደመራ በዓል የተከበረው በጃን ሜዳ ነበር። በወቅቱ በነበረው ሥርዓት መሠረት መስከረም ፲፮ ቀን ከሰዓት በኋላ ጀምሮ ከፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ጀምሮ ሁሉም ሠራዊቱን አሰልፎ በንጉሡ በጳጳሱና በእጨጌው እንዲሁም በእንግዶች ፊት ያልፍ ነበር። በ፲፱፻፱ ዓ.ም ግን ልጅ ኢያሱን አውርደው ንግሥት ዘውዲቱንና ራስ ተፈሪን አልጋ ወራሽ ለማድረግ በሚኒስትሮች የተመከረው ምክር ፍጻሜ ያገኘ ዘንድ የተቀጠረው ለመስከ ረም ፲፮ ቀን ስለነበረ የደመራ በዓል በየአጥቢያው ተከብሮ እንዲውል ተወሰነና በዚያው መሠ ረት ተፈጸመ።


ከዚህ በኋላ ባሉ ዓመታት በተለመደው ስልፍ ቢከበርም በ፲፱፻፲፰ ዓ.ም ግን በፍል ውኃ ሜዳ በልዩ ሁኔታ ተከበረ። የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎ ችም የሰልፉ ተሳታፊዎች ነበሩ። የተፈሪ መኮንን ት/ቤት ተማሪዎችም ልዩ መዝሙር አቅርበው ነበር። በዓመቱ መስከረም ፲፮ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ.ም ደግሞ በዚያው በፍል ውኃ ሜዳ ከቀድሞው በበለጠ ተከበረ። በዚህ ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ማርሽ እና የተፈሪ ማርሽ የሚባሉት በዓሉን በመዝሙር አጅበው ዋሉ። /መዝሙሩ ከታች አለ/ በ፲፱፻፳ ዓ.ም ደግሞ የደመራ በዓል የተከበረው አራዳ ጊዮርጊስ ፊት ለፊት ባለው አደባባይ ነበር። ከዚህ በኋላ ግን ተመልሶ በፍል ውኃ ሜዳ /የአሁኑ መስቀል አደባባይ/ ይከበር ጀመር። /የሃያኛው ክ/ዘመን ትውስታዬ ገጽ.፻፵፪፣ ፪፻፺፯፣ ፫፻፲፯፣/ በዓሉ በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ደግሞ የበለጠ በብዙ ሕዝብ ፊት በግሩም ሥር ዓት እየተከበረ ኖረ።

ደርግ ከመጣ በኋላ ግን አደባባዩን ስሙን ለውጦ ግብሩን አጥፍቶ አደባባዩን እንዳንጠቀም ከለከለ። በዚህ ምክንያት ለሁለት ዓመታት እንደገና በአ ራዳ ጊዮርጊስ አደባባይ ተከበረ። በኋላ ግን ደር ግም ሁኔታውን አይቶ ፈቀደና በዚያው ባሁኑ አደባ ባይ መከበሩ ቀጠለ። እስካሁንም በዚያው ይከበራል። ከደርግ መምጣት በኋላ የጦሩና የሚንስትሮች፣ የመኳንንቶችና የመሳሰሉት ሰልፍም በሰንበት ት/ቤት ወጣት መዘምራን ሰልፍ ተተካ።

ከ፴ ዓመታት በኋላ ደግሞ የሀገሪቱ ርእሰ ብሔር ፕሬዜዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስ እንደ ገና ለመጀመሪያ ጊዜ በ፲፱፻፺፮ ዓ.ም በደመራ በዓል ተገኙ። በዚሁ ምክንያትም ፖሊስና የመከላከያ ማርሾችም በአደባባዩ ተገኝተው በዓሉን እንደ ጥንቱ በማርሽ ሙዚቃ አጀቡት። በ፳፻ ዓ.ም ደግሞ የኢትዮጵያ አቆጣጠር ሁለት ሺሕ ዓመት መሙላት /የሁለት ሚሊኒዬም ማለቅ/ እና የሦስተኛው ሺሕን ዋዜማ ማክበረ ጋር ተያይዞ የግሪክ፣ የአርመን፣ የሕንድና እና የሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በተገኙበት እጅግ ደማቅ በሆነ ሥርዓት ተከበረ። በዓሉ የሚሌነየሙ /የእሥራ ምዕቱ/ የመጨረሻ በዓል በመሆኑ ምክን ያት በቀጥታ የቴሌቭዥን ሥርጭት ተላለፈ። ለበዓሉ የተገኙት የውጭ ሀገር ፓትርያርኮች፣ ጳጳሳትና ሌሎች እንግዶች ወደ አደባባዩ ደርሰው የቦታ ውን ስፋት በተመለከቱ ጊዜ ለምን እንደዚህ ባለ ሰፊ ቦታ ተደረገ ብለው አዘኑ። ቆይተው የሕ ዝቡን መሙላትና የአደባባዩን መጨነቅ በተመ ለከቱ ጊዜ ደግሞ ተደነቁ። ብዙዎቹም ቆመው በአንክሮ ይመለከቱ ነበር። ወደ በዓሉ የሚገባው ሁሉ ጧፍ ተሰጥቶት ስለነበር ከምሽቱ አንድ ሰዓት በሆነ ጊዜ ደመራው በተቀጣጠለና ርችቱ በተተኮሰ ጊዜ ሕዝቡም ጧፉን አበራና አደባባዩ በብርሃን ደመቀ፤ መስቀሉም በዚያ ዓመት ተቆጠ ፍሮ የወጣ እስኪመስል ድረስ በእጅጉ ደምቆ ተከበረ። የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የበዓሉን ዝግጅት ማስተባበር እንደተለመደው ሁሉ ሓላፊ ነቱ ቢሆንም በዚህ ዓመት ግን ልዩ ታሪካዊ አድርጎ አስከበረው። የበዓሉ አከባበር ትውስታም ለረጅም ጊዜ ያት ከመዝለቁ በላይ መስከረም ፩ ቀን በልዩ ድምቀት መንግሥት ካዘጋጀው የሚሊኒ የም በዓል ይልቅ የደመቀና ሕዝቡንም ሁሉ ያስደሰተ ነበር።♦











## ከጥንት የደመራ መዝሙሮች

### ሀ

መስቀሉ የጌታችን
መታሰቢያ የአምላካችን
የክርስቲያን ኒሻናችን።
እንድናገኝ ከበሬታ
በትምህርታችን እንበርታ
አንታለል በጨዋታ
ጥበብ ወዷል የእኛ ጌታ።
እንዳፈቀርህ ጥበብን
ያርዝምልን ዕድሜህን
ከዓለምህ ጋር ከመነን
ይባርክልን ዘርህን።
እንድንኖር በትዕግሥት
ሰብስቦናል በአንድነት
ፍቅር ይስጠን መለኮት
እንድንረዳ ለመንግሥት።

በ፲፱፻፲፰ ዓ.ም የተፈሪ መኮንን ተማሪዎች በደመራ ሰልፍ የዘመሩት።

*ምንጭ፦/የሃያኛ ክፍለ ዘመን መባቻ፣ ገጽ፣ ፪፻፺፰/*

### ለ

ኢትዮጵያ ሆይ ደስ ይበልሽ፣
በአምላክሽ ኃይል በንጉሥሽ
ተባብረዋል አርበኞችሽ
አይነካም ከቶ ነጻነትሽ፣
ብርቱ ናቸውና ተራሮችሽ፣
አትፈሪም ከጠላቶችሽ።
ድል አድራጊው ንጉሣችን፣
ይኑርልን ለክብራችን።
ብርቱ ናቸውና ተራሮችሽ፣
አትፈሪም ከጠላቶችሽ
ድል አድራጊው ንጉሣችን፣
ይኑርልን ለክብራችን።

ይህ መዝሙር በ፲፱፻፲፰ ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በመስቀል በዓል ላይ በኢትዮጵያ ማርሽ ተዘመረ በኋላ የሀገሪቱ ብሔራዊ መዝሙር ሆኖ አገልግሏል።

*ምንጭ: /የሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፣ ገጽ. ፫፻፲፯/*

''ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም'' ማቴ ፬፥፬




# አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ

- የስብከት ታሪካዊ አመጣጥና ዓላማ፣
- ክርስትናና ዘመናዊነት፣
- ክርስትናና ጉርብትና፣ ከማይመስሉን ጋር እንዴት እንኑር?
- እምነትን የሚያቀዘቅዙ ነገሮች፣
- ስለምን መሬት ትጕሰቈላለች?

የሚሉ ጉዳዮችና ሌሎች በሰፊው የተዳሰሱበት
ወቅታዊ መጽሐፍ

አርታዒ:- ዲ/ን ታደሰ ወርቁ
አሳታሚና አከፋፋይ:- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን

ሜጋ ማተሚያ ኃ.የተ.የግ.ማኅበር

ዋጋ 4.00

©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፤እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡